FaithLife Ministries
"Equipping Church Leaders Globally"

# አስተዳደር
# ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች ™

## የሥልጠና መምሪያ

## ቅጽ 1

**"እግዚአብሔር እንዲመሩ የጠራቸውን አገልግሎት ማስተዳደር እንዲችሉ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ማገዝ"**



**© 2010, 2006, 2002 by Barry Voss**
**FaithLife Ministries, Inc.**
**www.faithlifeministries.net**
**ስልክ፦ (770) 492-4903**
**ኢሜይል፦ BarryVoss@comcast.net**

# መግቢያ

ይህ የሥልጠና መምሪያ የተዘጋጀው መጋቢዎችን፣ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኛ እና አገልጋዮችን፣ እንዲሁም የአገልግሎት መሪዎችን የተጠሩባቸው የአገልግሎት መስኮች እንዴት ማስተዳደር እንዳለባቸው እንዲያውቁ ነው። መጋቢዎችን እና የአገልግሎት መሪዎችን ለስብከት፣ ለማስተማር፣ እንዲሁም ወንጌልን ለማሰራጨት የሚያዘጋጁ ብዙ ሴሚናሪዎች እና የመጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጆች ቢኖሩም፣ ያሏቸው ሥርዓተ ትምህርቶች አብዛኛውን ጊዜ መሠረታዊ የሆኑ የአስተዳደር ክህሎቶችን እንኳ ያካተቱ አይደሉም። አብዛኞቹ መጋቢዎች እና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ሰዎችን የመምራት፣ ግብዓቶችን በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የማመቻቸት፣ እንዲሁም አብያተ ክርስቲያናትን የማስተዳደር ኃላፊነት አለባቸው። በዚህ ምክንያት፣ እንዲህ ዓይነቱ ሥልጠና የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እና መጋቢዎች አንዴ አገልግሎት ላይ ከተሰማሩ ወዲህ እንዲያደርጉ ለሚጠብቅባቸው ነገር ለማዘጋጀት የታለመ ነው።

የዚህ መምሪያ ደራሲ ከ1996 እ.ኤ.አ አንሥቶ በተልዕኮ የአገልግሎት መስክ የተሰማሩ የቤተ ክርስቲያን እና የአገልግሎት (ሚኒስትሪ) መሪዎችን ሲያሰለጥኑ የቆዩ ናቸው። ይህ የሥልጠና መምሪያ ለበርካታ ዓመታት በልዩ ልዩ አገሮች ውስጥ ካሉ መጋቢዎች ጋር ስንሠራ ካስተዋልነው ቁሳቁስም ሆነ ልዩ ልዩ ግብዓት የማስተዳደር ሥልጠና ክፍተት የመነጨ ነው። ይባስ ብሎ፣ እንዲህ ያለ ይዘት ያለው ትምህርት ሲሰጥ እምብዛም አይታይም። በመሆኑም፣ በታዳጊ አገራት የሚገኙ ብዙ መጋቢዎች እና መሪዎች መሠረታዊ የአስተዳደር ሥልጠና የማግኘት ዕድላቸው የተገደበ መሆኑን በማጤን፣ ፌይዝላይፍ ሚኒስትሪስ ክፍተቱን ለመሙላት የታሰበ መምሪያ አዘጋጅቷል።

በዚህ የሥልጠና መምሪያ ውስጥ የተከተተው ይዘት፣ ከክርስቲያናዊ እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታ አንጻር የአስተዳደር መሣሪያዎች እና ዘዴዎች ላይ መሠረታዊ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የታሰበበት ነው። እነዚህ መሣሪያዎች እና ዘዴዎች በመንፈስ ቅዱስ ምሪት እና በእርሱ ላይ በመደገፍ ጥቅም ላይ ሲውሉ፣ ለእግዚአብሔር መንግሥት "በበጎ ሥራ ሁሉ ፍሬ" (ቆላስይስ 1፥10) ለማፍራት እንደሚውሉ እምነታችን ነው።

**© 2010, 2006, 2002 by Barry Voss, FaithLife Ministries, Inc.**

**መብቱ የተጠበቀ ነው። በኮፒራይት ሕግ ከተደነገገው በቀር፣ ያለ ደራሲው ፈቃድ ይህንን ሕትመት በከፊልም ሆነ በሙሉ ማባዛት፣ ቀድቶ ማስቀመጥ፣ በሌላ በኤሌክቶርኒክ፣ መካኒካል፣ ፎቶ ኮፒ፣ በድምጽ ቅጂ ወይም ማንኛውም መንገድ ማሠራጨት አይቻልም። ከዚህ በተለየ መጠቀም የሚቻለው ይህ ሕትመት ይዞታው ሳይለወጥ እና ያለ ምንም ክፍያ በአንድ አካባቢ ተገድቦ ጥቅም ላይ ሲውል ብቻ ነው፤ እንዲህ ከሆነ እንደ ሁኔታው አባዝቶ መጠቀም የሚፈቀድ እና የሚበረታታ ነው።**

# ስለ ፊይዝላይፍ ሚኒስትሪስ

ፊይዝላይፍ ሚኒስትሪስ የተጀመረው በጥር ወር 2001 እ.ኤ.አ በቤሪ ቮስ እና ኪም ስታር ቮስ ሲሆን፣ ዓላማውም በመላው ዓለም ለሚገኙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የአገልግሎት ሥልጠና እና ግብዓቶችን ለማቅረብ ነው። ቤሪ እና ኪም ቮስ በተለይ የገንዘብ እና ለዚህ ዓላማ የሚውሉ ግብዓቶች እጥረት ባሉባቸው የዓለም ክፍሎች የሚገኙ የእግዚአብሔር ሰዎችን ለአገልግሎት ደቀ መዝሙር የማድረግ እና የማስታጠቅ ቅንዓት አላቸው። አገልግሎትን/ሚኒስትሪን የመምራት ክህሎቶች ላይ አጽንዖት በመስጠት በልዩ ልዩ አገራት የሚገኙ መጋቢዎችን፣ የልጆች፣ የወጣት እና የአዋቂ አገልግሎት መሪዎችን ሲያሰለጥኑ ቆይተዋል። የሥልጠና ኮንፍረንሶችን እና ወርክሾፖችን ከማካሄድ በተጨማሪ፣ የራሳቸውን የሥልጠና መገልገያዎች ያዘጋጃሉ፤ ሁሉም አማኞችም እምነታቸውን የሚያንጸባርቅ ሕይወት እንዲኖሩ ያበረታታሉ።

ኪም ከዚህ ቀደም አልፋሬታ፣ ጆርጂያ (አሜሪካ) በሚገኘው ክራይስት ዘ ሼፐርድ ቤተ ክርስቲያን የልጆች የደቀ መዝሙርነት አገልጋይ የነበሩ ሲሆን፣ በዚያም ከ500 በላይ የሚሆኑ ልጆች እና አዋቂዎችን ያገለግሉ ነበር። ከአገልግሎት በተጨማሪም ከ15 ዓመታት በላይ በትልልቅ ድርጅቶች የኮምፒዩተር ሲስተም እና ፕሮጀክቶች አስተዳዳሪ ሆነው ሠርተዋል። ከ20 ዓመታት በላይ በቢዝነስ ዓለም ውስጥ ልምድ ያካበቱት ቤሪ ቤሪ በአሁኑ ጊዜ ሙሉ ጊዜያቸውን ለአገልግሎት የሰጡ ሲሆን፣ በአሁኑ ጊዜ ሙሉ ጊዜያቸውን ለአገልግሎት ሰጥተዋል። በአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናቸው ውስጥም በአምልኮ እና በወንዶች አገልግሎት ውስጥ ይሳተፋሉ። ኪም እና ቤሪ ለ35 ዓመታት በትዳር የቆዩ ሲሆን፣ ሁለት የአዋቂ ዕድሜ ላይ የሚገኙ ልጆች አሏቸው።

# ምስጋና

ከሁሉ አስቀድመን ይህ ፕሮጀክት እውን እንዲሆን ያስቻለውን እና ይህንን የሥልጠና መምሪያ እንድናዘጋጅ ራዕዩን የሰጠንን አምላካችንን እግዚአብሔርን እናመሰግናለን። እንዲሁም ኬን ጃክ፣ ዳሪል ሆህ፣ ዶሚንግ ኦርፔቺዮ፣ አዩብ ካዮ፣ እና ዴቪድ ኩዊስፒሮካን በአርትዖት እና ለዚህ መምሪያ ግብዓት በማቅረብ ላደረጉት ድጋፍ ልናመሰግናቸው እንወዳለን።

# <u>አስተዳደር ለቤተ ክርስቲያን መሪዎች</u>
## <u>ቅጽ 1</u>

**<u>ማውጫ</u>**


**<u>ክፍል 1:-</u>** **የአገልግሎት (ሚኒስትሪ) አመራር**

ምዕራፍ 1 የአገልግሎት (ሚኒስትሪ) አመራር
ምዕራፍ 2 መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሪ መሆን
ምዕራፍ 3 የአመራር ዘይቤዎች
ምዕራፍ 4 መሪዎችን ማፍራት/ማሳደግ

**<u>ክፍል 2:</u>** **ሰዎችን ማስተዳደር**


ምዕራፍ 5 መንፈሳዊ ስጦታዎች
ምዕራፍ 6 ሰዎችን ማስተዳደር
ምዕራፍ 7 ግጭትን መፍታት
ምዕራፍ 8 ደቀ መዛሙርትን ማፍራት

**<u>ክፍል 3:</u>** **ግብዓት አስተዳደር**

ምዕራፍ 9 ስልታዊ (ስትራቴጂክ) ዕቅድ ማውጣት
ምዕራፍ 10 ገንዘብ አያያዝ
ምዕራፍ 11 የጊዜ አጠቃቀም
ምዕራፍ 12 መረጃ ማደራጀት

# ክፍል 1

# <u>የአገልግሎት (ሚኒስትሪ) አስተዳደር</u>



**ምዕራፍ 1**

# <u>የአገልግሎት (ሚኒስትሪ) አመራር</u>

***"በእናንተ ኀላፊነት ሥር ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ የምትጠብቁትም ከእግዚአብሔር እንደሚጠበቅባችሁ በግድ ሳይሆን በፈቃደኝነት፣ ለጥቅም በመስገብገብ ሳይሆን ለማገልገል ባላችሁ ጽኑ ፍላጎት ይሁን፤ እንዲሁም በዐደራ ለተሰጣችሁ መንጋ መልካም ምሳሌ በመሆን እንጂ በላያቸው በመሠልጠን አይሁን። የእረኞች አለቃ በሚገለጥበት ጊዜ የማይጠፋውን አክሊል ትቀበላላችሁ።"***
**1 ጴጥሮስ 5፥2-4**

ጠንካራ የአመራር ክህሎቶች ለማንኛውም የቤተ ክርስቲያን መሪ አስፈላጊ ናቸው። እነዚህ ክህሎቶች የሚጎድሏቸው የቤተ ክርስቲያን መሪዎች፣ አገልግሎቶችን ወደ ፊት ለማራመድ እና በቤተ ክርስቲያን ተልዕኮ ውስጥ ሰዎች በንቃት እንዲሳተፉ ለማድረግ ይቸገራሉ። በቀላሉ፣ አመራር ወይም መሪነት አንድን ሰው፣ ሰዎች አንድ ተፈላጊ ግብ ወይም ውጤት ላይ እንዲደርሱ ለማነሣሣት የሚያስችሉት ክህሎቶች ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ይሁን እንጂ መሪነት ራዕይ መሰነቅ እና ዕቅድ ማውጣትን፣ እንዲሁም ሰዎችን ማብቃትን እና ግብ ማሳካት ላይ ማተኮርንም ይመለከታል። በዚህ ምዕራፍ ውጤታማ ለሆነ የአገልግሎት መሪነት ወሳኝ የሆኑ 5 ቁልፎችን እናያለን።

ጥያቄ: ማንኛውም መሪ "መሪ" እንዲባል፣ ምን ሊኖረው ያስፈልጋል?
መልስ: **ተከታዮች!**

***የሚከተልህ ከሌለ፣ መሪ አይደለህም።**

## <u>5 የውጤታማ የአገልግሎት መሪነት ቁልፎች</u>

### #1. <u>*መሪዎች ሥልጣንን ሳይሆን ተጽዕኖን ይጠቀማሉ*</u>

**ዮሐንስ 10፥2-4**
***"በበሩ የሚገባ ግን እርሱ የበጎቹ እረኛ ነው፤ በር ጠባቂው በሩን ይከፍትለታል፤ በጎቹም ድምፁን ይሰማሉ። የራሱንም በጎች በየስማቸው እየጠራ ያወጣቸዋል። የራሱ የሆኑትንም ሁሉ ካወጣ በኋላ ፊት ፊታቸው ይሄዳል፤ በጎቹም ድምፁን ስለሚያውቁ ይከተሉታል።"***

- <u>*መሪነት*</u> ተጽዕኖ ነው
    1. ሌሎችን እርምጃ እንዲወስዱ ወይም ወደ ድርጊት እንዲገቡ ማነሣሣት አለብህ
    2. ተጽዕኖ የመፍጠር አቅም የሚኖርህ መተማመን እና አክብሮትን በመገንባት ነው
    3. መሪነት ሌሎች የአንተን ውሳኔዎች <u>በፈቃደኝነት እንዲከተሉ</u> የማድረግ ችሎታ ነው

- ***ሥልጣን*** *ኃይል ነው*

1. በመዝገበ ቃላት ፍቺው፣ *ሥልጣን እንደዚህ ይገለጻል፡-*
   **"ሐሳብ፣ አስተያየት ወይም ጠባይ ላይ ተጽዕኖ የማድረግ ወይም የማዘዝ ኃይል"**
2. ከእግዚአብሔር የተሰጠህ ነው
   ***"ማንኛውም ሰው በሥልጣን ላሉት ሹማምት መገዛት ይገባዋል፤ ከእግዚአብሔር ካልሆነ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣናት በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው።"***
   **- ሮሜ 13፥1**
3. *ሥልጣን ካለፈው ጊዜ እና ሁኔታ የሚመነጭ እንጂ አሁን በአሁን የሚገኝ አይደለም*

4. *ሥልጣን ውሳኔዎችህን እንዲተገበሩ የማድረግ ችሎታ ነው*

   - *ሥልጣንን መጠቀም ያለብን ለምን ነገሮች ነው?*
     - ለማስተማር
       ***"አንተ ግን ከትክክለኛው ትምህርት ጋር ተስማሚ የሆነውን አስተምር። በሙሉ ሥልጣን ምከር፤ ገሥጽም፤ ማንም አይናቅህ።" – ቲቶ 2፥1 እና 15***

     - ለማገልገል
       ***"በእናንተ ኀላፊነት ሥር ያለውን የእግዚአብሔርን መንጋ ጠብቁ፤ የምትጠብቁትም ከእግዚአብሔር እንደሚጠበቅባችሁ በግድ ሳይሆን በፈቃደኝነት፣ ለጥቅም በመስገብገብ ሳይሆን ለማገልገል ባላችሁ ጽኑ ፍላጎት ይሁን" – 1 ጴጥሮስ 5፥2***

*****ሁልጊዜም በሥልጣን ከመምራት ይልቅ በተጽዕኖ መምራት ተመራጭነት አለው***

- ተጽዕኖህን ስትጠቀም ሰዎች ሊከተሉህ ይፈልጋሉ
- *ሥልጣንህን ስትጠቀም ሰዎች ሊከተሉህ ይገደዳሉ*
  - አብዛኛውን ጊዜ ሰዎችን ከአገልግሎትህ መስከ ልታጣቸው ትችላለህ
  - ተቃዋሚ ትፈጥራለህ

## #2. ***መሪዎች ራዕይ አላቸው***

**ምሳሌ 29፥18 – *"ራእይ በሌለበት ሕዝብ መረን ይሆናል"***

1. *መሪ የት መሄድ እንደሚፈልግ ያውቃል*
2. *ያለ ራዕይ፣ ቤተ ክርስቲያን አቅጣጫ ታጣለች*
   - *ራዕይ ትኩረትን ይሰጣል*
   - *ራዕይ የቤተ ክርስቲያን ዓላማ እና ግቦች ላይ ብዥታ እንዳይኖር ያደርጋል*
3. *ራዕይ የአገልግሎትን ግብ እና ዓላማ በሚሰፈር መለኪያ ለማስቀመጥ ያስችላል*
   - ለማሳካት የሚፈልገውን የመጨረሻ ግቡን ግልጽ ያደርጋል
   - *መሆን የሚሻውን ወይም መድረስ የሚፈልግበትን ስፍራ በግልጽ ያሰፍራል*

     - **የራዕይ ምሳሌዎች**
       1. በ12 ወራት ውስጥ የቤተ ክርስቲያን መገልገያ ስፍራ ገንብቶ ማጠናቀቅ
       2. በኅብረተ ሰቡ ውስጥ ለሚገኙ ድሃ ወገኖች መመገቢያ ስፍራ ማዘጋጀት
       3. በኅብረተ ሰቡ ውስጥ የክርስቲያን ትምህርት ቤት ማቋቋም
       4. 10,000 ሰዎችን በወንጌል መድረስ

4. ራዕይ፣ ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር የታለመላትን ግብ እንድትመታ ያስችላታል

- ከእግዚአብሔር የተሰጠ ራዕይ አብዛኛውን ጊዜ በቀላሉ በራሳችን ልናሳካው የምንችለው አይደለም።
  **ዮሐንስ 15፥5 – "*ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና።*"**

- ለቤተ ክርስቲያን፣ የእግዚአብሔርን ምሪት መፈለግ ወሳኝ ነው።
  ***ማቴዎስ 19፥26 – "ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም፤ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉም ነገር ይቻላል"***

5. ራዕይ ቤተ ክርስቲያንን ያነሣሣል፤ ያበረታታል

- የቤተ ክርስቲያን አባላት የራዕዩ ተጋሪዎች ሲሆኑ በንቃት የመሳተፍ ዕድላቸው ይጨምራል
- የቤተ ክርስቲያን አባላት ራዕዩ ለማሳካት እንዲተጉ ያደርጋቸዋል
- የራዕይ መኖር ሰዎችን የአንድ ትልቅ ነገር አካል እንደሆኑ እንዲሰማቸው ያግዛል

****ማስታወሻ: <u>ራዕይ የተልዕኮ መግለጫ አይደለም</u>**

- የተልዕኮ መግለጫ (በተለምዶ "ተልዕኮ" የሚባለው) የሚናገረው የምታደርገውን ነገር እንጂ የት መድረስ እንደምትፈልግ አይደለም

**<u>ራዕይ እንዴት ይቀረጻል?</u>**

**ደረጃ #1**: ከእግዚአብሔር ምሪት እና መገለጥን ለማግኘት ጸልይ

- በምትገኝበት ማኅበረ ሰብ ብሎም በዓለም ሁሉ እንዴት ሊጠቀምህ እንደሚፈልግ እግዚአብሔርን ጠይቅ
- ምን እንድታደርግለት እንደሚፈልግ እግዚአብሔርን ጠይቀው

**ደረጃ #2:** **በትልቁ** አስብ

- ራስህን ባለህ ነገር አትገድበው
- የሚያስፈልግህን አቅርቦት እንዲያደርግልህ ለእግዚአብሔር ስፍራ ስጥ

**ደረጃ #3:** በራዕይ ቀረጻ ውስጥ ሌሎች መሪዎችን አሳትፍ

**ደረጃ #4:** ራዕዩን በጽሑፍ አስፍረው፤ እንዲሁም ሌሎች አማራጮችን አጢን

- አማራጮቹን ለማሰብ እና በእነርሱ ላይ ለመጸለይ ጊዜ ውሰድ
- አማራጮቹ ላይ ከሌሎች ግብዓትን ጠይቅ

**ደረጃ #5:** ጸልይ እና እግዚአብሔር ለዚያ እንደጠራህ የተሰማህን ራዕይ ምረጥ!

**ደረጃ #6:** ራዕይህን ለሌሎች አጋራ

- ራዕዩ እንዲታወቅ እና ሌሎች ተሳታፊ እንዲሆኑበት፣ መሪዎች ራዕያቸውን ለሌሎች ማጋራት/መግለጽ አለባቸው
- እንደ መሪ፣ ለራዕዩ መሰጠት አለብህ

## #3. *መሪዎች ዕቅድ አላቸው*

**ምሳሌ 16፥3**

***"የምታደርገውን ሁሉ ለእግዚአብሔር ዐደራ ስጥ፤ ዕቅድህም ሁሉ ይሳካልሃል።"***

ሀ. *መሪ፣ እንዴት ራዕዩን እንደሚያሳካ ዕቅድ ያወጣል*

- *ዕቅድ ከሌለህ፣ ራዕዩን የማሳካት ዕድልህ የኮሰሰ ይሆናል*
- *ዕቅድ መኖሩ፣ ያሉህን ግብዓቶች እና የምታደርጋቸውን እንቅስቃሴዎች ራዕዩን ለማሳካት በሚያስችል መልኩ እንድታቀናጅ ያግዝሃል*
- *መሪ ራዕይ ሳይኖረው ሊያቅድ አይችልም*

ለ. *መሪ፣ የእግዚአብሔርን ግብዓቶች ለእግዚአብሔር ራዕይ ማሳኪያ እንዲውሉ ያመቻቻል*

- እግዚአብሔር ለመሪዎች የሚጠቀሙባቸውን ግብዓቶች ይሰጣል
- እግዚአብሔር መሪዎች የእርሱን ግብዓቶች በብልሃት እንዲጠቀሙ ይፈልጋል
- እግዚአብሔር "ኢንቨስት" ላደረጋቸው ግብዓቶች በምላሹ ትርፍ ይፈልጋል

ሐ. የመሪ *ሥራ ሥራውን ማቀድ* እና *ዕቅዱን ሥራ* ላይ *ማዋል* ነው

- *መሪ ሳያሳልስ ዕቅዱን ማዘመን* (ከሁኔታዎች *ጋር* እያስተካከለ *መሄድ*) አለበት
- ጥሩ *ዕቅድ መሪው* የተሻሉ ውሳኔዎችን እንዲወስን *ያግዘዋል*
- ጥሩ *ዕቅድ* የእግዚአብሔር *ግብዓቶች* እንዳይባክኑ ይከላከላል

## #4. *መሪዎች ሰዎችን ያሳድጋሉ*

**ሉቃስ 9፥1-2**

***"ኢየሱስም ዐሥራ ሁለቱን ሐዋርያት በአንድነት ጠርቶ ኢጋንንትን ሁሉ እንዲያወጡ፣ ደዌንም እንዲፈውሱ ኀይልና ሥልጣን ሰጣቸው፤ ደግሞም የእግዚአብሔርን መንግሥት እንዲሰብኩና የታመሙትን እንዲፈውሱ ላካቸው"***

ሀ. *መሪዎች* ከሁሉ አስቀድሞ ደቀ *መዛሙርትን ያፈራሉ* (**ማቴዎስ 28፥19-20**)

- *ቃሉን ያስተምራሉ፤* ይሰብካሉ
- ለተከታዮቻቸው *ቃሉን* እንዲ*ታዘዙ ያስተምራሉ*

ለ. *መሪዎች* ሌሎችን ለአገልግሎት *ያሰለጥናሉ፤ ያስታጥቃሉ*

- የእያንዳንዱን ሰው *መንፈሳዊ* ስጦታዎች ለይተው በማወቅ ጥቅም ላይ *ያውላሉ*
- በአገልግሎት ውስጥ ሌሎች እንዲሳተፉ *ያበረታታሉ*

ሐ. *መሪዎች* ሌሎች *መሪዎችን ይመለምላሉ፤ ያሳድጋሉ*

- ይህንን በማድረግ አገልግሎታቸውን *ያሳድጋሉ*
- ይህንን በማድረግ አገልግሎታቸውን ዘላቂ *ያደርጋሉ*
- የበለጠ ቁጥር *ያላቸው መሪዎች* በኖሩ *መጠን*፣ ስኬትን የመቀዳጀት *ዕድላቸውን ያሳድጋሉ*

## #5. ***<u>መሪዎች ተጨባጭ ውጤት ማምጣት ላይ ያተኩራሉ</u>***

**ሮሜ 14፥12**

***"ስለዚህ እያንዳንዳችን ስለ ራሳችን ለእግዚአብሔር መልስ እንሰጣለን።"***

*ሀ. መሪዎች ግቦችን ማሳካት እና ውጤት ማምጣት ላይ ያተኩራሉ*

- *መሪ ሁልጊዜም ራዕዩ ከሐሳቡ አይርቅም*
- *መሪ ስኬትን የሚለካው በመጡት ውጤቶች ነው*

*ለ. መሪዎች ጥረት እና ግብዓት የሚያፈሱት ከፍተኛ ምላሽ የሚያገኙባቸው መስኮች ላይ ነው*

- *መሪ ግብዓቶችን የሚያፈሰው ከፍተኛ ስኬት ሊቀዳጅ በሚችልበት አቅጣጫ ነው*
- *መሪ ፍሬ አልባ አገልግሎቶችን ይተዋል*

*ሐ. መሪዎችን እንቅስቃሴዎች ወይም ድርጊቶች በራሳቸው ውጤት እንዳልሆኑ ይገነዘባሉ*

- *መሪ አገልግሎቶችን የሚለካው በውጤታማነታቸው ነው*
- *መሪ እንቅስቃሴዎች ወይም ድርጊቶችን የሚለካው ከራዕዩ አንጻር ባሳደሩት ተጽዕኖ ነው*

**ሉቃስ 10፥38-42**

***"ኢየሱስና ደቀ መዛሙርቱ መንገድ ሲሄዱ፣ ኢየሱስ ወደ አንድ መንደር ገባ፤ ማርታ የተባለች አንዲት ሴትም በቤቷ ተቀበለችው። እርሷም ማርያም የተባለች እኅት ነበረቻት፤ ማርያምም ቃሉን እየሰማች በጌታ እግር ሥር ተቀምጣ ነበር። ማርታ ግን በሥራ ብዛት ትባክን ነበርና ወደ እርሱ ቀርባ፣ "ጌታ ሆይ፤ እኅቴ ሥራውን ለእኔ ብቻ ጥላ ስትቀመጥ ዝም ትላለህን? እንድታግዘኝ ንገራት እንጂ" አለችው። ጌታ ግን እንዲህ ሲል መለሰላት፤ 'ማርታ፣ ማርታ፤ ስለ ብዙ ነገር ትጨነቂያለሽ፤ ትዋከቢአለሽም፤ የሚያስፈልገው ግን አንድ ነገር ብቻ ነው፤ ማርያም እኮ የሚሻለውን ድርሻ መርጣለች፤ ይህም ከእርሷ አይወሰድም።'"***

*(ይህ የእግዚአብሔር ቃል፣ ማርታን ያሳሰባት እንቅስቃሴ ማድረጉ ሲሆን፣ ማርያምን ግን ያሳሰባት ውጤት መሆኑን ያሳያል።)*

# ተልዕኮ እና ራዕይ

**1. የተልዕኮ መግለጫህን በጽሑፍ አስፍር**
(እግዚአብሔር ለእርሱ እንድታደርግ የጠራህ ነገር ምንድን ነው?)

**2. የራዕይ መግለጫህን በጽሑፍ አስፍር**
(እግዚአብሔር እንድታሳካው የሚፈልገው የአገልግሎት ግብ ምንድን ነው?)

**የራዕይ መግለጫ፣ ራዕዩ ተሳክቷል ወይስ አልተሳካም የሚለውን መለኪያ መንገድ አብሮ ማካተት አለበት

**ምዕራፍ 2**

# ***<u>መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሪ መሆን</u>***

***"እኔ የወይን ተክል ነኝ፤ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ። ማንም በእኔ ቢኖር እኔም በእርሱ ብኖር፣ እርሱ ብዙ ፍሬ ያፈራል፤ ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና። በእኔ የማይኖር ተጥሎ እንደሚደርቅ ቅርንጫፍ ነው፤ እንዲህ ያሉት ቅርንጫፎች ተለቅመው ወደ እሳት ይጣላሉ፤ ይቃጠላሉም። በእኔ ብትኖሩ ቃሎቼም በእናንተ ቢኖሩ፣ የምትፈልጉትን ማንኛውንም ነገር ለምኑ፤ ይሰጣችኋልም። ብዙ ፍሬ በማፍራት ደቀ መዛሙርቴ መሆናችሁን ብትገልጡ፣ በዚህ አባቴ ይከብራል።"***
**ዮሐንስ 15፥5-8**

መሪ ሌሎችን ሲመራ፣ ሊሻው የሚገባው ምናልባትም ከሁሉም ይልቅ አስፈላጊ የሆነው ነገር መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሆዎችን መከተል ነው፤ ለምን ቢባል ኢየሱስ ሊያስተምረን የመጣው ይህንን ነው። ምንም እንኳ አንዳንዴ ለእኛ ትርጉም የማይሰጥ ቢመስለንም፣ ከራሳችን ይልቅ የእግዚአብሔርን መንገድ መከተል ይበልጥ ውጤታማ አገልግሎት እንዲኖረን ያስችለናል። አስደናቂ የሆነ የመሪነት ችሎታ ቢኖረን እንኳ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ካልተመረኮዝን ተከታዮቻችንን ወደ ተሳሳተ አቅጣጫ ልንመራቸው እንችላለን። በዚህ ምዕራፍ የውጤታማ መሪዎች መገለጫ የሆኑ 10 መጽሐፍ ቅዱሳዊ መለያዎችን እና በዚህ ዘመን መሪዎችን የሚገጥሟቸው ተግዳሮቶችን እናያለን።

## **I. *መግቢያ***

### **የክርስቲያን *መሪ* ግብ ምንድን ነው?**

የተሳታፊ ቁጥር ለመጨመር እና ተሳታፊ ለማብዛት …. **<u>አይደለም</u>**
**<u>ክርስቶች በሌሎች ውስጥ ተስሎ ማየት</u>** …. ነው!
***"የምወዳችሁ ልጆቼ ሆይ፤ ክርስቶስ በውስጣችሁ እስኪቀረጽ ድረስ ስለ እናንተ እንደ ገና ምጥ ይዞኛል"*** (**ገላትያ 4፥19**)

### **ክርስቲያን *መሪ* ክርስቲያን ካልሆነ *መሪ* የሚለየው እንዴት ነው?**

ክርስቲያን መሪ ይህንን ያውቃል — ***"ያለ እግዚአብሔር ምንም ሊያደርግ አይችልም!!"*** (**ዮሐንስ 15፥5**)

**II. *የመሪነት መለያዎች*:-** ውጤታማ መሪ የሚከተሉት 10 መለያዎች ይኖሩታል:-

1. ውጤታማ መሪ **<u>ባለ ራዕይ</u>** መሆን አለበት።
   ***"ራዕይ በሌለበት ሕዝብ መረን ይሆናል"*** **ምሳሌ 29፥18**
   - ግቦች ሊኖሩህ ያስፈልጋል
   - ራዕይህን ሌሎች ሊጋሩት በሚችሉት መልኩ መግለጽ ያስፈልግሃል

ለምሳሌ:- **ሙሴ** (በሚቃጠለው ቁጥቋጦ ከእግዚአብሔር ራዕይን መቀበሉ - ዘፍጥረት 3)

2. ውጤታማ መሪ **<u>ተልዕኮ-ተኮር</u>** መሆን አለበት።
   ***"ደቀ መዛሙርቱንም እንዲህ አላቸው፤ 'መከሩ ብዙ ነው፤ የመከሩ ሠራተኞች ግን ጥቂቶች ናቸው፤ 38ስለዚህ የመከሩ ጌታ፣ ወደ መከሩ ሠራተኞችን እንዲልክ ለምኑት።'"*** **ማቴዎስ 9፥37-38**
   - የማያምኑትን መድረስ ላይ ማተኮርህን አትተው።
   - ሌሎች አማኞችን በደቀ መዝሙርነት ማሳደግ ግድ ይበልሀ።

ለምሳሌ:- **ጳውሎስ** (ብዙ የተልዕኮ ጉዞዎችን ማድረጉ – የሐዋርያት ሥራ)

3. ውጤታማ መሪ **በቅንዓት የተሞላ** መሆን አለበት።
   ***"አሁንም የጀመራችሁትን ተግባር በዐቅማችሁ መጠን ከፍጻሜ አድርሱት፤ ይህም ለመስጠት የነበራችሁ በጎ ፈቃድ እውን እንዲሆን ነው።" 2 ቆሮንቶስ 8፥11***
   - ስለ አገልግሎትህ ጥልቅ በሆነ መልኩ ግድ ሊልህ ይገባል።
   - ስኬት ላይ ለመድረስ መሰጠት ሊኖርህ ይገባል (ቅንዓት = መሰጠት)።

ለምሳሌ፡- **እስጢፋኖስ** (ለዓላማው የተሰጠ መሆኑ - የሐዋርያት ሥራ 7)

4. ውጤታማ መሪ **በመንፈስ የሚመራ** መሆን አለበት።
   ***"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።" የሐዋርያት ሥራ 1፥8***
   - መንፈስ ቅዱስ እንዲመራህ ፍቀድለት።
   - ከኃይልህ ምንጭ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ግንኙነትህን አታቋርጥ!

ለምሳሌ፡- **ዳንኤል** (እምነቱን አለመካዱ – ዳንኤል 6)

5. ውጤታማ መሪ **አገልጋይ** መሆን አለበት።
   ***"በእናንተ መካከል ግን እንዲህ መሆን የለበትም። ከእናንተ ትልቅ መሆን የሚፈልግ አገልጋያችሁ ይሁን፤ የበላይ ለመሆን የሚሻም የእናንተ የበታች ይሁን" ማቴዎስ 20፥26-27***
   - መሪ የተጠራው በተከታዮቹ ለመገልገል ሳይሆን እነርሱን ለማገልገል ነው።
   - አገልጋይ መሪ ተከታዮቹን እንዲያድጉ እና ለስኬት እንዲበቁ ያግዛል።

ለምሳሌ፡- **ኢየሱስ** (የደቀ መዛሙርቱን እግር ማጠቡ – ዮሐንስ 13)

6. ውጤታማ መሪ **ትኩረቱን የሰበሰበ** መሆን አለበት።
   ***"ወንድሞች ሆይ፤ እኔ ገና እንደያዝሁት አድርጌ ራሴን አልቈጥርም፤ ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ ከኋላዬ ያለውን እየረሳሁ ከፊቴ ወዳለው እዘረጋለሁ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ ወደ ላይ ስለ ጠራኝ፣ ሽልማት ለመቀዳጀት ወደ ግቡ እፈጥናለሁ።" ፊልጵስዩስ 3፥13-14***
   - ከራዕይ እና ከተልዕኮህ ጋር ባልተያያዙ ጉዳዮች አትኩሮትህ መከፈል የለበትም።
   - ሰይጣንን እንዲያባዝንህ አትፍቀድለት።

ለምሳሌ፡- **ነህምያ** (ትኩረቱን የኢየሩሳሌሙ መቅደስ መልሶ መገንባት ላይ ማድረጉ – ነህምያ 6)

7. ውጤታማ መሪ **ደፋር** መሆን አለበት።
   ***"ከዚያም ሙሴ ኢያሱን ጠርቶ በእስራኤል ሁሉ ፊት እንዲህ አለው፤ 'እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው ሊሰጥ ወደ ማለላቸው ምድር ከዚህ ሕዝብ ጋር አብረህ ስለምትገባ፣ ምድሪቱን ርስታቸው አድርገህ ስለምታከፋፍል በርታ፤ ደፋርም ሁን። እግዚአብሔር ራሱ በፊትህ ይሄዳል፤ ከአንተም ጋር ይሆናል፤ ፈጽሞ አይለይህም፤ አይተውህምም፤ አትፍራ፤ ተስፋም አትቍረጥ።'" ዘዳግም 31፥7-8***
   - መሪ በእምነት ለመውጣት ፈቃደኛ ነው
   - መሪ የላቀ ስኬትን ለመቀዳጀት ሲል አደጋን ለመጋፈጥ ("ሪስክ ለመውሰድ") ፈቃደኛ ነው
   - እግዚአብሔር ያስታጥቅሃል፤ ብርታትም ይሰጥሃል

ለምሳሌ፡- **ዳዊት** (ከጎልያድ ጋር ያደረገው ግጥሚያ – 1ኛ ሳሙኤል 17)

8. *ውጤታማ መሪ* **<u>በእግዚአብሔር የሚተማመን</u>** *መሆን* አለበት።

***"በፍጹም ልብህ በእግዚአብሔር ታመን፤ በራስህ ማስተዋል አትደገፍ"* ምሳሌ 3፥5**

- *መሪ ታማኝ* እና እውነተኛ በሆነው በእግዚአብሔር *ይታመናል*
- *ሁኔታዎች የማያስኬዱ* በሚመስሉበት ጊዜ *መሪ* በእግዚአብሔር *ይተማመናል*

ለምሳሌ፡- **አብርሃም** (ይስሐቅን ለመስዋዕት ማቅረቡ – ዘፍጥረት 22)

9. *ውጤታማ መሪ* **<u>ዝግጁ</u>** *መሆን* አለበት።

***"ቃሉን ስበክ፤ ጊዜው ቢመችም ባይመችም ዝግጁ ሁን፤ በታላቅ ትዕግሥትና በማስተማር አቅና፤ ገሥጽ፤ አበረታታም።"* 2 ጢሞቴዎስ 4፥2**

- ዝግጁነት *መስዋዕትነት* እና አስቀድሞ *ማቀድን* ይጠይቃል
- ስኬት 1% ተነሳሽነት፣ 99% ዝግጁነት ነው

ለምሳሌ**፡- ዮሴፍ** (ለረሃብ ዘመን *መዘጋጀቱ* – ዘፍጥረት 41)

10. *ውጤታማ መሪ* **<u>ሁኔታዎችን የሚጠቀም</u>** *መሆን* አለበት።

***"በጎ ነገር ከማድረግ አንታክት፤ ተሰፋ ካልቆረጥን ጊዜው ሲደርስ መከሩን እናጭዳለን። ስለዚህ ዕድሉ ካለን ለሰው ሁሉ፣ በተለይም ለእምነት ቤተ ሰቦች መልካም እናድርግ።"***

***ገላትያ* 6፥9-10**

- ዛሬውኑ እግዚአብሔር የሰጠህን *ዕድል* እና *አጋጣሚ* ተጠቅምበት
- *ዕድሎች* እንዳያልፉህ በንቃት ተጠባበቅ

ለምሳሌ፡- **አስቴር** (ሕዝቧን ከጥፋት *መታደጓ* – አስቴር 4)

## II. የመሪነት ተግዳሮቶች

***"በርግጥም በክርስቶስ ኢየሱስ በእውነተኛ መንፈሳዊ ሕይወት መኖር የሚወዱ ሁሉ ይሰደዳሉ።"***
**2 ጢሞቴዎስ 3፥12**

*መሪነት ተግዳሮት የተሞሉ ፈታኝ ገጽታዎች አሉት፡-*

ሀ. የመጨረሻው አናት ላይ ሊኖር የሚችለው አንድ መሪ ብቻ ነው

1. አስተዋይ ሁን
2. ፍትሃዊ ሁን
3. የውሳኔ ሰው ሁን

ለ. ሁልጊዜ፣ ሁሉም ሰው ከአንተ ጋር የሚስማማ አይሆንም

1. ውሳኔዎችህ ተግዳሮት ሊገጥማቸው እንደሚችል ጠብቅ
2. ሰዎች ጉዳዮችን በተለያየ መልኩ ሊያዩዋቸው ይችላሉ
3. ውሳኔህን በምክንያታዊነት እና በቃለ እግዚአብሔር እንጂ በስሜት ለማስረዳት ወይም ለመከላከል አትሞክር

ሐ. ውጊያዎችን አሸንፎ ሙሉውን ጦርነት የመሸነፍ አደጋ አለ

1. የአጭር ጊዜ ግቦችን ለማሳካት ስትጥር ከረጅም ጊዜ ራዕይህ ላይ ዓይንህን አታንሣ
2. ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ነገሮች ቅድሚያ ስጥ
3. ግትር አትሁን፤ ሆኖም መርሆዎችህን ቸል አትበል

# <u>የመሪነት ራስ-ምዘና</u>

| | |
|---|---|
| ***መመሪያ፡-*** | በተከታዩ መለኪያ መሠረት ለራስህ በእያንዳንዱ መለያ ላይ ነጥብ ስጥ፡- |
| **1=ከስንት አንዴ** | **2=አልፎ አልፎ  3=በተደጋጋሚ  4=በአብዛኛው  5=ሁልጊዜ** |

***<u>መለያ</u>*** **<u>ነጥብ</u>**

1. ባለ ራዕይ ______
2. ተልዕኮ-ተኮር ______
3. በቅንዓት የተሞላ ______
4. በመንፈስ የሚመራ ______
5. አገልጋይ ______
6. ትኩረቱ የተሰበሰበ ______
7. ደፋር ______
8. በእግዚአብሔር የሚተማመን______
9. ዝግጁ ______
10. ሁኔታዎችን የሚጠቀም ______

ድምር ______

| <u>**ድምር ነጥብ**</u> | <u>**ትርጉም**</u> |
|---|---|
| 40+ | ጠንካራ የሆኑ የመሪነት ክህሎቶች አሉህ። እግዚአብሔር በሚገባ ሊጠቀምብህ ይችላል! |
| 30-39 | አንዳንድ የመሪነት ችሎታዎች አሉህ፤ ሆኖም ልትሻሻል የምትችልበት ክፍተት አለ። |
| 20-29 | አልፎ አልፎ የመሪነት ክህሎት ብታሳይም፣ በበርካታ አቅጣጫዎች የመሪነት ክህሎቶችህን ማዳበር ያስፈልግሃል። |
| 10-19 | የመሪነት ክህሎቶችህ ደካማ ናቸው። ሥልጠና እና ማሻሻያ በሚገባ ያስፈልግሃል። |
| 0-9 | ምንም ዓይነት የመሪነት ችሎታ አይታይብህም። ሁነኛ ሥልጠና ውሰድ፤ አሊያም አቅጣጫህን ቀይር። |

**ምዕራፍ 3**

# የአመራር ዘይቤዎች

***"አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹ ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው፤ ይኸውም የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት [ነው]"***

**ኤፌሶን 4፥11-12**

እግዚአብሔር እያንዳንዱን መሪ የጠራው እንደየ ችሎታው የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት እንዲተጋ እንዲያዘጋጅ እና የክርስቶስን አካል እንዲገነባ ነው። እያንዳንዱ መሪ ***እንዴት*** ይምራ የሚለው ግን፣ የግል ዘይቤ እና እያንዳንዱ ሰው የሚመቸው አካሄድ ጉዳይ ነው። እንደ መሪ የምንመራው፣ የምናስተዳድረው፣ የምንሠራው የግል ሰብዕናችንን፣ ስጦታችንን እና ልምዳችንን በሚስማማ መልኩ ነው። የአመራር መንገዳችን በአንዳንድ ሁኔታዎች እጅግ ውጤታማ፣ በሌሎች ሁኔታዎች ደግሞ ውጤት የማያስገኝ ሆኖ ሊገኝ ይችላል። ስለሆነም የራሳችንንም ሆነ የሌሎችን የአመራር ዘይቤ መገንዘብ በተለያዩ ሁኔታዎች ውስጥ የመሪነት ችሎታችንን ውጤታማ በሆነ መልኩ እንድንጠቀም ያግዘናል። በዚህ ምዕራፍ 4ቱን መሠረታዊ የአመራር ዘይቤዎች፣ እንዲሁም እነዚህን የአመራር ዘይቤዎች እንዴት ከፍተኛ ውጤት ለማስመዝገብ ልንጠቀማቸው እንደምንችል እናያለን።

## I. የአመራር ዘይቤዎች ምንድን ናቸው?

- 4 የአመራር ዘይቤዎች አሉ (ጆርጅ በርማ በጻፉት *"**ከውሃ የወጣ አሳ**"* በሚለው መጽሐፍ መሠረት - ***"A Fish Out Of Water"***; Integrity Publishers, 2002)

  1. **አዛዥ** *መሪ*
     - የዚህ ዓይነቱ መሪ አብዛኛውን ጊዜ ባለ ራዕይ ሰው ነው
     - የዚህ ዓይነቱ መሪ ከዝርዝር ጉዳዮች ይልቅ ውጤቶች ላይ ያተኩራል

  2. **ስልታዊ** *መሪ*
     - የዚህ ዓይነቱ መሪ መረጃን መተንተን እንዲሁም ይህ ወይም ያ ቢሆን እያለ የተለያዩ አማራጮችን ማመዛዘን ይወዳል
     - የዚህ ዓይነቱ መሪ ለራዕዩ ዕቅድ ማውጣት እና ዕቅዱን መልክ ማስያዝ ይወዳል

  3. **ቡድን ገንቢ** *መሪ*
     - የዚህ ዓይነቱ መሪ ከተግባር ይልቅ በሰዎች መካከል ያሉ ግንኙነቶች እና መስተጋብሮች ያሳስቡታል
     - የዚህ ዓይነቱ መሪ ራዕዩን ለማሳካት ሰዎችን ማደራጀት ይወዳል

  4. **ክዋኔ ተኮር** *መሪ*
     - የዚህ ዓይነቱ መሪ ራዕዩን ለማስፈጸም ሂደቶችን የሚቀርጽ እና የሚያዳብር ነው
     - የዚህ ዓይነቱ መሪ ሥርዓቶችን መገንባት እና አፈጻጸሞችን መከታተል ይወዳል

## II. የአመራር ዘይቤህን ለይተህ ማወቅ

### <u>የአመራር ዘይቤህ የቱ ነው?</u>

ከዚህ በታች የመሪነት ሁኔታን የሚገልጹ ዐረፍተ ነገሮች ተዘርዝረዋል። እያንዳንዳቸውን በጥንቃቄ አንብብ። በመቀጠል ከታች በተመለከተው መስፈርት መሠረት እያንዳንዱ ዐረፍተ ነገር የአንተን የአመራር ሁኔታ ምን ያህል እንደሚገልጸው ለይተህ አስቀምጥ። ትክክለኛውን ውጤት ለማግኘት፣ በተቻለህ መጠን እውነተኛ መልስ ስጥ።

| ፈጽሞ | ከስንት አንዴ | አልፎ አልፎ | በተደጋጋሚ | በአብዛኛው | ሁልጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| **0** | **1** | **2** | **3** | **4** | **5** |


1. ________ የምመራው ቡድን በውሳኔ አሰጣጥ ውስጥ እንዲሳተፍ አበረታታለሁ፤ የሚያቀርቡትን ሐሳብም ተግባር ላይ ለማዋል እጥራለሁ።
2. ________ አንድን ግብ ወይም ተግባር ከማሳካት ይበልጥ አስፈላጊ ነገር የለም።
3. ________ ሰዎችን ማክበር ወይም ለሰዎች ዋጋ መስጠት ከሁሉ በላይ ቅድሚያ የምሰጠው ነገር ነው።
4. ________ አንድ ተግባር ወይም ሥራ በጊዜው መጠናቀቁን ለማረጋገጥ በቅርበት እከታተላለሁ።
5. ________ አዳዲስ ተግባሮች እና የአሠራር ዘዴዎችን እንዲለምዱ ሰዎችን ማሠልጠን ደስ ይለኛል።
6. ________ አንድ ተግባር ይበልጥ ፈታኝ በሆነ መጠን፣ ይበልጥ ያስደስተኛል።
7. ________ ሰዎች ሥራቸውን የራሳቸውን ፈጠራ አክለውበት እንዲሠሩ አበረታታለሁ።
8. ________ አንድን ውስብስብ ሥራ ከፍጻሜ በማድረስ ሂደት ውስጥ፣ እያንዳንዷን ዝርዝር ጉዳይ እከታተላለሁ።
9. ________ ሥልጠና፣ አመራር እና ሥነ ልቦና ላይ የተጻፉ መጣጥፎችን፣ መጻሕፍትን፣ የጥናት ውጤቶችን ማንበብ፣ ያነበብኩትንም በተግባር መሞከር ያስደስተኛል።
10. ________ በርካታ ውስብስብ ተግባራትን በአንድ ጊዜ ማከናወን አይከብደኝም።
11. ________ የሌሎችን ስህተት ሳርማቸው፣ ከእነርሱ ጋር ያለኝን ግንኙነት እያሻከርኩ እንዳይሆን ብዬ እሰጋለሁ።
12. ________ ጊዜዬን በሚገባ ከፋፍዬ መጠቀም አውቅበታለሁ።
13. ________ የውስብስብ ሥራ ወይም ፕሮጀክትን ዝርዝር ነገሮች እና ጥልፍልፎችን ለምመራቸው ሰዎች ማብራራት ያስደስተኛል።
14. ________ ትላልቅ ፕሮጀክቶችን ሊተገበሩ ወደሚችሉ ድርጊቶች መበታተን ተፈጥሮዬ የሆነ ያህል ይስማማኛል።
15. ________ ድንቅ የሆነ ቡድን ከመገንባት ይበልጥ አስፈላጊ ነገር የለም።
16. ________ ችግሮችን በታትኖ መተንተን ያስደስተኛል።
17. ________ የሌሎች ሰዎችን ወሰኖች አከብራለሁ።
18. ________ አገልግሎት ላይ የተጻፉ መጣጥፎች እና መጻሕፍትን ማንበብ፣ እንዲሁም የተማርኳቸውን አዳዲስ ዘዴዎች ተግባር ላይ ማዋል እወዳለሁ።
19. ________ የአፈጻጸም ችሎታቸውን ወይም ባህሪያቸውን እንዲያዳብሩ ለማድረግ ሌሎችን ማማከር ተፈጥሮዬ የሆነ ያህል ይስማማኛል።
20. ________ የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ማደራጀት እና ማቀድ ያስደስተኛል።

**ነጥብ ማስፈሪያ ክፍል**
መጠይቁን ከሞላህ በኋላ፣ መልሶችህን ከሥር በተመለከተው ቦታ ላይ ሙላ፡-

| **ሰዎች** | **ተግባር** |
|---|---|
| **ጥያቄ** | **ጥያቄ** |
| 1.________ | 2.________ |
| 3.________ | 4.________ |
| 5.________ | 6.________ |
| 7.________ | 8.________ |
| 9.________ | 10.________ |
| 11.________ | 12.________ |
| 13.________ | 14.________ |
| 15.________ | 16.________ |
| 17.________ | 18.________ |
| 19.________ | 20.________ |
| **ድምር**__________ | **ድምር**__________ |
| (ድምሩን በ10 አካፍለህ፣ ከዚያ በሁለት አካፍል) | (ድምሩን በ10 አካፍለህ፣ ከዚያ በሁለት አካፍል) |
| **ነጥብ**: ___________ | **ነጥብ**: ___________ |

## የውጤት ክፍል

የመጨረሻ ነጥብህን ከታች ያለው ግራፍ ላይ አመልክት። “ሰዎች” በሚለው ላይ ያገኘኸውን ነጥብ ከቁም መስመሩ ትይዩ፣ “ተግባር” በሚለው ላይ ያገኘኸውን ነጥብ ከአግድም መስመሩ ትይዩ አመልክት። ከዚያም ከሁለቱ ምልክቶች የሚነሡ አንድ የቁም፣ አንድ ደግሞ አግድም መስመር በማስመር ሁለቱ መስመሮች እንዲገናኙ አድርግ። በሁለቱ መስመሮች ውስጥ የሚገኘው ስፍራ፣ መሪነትህን ሥራ ላይ የምታውልበት ይዞታ ነው።




### III. የአመራር ዘይቤዎችን ሥራ ላይ ማዋል

1. ጆርጅ ባርና እንደሚሉት፣ እያንዳንዱ መሪ በዋናነት ከእነዚህ ዘይቤዎች ወደ አንዱ ያመዝናል። ይሁን እንጂ ሁሉም መሪዎች የሁሉም የአመራር ዘይቤዎች አንዳንድ ገጽታዎች ይኖሯቸዋል።

2. ዙሪያህን ከአንተ የተለየ የአመራር ዘይቤ ባላቸው ሰዎች ከበብ።
   - የአንተን ክፍተት ያካክሱልሃል
   - ነገሮችን አንተ ካላየሃቸው አቅጣጫ ያያሉ

   ***“ምክር ሲጓደል ዕቅድ ይፋለሳል፤ በብዙ አማካሪዎች ግን ይሳካል።”***
   **- ምሳሌ 15፥22**

3. ከጠንካራ ጎንህ እንጂ፣ ከደካማ ጎንህ ተነሥተህ አትምራ።
   ***“እንደ ተሰጠን ጸጋ የተለያዩ ስጦታዎች አሉን፤ ለአንዱ የተሰጠው ስጦታ ትንቢት መናገር ከሆነ፣ እንደ እምነቱ መጠን ይናገር። ማገልገል ቢሆን ያገልግል፤ ማስተማርም ከሆነ ያስተምር፤ መምከር ከሆነ ይምከር፤ ለሌላቸው መለገስ ከሆነም አብዝቶ ይለግስ፤ ማስተዳደር ከሆነም በትጋት ያስተዳድር፤ ምሕረት ማድረግ ከሆነም በደስታ ይማር።” – ሮሜ 12፥6-8***

4. እንደየ ሁኔታው አስፈላጊ የሆነ የአመራር ሁኔታ መጠቀም እንደሚያስፈልግ ተረዳ።

   - አንተ የምታመዝንበት የአመራር ዘይቤ **በሁሉም** ሁኔታዎች ውስጥ ውጤታማ አይሆንም።

   - ለእያንዳንዱ የተለይ ሁኔታ የትኛው የአመራር ዘይቤ ይበልጥ ውጤታማ እንደሚሆን ለይተህ እወቅ።
     ለምሳሌ፡-
     1. ለአገልግሎትህ (ለሚኒስትሪህ) አዲስ አቅጣጫ ለመቀየስ – **አዛዥ መሪነት (*ተግባር* በሚያስፈልግበት)**
     2. ለአገልግሎትህ ዕቅዶችን ለማውጣት – **ስልታዊ መሪነት (*ምዘና እና ማቀድ* በሚያስፈልግበት)**
     3. በአገልግሎትህ ውስጥ አለመግባባቶችን ለመፍታት – **ቡድን ገንቢ መሪነት (*ከሰዎች ጋር መሥራት* በሚያስፈልግበት)**
     4. ቴክኖሎጂን በአገልግሎትህ ውስጥ ለመጠቀም – **ከዋኔ ተኮር መሪነት (*ሥርዓቶች ወይም ሂደቶች* በሚያስፈልጉበት)**
   - በቡድንህ ውስጥ የሚገኝ ከአንተ የተለየ የአመራር ዘይቤ ያለውን ሌላ መሪ እንዲመራ ዕድል ለመስጠት ፈቃደኛ ሁን።
     - የመጨረሻ ወሳኝነቱን አንተው እንደያዝክ ቆይ
     - የፕሮጀክት ወይም የአንድ ተግባር መሪነትን ሥራ በቡድንህ ውስጥ ለሚገኝ ሌላ መሪ አስተላልፍ

5. ሁኔታው የሚጠይቀውን ዓይነት የአመራር ዘይቤ አለመጠቀም መዘዝ ያስከትላል
   - መሪነትህ ተግዳሮት ሊገጥመው ይችላል
   - ተዓማኒነትህን ልታጣ ትችላለህ
   - አላስፈላጊ አለመግባባት ልትፈጥር ትችላለህ
   - አገልግሎቱ ባለበት የመቆም ወይም የመጎዳት አደጋ ሊያጋጥመው ይችላል

# የአመራር ዘይቤዎች መልመጃ

*መመሪያ፡-* በግራ በኩል ለተመለከተው እያንዳንዱ ሁኔታ፣ ጥቅም ላይ መዋል ያለበትን ወይም የነበረበትን ተገቢ የሆነውን የአመራር ዘይቤ ጻፍ።
(አዛዥ፣ ስልታዊ፣ ቡድን ገንቢ፣ ከዋኔ ተኮር)

| ***ሁኔታ*** | ***ጥቅም ላይ መዋል ያለበት የአመራር ዘይቤ*** |
|---|---|
| 1. ለቤተ ክርስቲያን ሥራ ኮምፒዩተር ተሰጥቶሃል፤ እንዴት ጥቅም ላይ እንደምታውለው መወሰን አለብህ | |
| 2. ማረሚያ ቤት ያሉ ወገኖችን የሚደርስ አገልግሎት ልትጀምር ነው፤ ሆኖም ይህ አገልግሎት ከሌሎቹ አገልግሎት ዘርፎች ግብዓቶችን እንዲወስድ አትፈልግም | |
| 3. የአምልኮ ቡድንህ አባላት የአምልኮ መሪው ላይ ስሞታ ይዘው ወደ አንተ መጥተዋል | |
| 4. ባለህበት ማኅበረ ሰብ ውስጥ በወንጌል የመድረስ ሥራዎችን ይበልጥ መሥራት ትፈልጋለህ፤ ሆኖም እንዴት አድርገህ ተግባር ላይ እንደምታውለው እርግጠኛ አይደለህም | |
| 5. የቤተ ክርስቲያንህን መገኛ የከተማው ሌላ ሰፈር ወዳለ ሰፋ ያለ ቦታ ማዛወር ትፈልጋለህ | |
| 6. አንዳንድ ሰዎች አምልኮ አገልግሎቱ ላይ ቅሬታ አቅርበዋል፤ አንዳንድ ነገሮች እንዲለወጡም ይፈልጋሉ | |
| 7. የልጆች አገልግሎትህ ግቦቹን ማሳካት እየተሳነው ነው፤ የተሳታፊ ቁጥርም መቀነስ ይዟል | |
| 8. ሰዎች ከአንተ ቤተ ክርስቲያን እየለቀቁ በቅርብ ያለ ሌላ ቤተ ክርስቲያንን እየተቀላቀሉ ነው | |
| 9. ከተማ ውስጥ የሚገኝ ሌላ ቤተ ክርስቲያን የአንተን ቤተ ክርስቲያን መሰብሰቢያ አዳራሽ ለራሳቸው ፕሮግራም ለመጠቀም ጠይቀዋል | |
| 10. ቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሃሜት ችግር አለ | |

**ምዕራፍ 4**

## *<u>መሪዎችን ማፍራት/ማሳደግ</u>*

***"ስለዚህም እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤ 'መንፈስ ቅዱስ ያደረበትን የነዌን ልጅ ኢያሱን ወስደህ እጅህን ጫንበት። በካህኑ በአልዓዛርና በመላው ማኅበር ፊት እንዲቆም አድርገው፤ በፊታቸውም ሹመው፤ 20መላው የእስራኤል ማኅበረሰብ እንዲታዘዝለትም ከሥልጣንህ ከፍለህ ስጠው።'"***
**ዘኁልቁ 27፥18-20**

ከቤተ ክርስቲያን ወይም ከአገልግሎት መሪነት ጋር ተያይዞ ጌታ እንንሠራ የጠራንን የአገልግሎት ሥራ ከዳር የማድረስ ከፍተኛ ኃላፊነት አለብን። አብዛኛውን ጊዜ አመራራችን ውጤታማ እንዲሆን፣ በእያንዳንዱ የአገልግሎታችን ጉዳዮች ውስጥ መሳተፍ ያለብን ይመስለናል። እውነታው ግን እንዲህ ማድረግ የማንችል መሆኑ ነው። እያንዳንዱን ስብሰባ መምራት፣ እያንዳንዱን ዝርዝር ጉዳይ መከታተል፣ ወይም እያንዳንዱን ውሳኔ እኛው መወሰን አንችልም። መሪዎች እንደ መሆናችን፣ ግባችንን ማሳካት ከፈለግን የሌሎችን ድጋፍ እና ችሎታ ማካተት ይኖርብናል። ልክ ሙሴ እጁን በኢያሱ ላይ እንደጫነ፣ አንተም "በመንፈስ" የሆኑ መሪዎችን ለይተህ ማወቅ፣ እንዲሁም በአንተ ፈንታ ሆነው በአንተ ሥልጣን እንዲሠሩ ማሰማራት ይኖርብሃል። በዚህ ምዕራፍ መሪ ማን እንደ ሆነ፣ መሪዎችን ማፍራት እና ማሳደግ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ፣ እንዲሁም መሪዎችን እንዴት ለይቶ ማወቅ እና ማሳደግ እንደሚቻል እናያለን።

### I. *መሪ ማነው?*

***መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለን፣ መሪ …***

1. በክርስቶስ ያለውን ማንነት ያውቃል (**2 ቆሮንቶስ 5፥15-21**)
    a. ሁላችንም የክርስቶስ አገልጋዮች መሆናችንን ያውቃል (**1 ጴጥሮስ 2፥9**)
    b. ክርስቶስ በኃይሉ አስታጥቆናል (**ኤፌሶን 1፥18-20 ፤ 3፥14-20**)
    c. ሁላችንም በእኩል ደረጃ ለአካሉ ዋጋ አለን (**1 ቆሮንቶስ 12፥27**)

2. መንፈሳዊ ስጦታዎችን ይገነዘባል
    a. ጌታ ለሁሉም ሰው መንፈሳዊ ስጦታን ሰጥቷል (**1 ቆሮንቶስ 12፥7**)
    b. ሁላችንም የተሰጡንን ስጦታዎች ጥቅም ላይ እንድናውል ተጠርተናል (**ኤፌሶን 4፥11-13**)
    c. መሪ፣ ሌሎች ሰዎች ስጦታዎቻቸውን ጥቅም ላይ እንዲያውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት (**2 ጢሞቴዎስ 2፥2**)

3. መሪ ሥራው ጨው እና ብርሃን መሆን እንደሆነ ይገነዘባል (**ማቴዎስ 5፥13-16**)
    a. ባለንበት ባሕል ውስጥ ተጽዕኖ ፈጣሪ መሆን አለብን (**ቆላስይስ 4፥5-6**)
    b. ለሌሎች አርዓያ ነን (**1 ተሰሎንቄ 1፥7**)
    c. እንደራሴዎች ነን (**2 ቆሮንቶስ 5፥20**)

4. መሪ ወንጌልን ለማሰራጨት (**የሐዋርያት ሥራ 1፥8**) እና ለክርስቶስ ደቀ መዛሙርትን ለማፍራት (**ማቴዎስ 28፥19**) የተሰጠ ነው

## II. ***ሌሎች መሪዎችን ማፍራት/ማሳደግ ያን ያህል አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?***

1. የእግዚአብሔር መንግሥት የሚሰፋበት መንገድ ስለሆነ

- ኢየሱስ የመባዛትን አገልግሎት በደቀ መዛሙርቱ በኩል አስተምሯል
    - ኢየሱስ የእርሱን ቤተ ክርስቲያን በምድር ላይ የሚገነቡ መሪዎችን ራሱ መርጧል
    - ኢየሱስ ሁሉንም በደቀ መዝሙርነት ቀርጿቸዋል፤ አስታጥቋቸዋል
    - ***"ሕዝቦችን ሁሉ … ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው"*** ብሏቸዋል – **ማቴዎስ 28፥19**

- ኢየሱስ ሌሎችን ሳያሳትፍ ቤተ ክርስቲያንን ራሱ በራሱ አልገነባም
  ***"አብ እኔን እንደ ላከኝ፣ እኔም እናንተን እልካችኋለሁ"*** **- ዮሐንስ 20፥21**
    - ጳውሎስ የወንጌል ተልዕኮ ጉዞዎችን አድርጓል
    - ሌሎች ደቀ መዛሙርት እና የጌታ ተከታዮች አብያተ ክርስቲያናትን ተክለዋል

- ቤተ ክርስቲያን አንድ አካል እንደ መሆኗ፣ ሁሉም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚጫወተው ሚና አለ
  ***"እንግዲህ እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ፤ ኢያንዳንዳችሁም የአካሉ ብልቶች ናችሁ።"***
  **- 1 ቆሮንቶስ 12፥27**

2. አገልግሎትህን ያባዛል

- አገልግሎትህ በበለጠ ብዙዎችን እንዲደርስ ያስችላል
    - አገልግሎትህ የብዙዎችን ሕይወት ሊነካ ይችላል
    - አገልግሎትህ የበለጠ ርቀት ሊጓዝ ይችላል

- በአነስተኛ ጥረት እና ጊዜ የበለጠ ውጤት እንድታስመዘግብ ያግዝሃል
    - ሁሉም ስፍራ ልትገኝ አትችልም
    - ሁልጊዜ ሁሉንም ነገር አንተው ልታደርገው አትችልም
    ***"እኛ የማእዱን አገልግሎት ለማስተናገድ ስንል የእግዚአብሔርን ቃል አገልግሎት መተው አይገባንም።"*** **- የሐዋርያት ሥራ 6፥2**

- ልታያቸው ወይም ልትጠቀማቸው አትችል የነበሩ ሌሎች ዕድሎች ይከፍትልሃል
    - ሌሎች መሪዎች ዘንድ ሌሎች የሚያካፍሏቸው ስጦታዎች አሉ
    - ሌሎች መሪዎች ዘንድ ሌሎች ቅንዓቶች እና ፍላጎቶች አሉ

3. በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ መንፈስ ቅዱስ እንዲሠራ ያስችላል

- መንፈስ ቅዱስ በመጋቢዎች ብቻ ሳይሆን ***በሁሉም*** ሰዎች በኩል ይሠራል
    - አማኞች ***ሁላችን*** ካህናት ነን
      ***"አይሁድ ወይም የግሪክ ሰዎች ብንሆን፣ ባሪያ ወይም ነጻ ሰዎች ብንሆን፣ እኛ ሁላችን አንድ አካል እንድንሆን በአንድ መንፈስ ተጠምቀናልና፤ ሁላችንም አንዱን መንፈስ እንድንጠጣ ተሰጥቶናል።"***
      **–1 ቆሮንቶስ 12፥13**

    - መንፈስ ቅዱስ ***ለሁሉም*** አማኞች ኃይል ይሰጣል
      ***"ገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ"***
      **- የሐዋርያት ሥራ 1፥8**

4. የአገልግሎት ስኬት የሚወሰነው በአመራር እና በመንፈስ ቅዱስ ነው

- ጠንካራ አመራር የሌለው አገልግሎት ስኬታማ ሊሆን አይችልም
  - ጥሩ መሪዎች ደካማ አገልግሎቶችን ሊያነቃቁ ይችላሉ
  - ጥሩ ያልሆኑ መሪዎች ስኬታማ አገልግሎቶችን ሊያበላሹ ይችላሉ

- መንፈስ ቅዱስ የኃይል ምንጫችን ***ነው***
  - እኛ ዘሩን ተካዮች ብቻ ነን
    ***"ስለዚህ የሚያሳድግ እግዚአብሔር እንጂ፣ የሚተክልም ሆነ ውሃ የሚያጠጣ ምንም አይደለም።"*** **- 1 ቆሮንቶስ 3፥7**

  - ኃይላችን የሚመጣው ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ነው
    ***"ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና።"*** **– ዮሐንስ 15፥5**

## IV. ሌሎች መሪዎችን ለይተህ ማወቅ የምትችለው እንዴት ነው?

1. የጠንካራ መሪዎች መመዘኛዎች
   - የባሕሪ ሰዎች (መልካም ባሕሪ የተላበሱ)
     ***"እንግዲህ የቤተ ክርስቲያን ኤጲስቆጶስ የማይነቀፍ፣ የአንዲት ሚስት ባል፣ ልከኛ፣ ራሱን የሚገዛ፣ በሥርዐት የሚኖር፣ እንግዳ ተቀባይ፣ ማስተማር የሚችል፣ የማይሰክር፣ የማይጣላ ግን ጨዋ የሆነ፣ የማይጨቃጨቅ፣ ገንዘብንም የማይወድ ሊሆን ይገባዋል።"***
     **- 1 ጢሞቴዎስ 3፥2-3**

   - የእምነት ሰዎች
     ***"በትዕቢት ተነፍቶ ዲያብሎስ በወደቀበት ፍርድ እንዳይወድቅ አዲስ ክርስቲያን አይሁን።"*** **– 1 ጢሞቴዎስ 3፥6**

     ***"የእምነትንም ጥልቅ ምስጢር በንጹሕ ኅሊና መጠበቅ አለባቸው።"*** **– 1 ጢሞቴዎስ 3፥9**

   - በመንፈስ የተሞሉ ሰዎች
     ***"ስለዚህ ወንድሞች ሆይ፤ ከእናንተ መካከል በመንፈስ ቅዱስና በጥበብ የተሞሉ ለመሆናቸው የተመሰከረላቸውን ሰባት ሰዎች ምረጡ፤ ይህን ኀላፊነት ለእነርሱ እንሰጣለን፤ "*** **- የሐዋርያት ሥራ 6፥3**

2. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያልተጠቀሱ (ሆኖም በብዛት ጥቅም ላይ የሚውሉ) የመሪዎች መመዘኛዎች
   - የትምህርት ደረጃ
   - ማኅበራዊ አቋም
   - ልምድ

   **** እነዚህ ጥሩ ነገሮች ቢሆኑም፣ ዋና መመዘኛዎች መሆን <u>የለባቸውም</u>**

3. መሪዎችን መምረጥ
   - ቅንዓት ያላቸውን ሰዎች ምረጥ
   - ሥልጠና አግኝተው ለመሻሻል ክፍት የሆኑ ሰዎች ምረጥ
   - አስፈላጊ ወይም ተገቢ የሆኑ መንፈሳዊ ስጦታዎች ያሏቸውን ሰዎች ምረጥ

## V. ሌሎች መሪዎችን እንዴት ልታፈራ/ልታሳድግ ትችላለህ? (ማቴዎስ ምዕራፍ 10ን ለማመሳከሪያ ተመልከት)

**ደረጃ #1:** **በደቀ መዝሙርነት አሳድጋቸው**

- ሳምንታዊ በግል የማማከር ጊዜ (ሳምንታዊ "ሜንተሪንግ")
- የማበረታቻ ቃላት እና ተግባራት
- እምነት መገንባት
- ዝግጅት (የመሪነት ሥልጠና)

**ደረጃ #2:** **ኃላፊነት ስጣቸው (ማቴዎስ 10፥1)**

- የሚመሩት ወይም የሚያስተዳድሩት ነገር ስጣቸው
- አንድን ሥራ ከዳር እንዲያደርሱ የሚያስፈልጋቸውን ሥልጣን ስጣቸው
- በራስ መተማመናቸውን ገንባ

**ደረጃ #3:** **ከእነርሱ ምን እንደምትጠብቅ አስረዳቸው (ማቴዎስ 10፥6-8 ፣ 16)**

- ግልጽ የሆኑ ግቦችን አስቀምጥ እና የመሪነት ዕቅድ እንዲያዘጋጁ አግዛቸው
- መለኪያ መስፈርቶች ወይም መመሪያዎች አስቀምጥ

**ደረጃ #4:** **በኃላፊነት ጠይቃቸው (ማቴዎስ 10፥32-33)**

- የተቀመጡ ዓላማዎችን ማሳካታቸውን ተከታተል
- ችግሮች ካጋጠሟቸው ጣልቃ ገብተህ ችግሮቹን ከመፍታት ይልቅ፣ ራሳቸው እንዲፈቷቸው ተዋቸው
  - እንደ አስፈላጊነቱ ምክር ለግስ
  - ራሳቸው መፍትሔ እንዲያመጡ ተዋቸው

**ደረጃ #5:** **የደረሱበትን ደረጃ በየጊዜው መዝን**

- ያጋጠሟቸውን ጉዳዮች እና ያሳሰቧቸውን ነገሮች ለመወያየት በተደጋጋሚ አግኛቸው
- እንዲሁ በራሳቸው አትተዋቸው ወይም ቸል አትበላቸው
- እንዲማሩ እና ስኬታማ እንዲሆኑ ለማገዝ ፍላጎት እንዳለህ አሳይ

**ደረጃ #6:** **ለአገልግሎት ልቀቃቸው**

- ጊዜያቸው ሲደርስ ልቀቃቸው - ይዘህ አታቆያቸው
- የሚመሩት አገልግሎት ስጣቸው
- ለአገልግሎት ሥራ ላካቸው

# መሪዎችን የማፍራት/የማሳደግ መልመጃ

ከእያንዳንዱ የአገልግሎት አመራር ኃላፊነት ትይዩ፣ ለዚያ ኃላፊነት ያስፈልጋሉ ብለህ የምታስባቸውን መንፈሳዊ ስጦታዎች እና ሊያግዙ ይችላሉ የምትላቸውን ክህሎቶች ወይም ልምዶች አስፍር።

| **የአገልግሎት አመራር ኃላፊነት** | **መንፈሳዊ ስጦታ**** | **ክህሎት/ልምድ** |
|---|---|---|
| 1. መጋቢ | | |
| 2. የአምልኮ መሪ | | |
| 3. የልጆች አገልግሎት መሪ | | |
| 4. የወጣቶች አገልግሎት መሪ | | |
| 5. ሽማግሌ | | |
| 6. አስተማሪ | | |
| 7. ወንጌላዊ | | |
| 8. የተልዕኮ አገልጋይ (ሚሽነሪ) | | |
| 9. የፋይናንስ አስተዳዳሪ | | |
| 10. የጸሎት አገልግሎት መሪ | | |

** ገጽ 39-40 ላይ የተጠቀሱትን መንፈሳዊ ስጦታዎች ለማመሳከሪያ ተጠቀም

# ክፍል 2

# ሰዎችን ማስተዳደር



**ምዕራፍ 5**

## <u>መንፈሳዊ ስጦታዎች</u>

***"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ሊጋራ ጥቅም ነው። … እነዚህ ሁሉ የዚያው የአንዱ መንፈስ ስጦታዎች ሲሆኑ፣ ለእያንዳንዱ ሰው እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ ይሰጠዋል።"***
**1 ቆሮንቶስ 12፥7 ፣ 11**

መጽሐፍ ቅዱስ የክርስቶስን አካል ለማነጽ እንዲጠቅም እያንዳንዱ ክርስቲያን መንፈሳዊ ስጦታ እንደተሰጠው ይናገራል። የሆነ ሆኖ፣ መንፈሳዊ ስጦታዎች ምንድናቸው? ከክህሎቶቻችን እና ከተፈጥሯዊ ችሎታዎቻችን ጋር አንድ ናቸው ወይስ ይለያሉ? ያሉንን መንፈሳዊ ስጦታዎች ልናውቅ የምንችለው እንዴት ነው? መቼ እና እንዴት እንደምንጠቀማቸው የምናውቀው እንዴት ነው? እነዚህ ጥያቄዎች ብዙ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያን ወይም በክርስቶስ አካል ውስጥ ያላቸውን ሚና አስመልክቶ የሚያነሷቸው ናቸው። እንደ መሪ የራስህን ብቻ ሳይሆን የሌሎችንም ስጦታ ማወቅ አስፈላጊ ነው። የሌሎችን ስጦታ ማወቅህ እግዚአብሔር ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ ሊጠቀማቸው በሚችል አቅጣጫ እንድትመራቸው ያስችልሃል። በዚህ ምዕራፍ መንፈሳዊ ስጦታዎች ምን እንደሆኑ፣ ለምን አስፈላጊ እንደሆኑ፣ እንዲሁም ለመንግሥቱ መስፋት እንዴት ጥቅም ላይ ሊውሉ እንደሚችሉ እናያለን። በተጨማሪም መንፈሳዊ ስጦታዎችህ ምን እንደሆኑ ለመለየት የሚያግዝ መመዘኛ መሣሪያ እንጠቀማለን።

### I. *መንፈሳዊ ስጦታዎች ምንድን ናቸው?*

- መንፈሳዊ ስጦታዎች ማለት መንፈስ ቅዱስ የክርስቶስ ተከታዮችን ለአገልግሎት ለማስታጠቅ የሚሰጣቸው ችሎታዎች ናቸው።
  1. እነዚህ ስጦታዎች ሊጋራ ጥቅም የሚሰጡ ናቸው
     ***"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ሊጋራ ጥቅም ነው።"***
     **- 1 ቆሮንቶስ 12፥7**

  2. እነዚህ ስጦታዎች የሚሰጡት መንፈስ ቅዱስ እንደ ወሰነው ነው
     ***"እነዚህ ሁሉ የዚያው የአንዱ መንፈስ ስጦታዎች ሲሆኑ፣ ለእያንዳንዱ ሰው እርሱ ራሱ እንደ ፈቀደ ይሰጠዋል።"* - 1 ቆሮንቶስ 12፥11**

  3. እነዚህ ስጦታዎች የሚሰጡት እንደ አስፈላጊነቱ ነው

- መንፈሳዊ ስጦታዎች በ 3 ዋና ዋና መደቦች ይከፈላሉ
  1. **<u>የአገልግሎት</u>** ስጦታዎች – ብዙውን ጊዜ የአንድ አገልግሎት ድርሻ ጥሪ
  2. **<u>ተግባራዊ</u>** ስጦታዎች – ሌሎችን ለማገልገል
  3. **<u>አነቃቂ</u>** ስጦታዎች – መንፈሳዊ መገለጦች እና ኃይሎች

- መጽሐፍ ቅዱስ 21 ተለይተው የተገለጹ ስጦታዎችን ይዘረዝራል
  1. **አገልግሎት**
     - ሐዋርያ፣ ነቢይ፣ ወንጌላዊ፣ መጋቢ/እረኛ፣ አስተማሪ
       ***"አንዳንዶቹ ሐዋርያት፣ አንዳንዶቹ ነቢያት፣ አንዳንዶቹም ወንጌል ሰባኪዎች፣ ሌሎቹ ደግሞ እረኞችና አስተማሪዎች ይሆኑ ዘንድ የሰጠ እርሱ ነው"***
       **- ኤፌሶን 4፥11**

2. **ተግባራዊ**

- ማገልገል፣ መምከር/ማበረታታት፣ መስጠት፣ መምራት፣ መማር፣ መርዳት፣ ማስተዳደር
***"ማገልገል ቢሆን ያገልግል፤ ማስተማርም ከሆነ ያስተምር፤ መምከር ከሆነ ይምከር፤ ለሌላቸው መለገስ ከሆነም አብዝቶ ይለግስ፤ ማስተዳደር ከሆነም በትጋት ያስተዳድር፤ ምሕረት ማድረግ ከሆነም በደስታ ይማር።"***
**- ሮሜ 12፥7-8**

***"እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አንደኛ ሐዋርያትን፣ ሁለተኛ ነቢያትን፣ ሦስተኛ መምህራንን፣ ቀጥሎም ታምራት አድራጊዎችን፣ የመፈወስ ስጦታዎች ያላቸውን፣ ሌሎችን የመርዳት ስጦታ ያላቸውን፣ የማስተዳደር ስጦታ ያላቸውንና በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር ስጦታ ያላቸውን ሰዎች መድቦአል።"***
**- 1 ቆሮንቶስ 12፥28**

3. **አነቃቂ**

- ጥበብ፣ እውቀት፣ መለየት፣ ትንቢት፣ በልሳን መናገር፣ መተርጎም፣ እምነት፣ ፈውስ፣ ተአምራት
***"ለአንዱ በመንፈስ የጥበብን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው መንፈስ የዕውቀትን ቃል መናገር ይሰጠዋል፤ ለአንዱ በዚያው መንፈስ እምነት ይሰጠዋል፤ ለሌላው ደግሞ በዚያው በአንዱ መንፈስ የመፈወስ ስጦታዎች ይሰጠዋል፤ ለአንዱ ታምራትን የማድረግ፣ ለሌላው ትንቢትን የመናገር፣ ለሌላው ደግሞ መናፍስትን የመለየት፣ ለአንዱ በልዩ ልዩ ልሳን የመናገር፣ ለሌላው ደግሞ በልዩ ልዩ ልሳን የተነገረውን የመተርጎም ስጦታ ይሰጠዋል።"*** **- 1 ቆሮንቶስ 12፥8-10**

**በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሱ ሌሎች መንፈሳዊ ስጦታዎች ይገኛሉ፤ ሆኖም እነዚህ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልጽ የተቀመጡ ናቸው።

## II. *መንፈሳዊ ስጦታዎች ለምን አስፈላጊ ሆኑ?*

- እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ያለውን ዓላማ እና ዕቅድ ለማሳካት
***"የሰላም አምላክ፣ ፈቃዱን እንድታደርጉ በመልካም ነገር ሁሉ ያስታጥቃችሁ"***
**- ዕብራውያን 13፥20-21**

- የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት
***"ይኸውም የክርስቶስ አካል ይገነባ ዘንድ፣ ቅዱሳንን ለአገልግሎት ሥራ ለማዘጋጀት"*** **- ኤፌሶን 4፥12**

- መንፈሳዊ ብስለት ላይ ለመድረስ
***"ሁላችንም … በክርስቶስ ወዳለው ፍጹምነት ደረጃ እስከምንደርስ ነው።"*** **– ኤፌሶን 4፥13**

- የክርስቶስን አካል አንድ ለማድረግ
***"እንግዲህ እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ፤ እያንዳንዳችሁም የአካሉ ብልቶች ናችሁ።"***
**- 1 ቆሮንቶስ 12፥27**

## III. *መንፈሳዊ ስጦታዎች ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው እንዴት እና በምን መልኩ ነው?*

- ቤተ ክርስቲያንን ለማነጽ
***"መንፈሳዊ ስጦታዎችን ለማግኘት የምትሹ በመሆናችሁ፣ ቤተ ክርስቲያን የምትታነጽበትን ስጦታዎች ለማግኘት ይበልጥ ፈልጉ።"*** **1 ቆሮንቶስ 14፥12**

- ሌሎችን ለማገልገል
  ***“እንደ ታማኝ የእግዚአብሔር ልዩ ልዩ ጸጋ መጋቢ እያንዳንዱ ሰው በተቀበለው የጸጋ ስጦታ ሌላውን ያገልግል” - 1 ጴጥሮስ 4፥10***

- እግዚአብሔርን ለማክበር
  ***“ከእናንተ ማንም የሚናገር ቢኖር እንደ እግዚአብሔር ቃል ይናገር፤ የሚያገለግልም ቢኖር እግዚአብሔር በሚሰጠው ብርታት ያገልግል፤ ይኸውም እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ አማካይነት እንዲከበር ነው” - 1 ጴጥሮስ 4፥11***

- የእግዚአብሔርን ባሕርይ ለመግለጥ
  ***“የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትዕግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ ታማኝነት፣ 23 ገርነት፣ ራስን መግዛት ነው።” - ገላትያ 5፥22***

  **<u>ጳውሎስ መንፈሳዊ ስጦታዎችን በተመለከተ 2 ማሳሰቢያዎችን ይሰጣል፡-</u>**

- ቸል ሊባሉ አይገባም
  ***“ሽማግሌዎች እጃቸውን በአንተ ላይ ሲጭኑ በትንቢት የተሰጠህን የጸጋ ስጦታቸል አትበል።”***
  **- 1 ጢሞቴዎስ 4፥14**

- ሥነ ስርዓት በጠበቀ መልኩ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው
  ***“ነገር ግን ሁሉም በአግባብና በሥርዐት ይሁን።”***
  **- 1 ቆሮንቶስ 14፥40**

## IV. የመንፈሳዊ ስጦታ ምዘና

- ይህ ምዘና ምንድን ነው?
  - ጥያቄዎችን እና የምርጫ መልሶችን የያዘ ስጦታችንን ፈልጎ ማግኛ መሣሪያ ነው
  - የአንድን ሰው መንፈሳዊ ስጦታዎች ማወቂያ መሣሪያ ነው
  - ሰዎች በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን ሚና ለይተው እንዲያውቁ የሚረዳ አጋዥ ነው

- ይህ ምዘና ምን አይደለም?
  - የማያዳግም መለያ አይደለም። ስጦታዎች በጊዜ ሂደት ሊለዋወጡ ይችላሉ
  - የአንድን ሰው አገልግሎት ይህ ብቻ ነው ብሎ ለመገደብ ፈጽሞ ጥቅም ላይ መዋል የለበትም። እንደ አስፈላጊነቱ ስጦታዎች ከእግዚአብሔር ሊሰጡ ይችላሉ

## **የመንፈሳዊ ስጦታዎች ምዘና**

http://www.kodachrome.org/spiritgift

እግዚአብሔር ሁሉንም ሰው **በመንፈሳዊ ስጦታ(ዎች)** ባርኳል። እግዚአብሔር የሰጠህን ***መንፈሳዎ ስጦታ(ዎች)*** ለይተህ ታውቃለህ? ያሉኝ ***መንፈሳዊ ስጦታዎች*** ምን ይሆኑ የሚል ጥያቄ ካለህ፣ ይህ ምዘና ምን እንደሆኑ ለማሳየት ሊረዳህ ይችላል።

ይህ ***የመንፈሳዊ ስጦታዎች ምዘና*** ነው። በውስጡ 110 ***ዐረፍተ ነገሮች*** የያዘ ሲሆን፣ እያንዳንዱ ዐረፍተ ነገር ለሚገልጸው ነገር ከሚከተሉት መልሶች አንዱን መልስ፡**- ሁልጊዜ፣ በአብዛኛው፣ በተደጋጋሚ፣ አልፎ አልፎ፣ ከስንት አንዴ** ወይም ***ፈጽሞ***።

ይህ ምዘና የተዘጋጀው በሰዎች እንጂ በእግዚአብሔር ስላይደለ፣ እንከን የለሽ አለመሆኑ አያጠያይቅም። ***መንፈሳዊ ስጦታዎችህን*** ለማወቅ እንደ መነሻ የሚያገለግል እንጂ እቅጩን የሚናገር ጠቋሚ አይደለም። ምዘናው ሁልጊዜም እውነተኛ ***መንፈሳዊ ስጦታዎችህን*** ላያመላክት ይችላል። እግዚአብሔር ሌሎችን እንድትባርክበት፣ በምን እንደባረከህ እያወቅክ የምትሄድበት የሕይወት ዘመን ፍለጋን የሚያግዝ አንድ ተጨማሪ መሣሪያ ነው።

_ለሁሉም_ ***ዐረፍተ ነገሮች*** ምላሽህን ለማስፈር በቂ ጊዜ ሊኖርህ ይገባል፤ እንዲያ ካልሆነ ትርጉም ያለው ውጤት ልታገኝበት አትችልም።

ለእያንዳንዱ ***ዐረፍተ ነገር*** ቀድሞ ወደ አእምሮህ የመጣውን መልስ ስጥ፤ ከዚያም በመልስህ መሠረት የሚከተሉትን ነጥቦች ስጥ፡-

| | |
|---|---|
| ***ሁልጊዜ*** | **= 5** |
| **በአብዛኛው** | **= 4** |
| ***በተደጋጋሚ*** | **= 3** |
| **አልፎ አልፎ** | **= 2** |
| **ከስንት አንዴ** | **= 1** |
| ***ፈጽሞ*** | **= 0** |

እንጀምር፡-

1) _______***ሰዎች ብዙም ሳያንገራግሩ የእኔን መሪነት ለመከተል ፈቃደኛ ይሆናሉ።***
2) _______***ለሌሎች ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ እፈልጋለሁ።***
3) _______***እግዚአብሔር ያለውን የድነት ዕቅድ በቤተ ክርስቲያን ጥላ ሥር ላልታቀፉ ሰዎች ማወጅ ደስታዬ ነው።***
4) _______***ሌሎች ሰዎችን በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የመምራት ኃላፊነት ደስ የሚያሰኝ ነው።***
5) _______***ሰዎች በቃለ እግዚአብሔር ውስጥ ያሉ አስፈላጊ እውነቶችን እንዲያውቁ መርዳት ያስደስተኛል።***
6) _______***ለብቻዬም ሆነ ከሌሎች ጋር አብሬ የእግዚአብሔርን ምስጋና መዘመር የተለየ ደስታ ይሰጠኛል።***

7) _______***ሰዎችን ለላቀ መንፈሳዊ መሰጠት ማነሣሣት ያስደስተኛል።***
8) _______***መንፈሳዊ ጉዳይ ላይ ችግር የገጠማቸው ሰዎች ምክር ፍለጋ ወደ እኔ ይመጣሉ።***
9) _______***ትምህርት ቤት እያለሁ ከፍተኛ ውጤት አገኝ ነበር።***
10) _______***በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ትናንሽ ሥራዎችን በመሥራት ከፍተኛ ደስታ አገኛለሁ።***
11) _______***ሰዎችን በሥራቸው ለማገዝ የማገኛቸውን ዕድሎች እጠቀማለሁ።***
12) _______***ሰዎች የቡድን ግባቸውን እንዲያሳኩ በመምራት ከፍተኛ ደስታ አገኛለሁ።***
13) _______***ለበለጠ ውጤታማ አገልግሎት ሰዎችን ማስተባበር ያስደስተኛል።***
14) _______***ለጌታ ሥራ ከፍተኛ ገንዘብ መስጠት ትልቅ እርካታ ይሰጠኛል።***

15) _______ሌሎች የሚገጥሟቸውን ችግሮች ሳይ ትልቅ የርኅራኄ ስሜት ይሰማኛል።
16) _______አንድ ሰው ሃቀኛ ይሁን አይሁን መለየት ይቀለኛል።
17) _______በእግዚአብሔር ስለምተማመን አይቻልም የሚባለውን ነገር ለመሞከር ዝግጁ ነኝ።
18) _______ሰዎችን በቤቴ ተቀብዬ ማስተናገድ ትልቅ ደስታ ይሰጠኛል።
19) _______በአካባቢዬ ያሉ ነገሮችን መጠገን እና ማደስ ይቀለኛል።
20) _______ከሌሎች ይበልጥ ሰዎች ያሏቸውን የጸሎት ጥያቄዎች አስቀድሜ የማወቅ አዝማሚያ አለኝ።
21) _______ለታመመ ሰው ከሕመሙ እንዲድን በራሴም ሆነ አብሬው የመጸለይ ዕድል ያስደስተኛል።
22) _______ከራሴ የተለየ ባሕል ውስጥ ስገኝ ለመቀላቀል አልቸገርም።
23) _______ከቡድኔ ጋር ባለኝ ግንኙነት የሥልጣን/ኃላፊነት ስሜት ይሰማኛል።
24) _______ሌሎችን ለማጽናናት የእግዚአብሔርን ቃል ማወጅ እወዳለሁ።
25) _______መንፈስ ቅዱስ አንድን ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኙ እንዲቀበል ልቡን ያዘጋጀው ሲሆን አይቼ የመለየት ችሎታ ያለኝ ይመስለኛል።
26) _______ለጉባዔ መንፈሳዊ አመራርን መስጠት ያስደስተኛል።
27) _______የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መስጠት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እጅግ ከሚያስደስቱኝ (ወይም ባደርገው እጅግ ሊያስደስቱኝ ከሚችሉ) ነገሮች አንዱ ነው።
28) _______እግዚአብሔር የሙዚቃ መሣሪያ የመጫወት ችሎታን አድሎኛል፤ ይህም ደስ የምሰኝበት ነገር ነው።
29) _______ተስፋ ለቆረጡ ሰዎች ተስፋቸውን ማደስ ልዩ ደስታ ይሰጠኛል።

30) _______በሕይወት ውስጥ ለሚያጋጥሙ ፈታኝ ችግሮች መፍትሔ መስጠት ያስደስተኛል።
31) _______አስቸጋሪ የሚባሉ እውነቶችን መማር ይቀለኛል።
32) _______ለእግዚአብሔር ክብር የዘወትር ሥራዎችን መሥራት ያስደስተኛል።
33) _______በቤተ ክርስቲያን አካባቢ ድንገተኛ የሚባሉ ሥራዎች ላይ ማገዝ ያስደስተኛል።
34) _______አንድን አስፈላጊ የሚባል ሥራ በማከናወን ሂደት ሰዎች እኔን ተከትለው መሥራት ደስ የሚላቸው ይመስለኛል።
35) _______ዋነኛ የሚባሉ ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ማስተላለፍ ደስ የሚያሰኘኝ ነገር ነው።
36) _______ከማገኘው ገንዘብ ከፍተኛ የሚባል መጠን ለጌታ መስጠት እውነተኛ ደስታ ይሰጠኛል።
37) _______በአረጋውያን መኖሪያ ያሉ አረጋውያንን መጎብኘት ትልቅ እርካታ ይሰጠኛል።
38) _______አንድ ነገር ልክ ይሁን ስህተት በፍጥነት የማወቅ ችሎታ ያለኝ ይመስለኛል።
39) _______ነገሮች የማይቻሉ በሚመስሉበት ጊዜ፣ ወደ ፊት ለመግፋት ዝግጁ ነኝ።
40) _______ሰዎች ቀድመው ሳይነግሩኝ በድንገት ወደ እኔ ሲመጡ ምቾት አይነሡኝም።
41) _______ልዩ ልዩ ዓይነት የሥነ ጥበብ እና የእጅ ሥራ ውጤቶችን መሥራት ያስደስተኛል።
42) _______ጸሎት እጅግ ከምወዳቸው መንፈሳዊ ልምምዶች አንዱ እና ዋነኛው ነው።
43) _______ስሜታዊ ቁስለት ላጋጠመው ሰው ጸልዬ ሲሻለው አይቻለሁ።
44) _______አዲስ ማኅበረ ሰብ ውስጥ መቀላቀል እና አዳዲስ ወዳጆች ማፍራት ይቀለኛል።
45) _______ሰዎችን እግዚአብሔር ወደሚፈልጋቸው ቦታ መምራት እምባዛም አያስፈራኝም።
46) _______የእግዚአብሔርን ቃል ለጊዜው በሚሆን መልኩ መናገር እና ከዘመኑ ጋር ማዛመድ ያስደስተኛል።
47) _______ወንጌልን ለሰዎች የማድረስ ሸክም ይሰማኛል።
48) _______ሰዎችን በመንፈሳዊ ችግሮቻቸው ማገዝ እወዳለሁ።
49) _______በማስተምርበት ጊዜ ሰዎች የምለውን በደንብ የሚማሩ ይመስለኛል።
50) _______በቤተ ክርስቲያን፣ በትምህርት ቤት ወይም በአቅራቢያዬ ባለ ከሙዚቃ/መዝሙር ጋር ተያያዥ ጉዳዮች መሳተፍ ያስደስተኛል።
51) _______ንቁ ተሳታፊ ያልሆኑ የቤተ ክርስቲያን አባሎችን በንቃት እንዲሳተፉ ማበረታታት እወዳለሁ።
52) _______በአጠቃላይ ሰዎች ምክሬን የሚሰሙ ይመስለኛል።
53) _______ከእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ለመረዳት አስቸጋሪ የሚባሉ ክፍሎች ለእኔ ይገቡኛል።
54) _______በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ትናንሽ ወይም ተራ የሚባሉ ድርጊቶችን ማከናወን ትልቅ እርካታ ይሰጠኛል።
55) _______ሌሎችን ለጠቃሚ አገልግሎት ነጻ ለማድረግ የሚያስችሉ ተግባሮችን የማከናወን ፍላጎት አለኝ።

56) _______አንድን ተግባር ራሴ ከማከናወን ይልቅ ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት ይበልጥ ውጤታማ ነው።
57) _______የቡድን ግቦችን ለማሳካት ኃላፊነቱን መሸከም ያስደስተኛል።
58) _______አንድን ወሳኝ ሁነት በገንዘብ የመደገፍ ዕድልን በደስታ እቀበላለሁ።
59) _______በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ ያሉ ሰዎችን ማጽናናት ደስታ ይሰጠኛል።
60) _______በእውነት እና በስህተት መካከል ያለውን ልዩነት በቀላሉ ነቅሼ ማውጣት እችላለሁ።
61) _______በአብዛኛው ሌሎች የማይቻል በመሰላቸው ጊዜ ውስጥ እግዚአብሔር መርቶ ያሳልፈናል ብዬ ለማመን ዝግጁ ነኝ።

62) _______ሰዎች በቤቴ ሲሆኑ ቤተኝነት የሚሰማቸው ይመስለኛል።
63) _______ነገሮችን በእጄ መፍጠር/መሥራት እወዳለሁ።
64) _______እግዚአብሔር ዘወትር ጸሎቶቼን ተጨባጭ በሆነ መንገድ ይመልስልኛል።
65) _______የታመመ ሰው ልጠይቅ ሄጄ እግዚአብሔር እንዲፈውሰው ጸልዬ፣ ያ ሰው ተሽሎት ያውቃል።
66) _______በልዩ ልዩ ስፍራዎች እና ባሕሎች ውስጥ ካሉ ክርስቲያኖች ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት መፍጠር አውቅበታለሁ።
67) _______የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ማወጅን እንደ ትልቅ ዕድል እቆጥረዋለሁ።
68) _______ለዛሬው ዓለም የእግዚአብሔርን የማስጠንቀቂያ እና የፍርድ ቃል መናገሬ ወሳኝ ሆኖ ይታየኛል።
69) _______በቤተ ክርስቲያን ላልታቀፈ ባልንጀራዬ ኢየሱስ ለእኔ ምን ማለት እንደሆነ ማካፈል ከፍተኛ ደስታ ይሰጠኛል።
70) _______ሰዎች ግድ እንደሚለኝ ስለሚሰማቸው ያሉባቸውን ችግሮች እና የሚያሳስቧቸውን ጉዳዮች ያዋዩኛል።

71) _______አንዱ የሚያስደስተኝ የአገልግሎቴ አካል ሰዎች የበለጠ ውጤታማ ክርስቲያኖች እንዲሆኑ ማሰልጠን ነው።
72) _______የሙዚቃ/መዝሙር ችሎታዬ የማገኛቸውን ሰዎች ሊጠቅም እንደሚችል እተማመናለሁ።
73) _______ግራ የተጋቡ ሰዎች ብዙ ጊዜ ማበረታቻ እና ማጽናኛ ፍለጋ ወደ እኔ ይመጣሉ።
74) _______አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥም የተሻለውን አማራጭ ለይቶ የማወቅ የተለየ ዕይታ እንዳለኝ ይሰማኛል።
75) _______መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮዎች ጥርት ብለው ይገቡኛል።
76) _______አንድን ሥራ የሚሠራ ሌላ ሰው ከመፈለግ ይልቅ ራሴ ስሠራው ይበልጥ ያረካኛል።
77) _______የሌሎችን ሸክም በመጋራት የማገዝ አገልግሎት ደስ ይለኛል።
78) _______ሌሎች በቤተ ክርስቲያን ሥራ ይበልጥ እንዲሳተፉ ማነሣሣት እጅግ ያስደስተኛል።
79) _______ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ውጤታማ ዕቅዶችን መንደፍ ከፍተኛ እርካታ ይሰጠኛል።
80) _______ለጌታ የምችለውን ያህል ገንዘብ መስጠት እጅግ ያስደስተኛል።
81) _______ታሞ ሆስፒታል የተኛ ሰው ማገልገል ያስደስተኛል።

82) _______ሥነ መለኮታዊ የሆነ ጉዳይ ላይ እውነቱን ከስሕተቱ በሚገባ መለየት እችላለሁ።
83) _______ሰዎች እኔን ሲያስቡኝ ሁሉም ነገር ይቻላል ብዬ የማስብ እመስላቸዋለሁ ብዬ አስባለሁ።
84) _______የወንጌል መልዕክተኞች (ሚሽነሪዎች) ወደ እኛ ቤተ ክርስቲያን ሲመጡ፣ ቤቴ ቢመጡ ደስ ይለኛል።
85) _______ከልዩ ልዩ የእግዚአብሔር ፍጥረቶች ጋር ያለኝ መስተጋብር፣ ሌሎች ሰዎች ከሚታያቸው በበለጠ ነገሮችን እንዳሻሽል እና እንዳስውብ ያግዘኛል።
86) _______የሰዎች ውጤታማነት እና ሙሉ ደኅንነት እግዚአብሔር ጸሎትን በመመለሱ ላይ እንደሚመረኮዝ ስለምረዳ፣ በታማኝነት ለሌሎች እጸልያለሁ።
87) _______አካላዊም ሆነ ስሜታዊ ሕመም ያለባቸውን ማገልገል እና እንዲፈወሱ መጸለይ እወዳለሁ።
88) _______አዲስ ማኅበረ ሰብ ውስጥ ሄዶ አዲስ ቤተ ክርስቲያን የመትከል ሃሳብ ያስደስተኛል።
89) _______በጉባዔ/በማኅበር ውስጥ የሚያገለግሉ ሠራተኞችን ማሰልጠን ደስ ይለኛል።
90) _______የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት በሚሰጥበት ክፍለ ጊዜ፣ አንዳንዴ ሌሎችን ቢያበሳጫቸውም እንኳን የእግዚአብሔርን ቃል ማካፈል ወሳኝ እንደሆነ አምናለሁ።
91) _______ባለሁበት ማኅበረ ሰብ ውስጥ ላሉ በወንጌል ያልተደረሱ ሰዎች ከፍተኛ ሸክም ይሰማኛል።
92) _______ከሰዎች ጋር አንድ ለአንድ በምገናኝበት ጊዜ ቅርብ የሆነ ግንኙነት እፈጥራለሁ።
93) _______የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ለማስተማር የሚሆን ዝግጅት ማድረግ ቀላል ነው።

94) _______ሌሎች እግዚአብሔርን በደስታ በዝማሬ እንዲያመሰግኑ መምራት የግል እርካታ ይሰጠኛል።
95) _______በቤተ ክርስቲያን ካልታቀፈ ቤተ ሰብ ጋር ኅብረት ከማድረግ፣ በቤተ ክርስቲያን የታቀፈ ግን ትጉ ያልሆነ ቤተሰብ ጋር ኅብረት ባደርግ እመርጣለሁ።

96) _______ለችግሮች በምሰጠው መፍትሔ ፍቱንነት ላይ ብርቱ በራስ መተማመን አለኝ።
97) _______አስቸጋሪ የሚባል የመጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ እና ማጥናት ያስደስተኛል።

98) _______ነገሮችን ብዙም ትኩረት ወደ እኔ ሳልስብ መሥራት እወዳለሁ።
99) _______አንድ ቤተ ሰብ አንዳች ቀውስ ውስጥ ሲገባ፣ የመርዳት ዕድል በማግኘቴ ደስ ይለኛል።
100) _______ሌሎች አንድን ሥራ እኔን ተከትለው ሲሠሩ ከፍተኛ እርካታ አገኛለሁ።
101) _______የምመራውን ቡድን አባላት አንዳች ውሳኔ ላይ እንዲደርሱ ከማግባባት ይልቅ፣ በራሴው ለቡድኑ መወሰን ይቀለኛል።
102) _______እግዚአብሔር የሚያስፈልገኝን ነገር እንደሚያሟላልኝ ስለማውቅ መስዋዕትነት እየከፈልኩ ለሌሎች መስጠት እችላለሁ።

103) _______ከቤታቸው መውጣት የማይችሉ ሰዎችን መጎብኘት ልዩ እርካታ ይሰጠኛል።
104) _______አብዛኛውን ጊዜ አንድ ሰው ከሚናገረው ነገር በስተጀርባ መነሻው ወይም ዓላማው ምን እንደሆነ ለማወቅ እሞክራለሁ።
105) _______ሰዎች ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ሲሰማቸው የሚያነቃቃ እይታ መስጠት ደስ ይለኛል።

106) _______ሰዎች ቤቴ መምጣት ደስ የሚላቸው ይመስለኛል።
107) _______የተለያዩ ነገሮችን መሳል፣ ዲዛይን ማድረግ የመሳሰሉ ድርጊቶች ደስታን ይሰጡኛል።
108) _______ምናልባት ሌላ ነገር ማድረግ ባለብኝ ሰዓት፣ ራሴን ስጸልይ አገኘዋለሁ።

109) _______ለታመመ ሰው ስጸልይ፣ ጸሎቴ ያንን ሰው በሙላት እንደሚያገኘው በብርቱ ይሰማኛል።
110) _______ከብዙዎች በበለጠ፣ ሌሎች ማኅበረ ሰቦች እና አገሮች ሁሉ በጌታ ተጠቅልለው የማየት ብርቱ መሻት አለኝ።

*************************************************************************

እንኳን ደስ አለህ፤ **የመንፈሳዊ ስጦታዎች ምዘናን** አጠናቀሃል!

እባክህን ለደቂቃ ያህል **መልስ ሳትሰጥ የዘለልከው አለመኖሩን** አጣራ።

አሁን፣ **መልሶችህን** አንድ በአንድ **የምዘና ሠንጠረዥ** ላይ ሙላ። ይህንን ለማድረግ ለእያንዳንዱ ጥያቄ የሰጠኸውን **መልስ** መመልከት ይኖርብሃል።

ለእያንዳንዱ 110 **ጥያቄዎች፣ የምዘና ሠንጠረዡ** ላይ ተያያዥ የሆነው ሣጥን ውስጥ ያገኘኸውን ቁጥር ሙላ። በመቀጠል፣ በአግድም ያገኘሃቸውን ቁጥሮች በመደመር **ድምር** ሣጥን ውስጥ አስፍር። በመቀጠል አጠር ያለ ምሳሌ ቀርቧል፦

| ጥ# | መልስ | ጥ# | መልስ | ጥ# | መልስ | ጥ# | መልስ | ጥ# | መልስ | ድምር | ደረጃ | መንፈሳዊ ስጦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 1 | 23 | 3 | 45 | 0 | 67 | 1 | 89 | 3 | 8 | 2 | ሐዋርያ |
| 2 | 3 | 24 | 1 | 46 | 1 | 68 | 0 | 90 | 1 | 6 | 3 | ነቢይ |
| 3 | 3 | 25 | 5 | 47 | 3 | 69 | 5 | 91 | 1 | 17 | 1 | ወንጌላዊ |

አሁን፣ **ድምሮቹን** ተመልከት። ከፍተኛው **ድምር** ዋነኛው የአንተ **መንፈሳዊ ስጦታ** የመሆን ዕድሉ ከፍተኛ ነው። አንዳንድ ሰዎች ተመሳሳይ **ድምር** ያላቸው በርካታ **መንፈሳዊ ስጦታዎች** ይኖሯቸዋል። ይህ ምዘና እንከን የለሽ አይደለም፤ በመሆኑም ከሁሉም ዋነኛው የሆነው የአንተ **መንፈሳዊ ስጦታ** ምናልባት ከፍተኛ **ድምር** ያገኘህበት ላይሆን ይችላል። በመጨረሻ፣ **የመንፈሳዊ ስጦታዎች ዝርዝር** ከመጽሐፍ ቅዱስ ማጣቀሻ ጋር ታገኛለህ።

ይህንን የመንፈሳዊ ስጦታዎች ምዘና (Spiritual Gifts Test)
በእንግሊዝኛው በሚከተለው ድረ ገጽ ማግኘት ይቻላል፦
http://www.kodachrome.org/spiritgift

# የመንፈሳዊ ስጦታዎች ምዘና ሠንጠረዥ

ምዘናውን ሞልተህ ሳትጨርስ በፊት ይህንን ገጽ አትመልከት

| ጥ# | መልስ | ጥ# | መልስ | ጥ# | መልስ | ጥ# | መልስ | ጥ# | መልስ | ድምር | ደረጃ | መንፈሳዊ ስጦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | | 23 | | 45 | | 67 | | 89 | | | | ሐዋርያ |
| 2 | | 24 | | 46 | | 68 | | 90 | | | | ነቢይ |
| 3 | | 25 | | 47 | | 69 | | 91 | | | | ወንጌላዊ |
| 4 | | 26 | | 48 | | 70 | | 92 | | | | መጋቢ |
| 5 | | 27 | | 49 | | 71 | | 93 | | | | አስተማሪ |
| 6 | | 28 | | 50 | | 72 | | 94 | | | | መዝሙር |
| 7 | | 29 | | 51 | | 73 | | 95 | | | | ምክር |
| 8 | | 30 | | 52 | | 74 | | 96 | | | | ጥበብ |
| 9 | | 31 | | 53 | | 75 | | 97 | | | | እውቀት |
| 10 | | 32 | | 54 | | 76 | | 98 | | | | አገልግሎት |
| 11 | | 33 | | 55 | | 77 | | 99 | | | | እርዳታ |
| 12 | | 34 | | 56 | | 78 | | 100 | | | | መምራት |
| 13 | | 35 | | 57 | | 79 | | 101 | | | | ማስተዳደር |
| 14 | | 36 | | 58 | | 80 | | 102 | | | | መስጠት |
| 15 | | 37 | | 59 | | 81 | | 103 | | | | ርኅራኄ |
| 16 | | 38 | | 60 | | 82 | | 104 | | | | መለየት |
| 17 | | 39 | | 61 | | 83 | | 105 | | | | እምነት |
| 18 | | 40 | | 62 | | 84 | | 106 | | | | እንግዶችን መቀበል |
| 19 | | 41 | | 63 | | 85 | | 107 | | | | የእጅ ሙያ |
| 20 | | 42 | | 64 | | 86 | | 108 | | | | መማለድ |
| 21 | | 43 | | 65 | | 87 | | 109 | | | | ፈውስ |
| 22 | | 44 | | 66 | | 88 | | 110 | | | | የወንጌል ተልዕኮ |

# የመንፈሳዊ ስጦታዎች ዝርዝር

**ሐዋርያ**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች እውነተኛውን አስተምህሮ በማወጅ እና በማስተማር የእግዚአብሔርን ቤተ ክርስቲያን እንዲመሩ፣ እንዲያነሣሡ እና እንዲያሳድጉ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ስጦታ ነው። የሐዋርያት ሥራ 12፥1-5 ፣ የሐዋርያት ሥራ 14፥21-23 ተመልከት።

**ነቢይ**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች ለጊዜው ሁኔታ የእግዚአብሔርን መገለጥ እንዲተረጉሙ እና ተግባር ላይ እንዲያውሉ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። 1 ቆሮንቶስ 14፥1-5 ፣ 1 ቆሮንቶስ 14፥30-33 ፣ 1 ቆሮንቶስ 14፥37 ተመልከት።

**ወንጌላዊ**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች ለማያምኑ ሰዎች ወንጌልን በማካፈል ሰዎች የጌታ ኢየሱስ ደቀ መዝሙር ወደ መሆን እንዲመጡ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። የሐዋርያት ሥራ 8፥26-40 ተመልከት።

**መጋቢ**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች ለአማኞች ማኅበር ሁለንተናዊ ደኅንነት ኃላፊነት እንዲወስዱ የሚያስችል መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። 1 ጴጥሮስ 5፥1-11 ተመልከት።

**አስተማሪ**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ቃል እውነት ሌሎች እንዲማሩ በሚያስችል መልኩ ማስተላለፍ እንዲችሉ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። ዕብራውያን 5፥12-14 ተመልከት።

**መዝሙር**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን በልዩ ልዩ ዝማሬ እንዲያመሰግኑ እና የጉባዔውን አምልኮ እንዲያግዙ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። 1 ቆሮንቶስ 14፥26 ፣ ማርቆስ 12፥36 ተመልከት።

**ምክር**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች ሌሎች ክርስቲያን ወገኖቻቸው ማጽናኛ፣ ምክር እና ማበረታቻ ሲያስፈልጋቸው ድጋፍ መስጠት የሚያስችላቸው መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። የሐዋርያት ሥራ 11፥23-24 ፣ የሐዋርያት ሥራ 14፥21-22 ተመልከት።

**ጥበብ**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ፈቃድ በልዩ ሁኔታ መረዳት እና ለዕለት ተዕለት ሕይወት እንዲተገብሩ የሚያስችል መንፈስ ቅዱስ የሚቸረው ልዩ ስጦታ ነው። ያዕቆብ 3፥13-17 ተመልከት።

**እውቀት**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ያሉ ታላላቅ እውነቶችን ልዩ በሆነ መንገድ እንዲረዱ እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ጋር እንዲያዛምዱ የሚያስችል መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። ኤፌሶን 3፥14-19 ተመልከት።

**አገልግሎት**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች ሌሎች ክርስቲያን ወገኖች ተግባራቸውን በበለጠ ውጤታማነት ማከናወን እንዲችሉ ሸክማቸውን በፈቃደኝነት ለመሸከም አቅም የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። ገላትያ 6፥1-2 ተመልከት።

**እርዳታ**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች ሌሎች ክርስቲያን ወገኖች ተግባራቸውን በበለጠ ውጤታማነት ማከናወን እንዲችሉ ሸክማቸውን በፈቃደኝነት ለመሸከም አቅም የሚሰጥ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው መንፈሳዊ ስጦታ ነው። የሐዋርያት ሥራ 6፥2-4 ተመልከት።

**መምራት**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር ሕዝብ በፈቃደኝነት እና በስምምነት የቤተ ክርስቲያንን ሥራ በውጤታማነት እንዲያከናውኑ ለማነሣሣት እና መንገድ ለማሳየት እንዲችሉ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። ዕብራውያን 13፥7 ፣ መሳፍንት 3፥10 ፣ ዘጸዓት 18፥13-16. ተመልከት።

**ማስተዳደር**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች የቤተ ክርስቲያንን አንድ የአገልግሎት ክፍል ያሰባቸውን ግቦች ማሳካት እንዲችል ውጤታማ በሆነ መልኩ አቅጣጫ እንዲያሲዙ እና ቤተ ክርስቲያን መንገዷን ይዛ እንድትቀጥል እንዲያደርጉ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። የሐዋርያት ሥራ 12፥12-21 ተመልከት።

**መስጠት**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች ለቤተ ክርስቲያን ሥራ እንዲውል ያላቸውን ቁሳዊ በረከት በተለየ ፈቃደኝነት፣ ደስታ እና ነጻነት እንዲሰጡ የሚያስችል መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። 2 ቆሮንቶስ 8፥1-5 ተመልከት።

**ርኅራኄ**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች መከራ እና ስቃይ ውስጥ ላሉት የተለየ የመረዳት እና የርኅራኄ ስሜት እንዲሰማቸው፣ በመሆኑም ለዚሁ ሲሉ ብዙ ጊዜ እና አቅም እንዲያፈሱ የሚያስችል መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። ሉቃስ 10፥30-37 ተመልከት።

**መለየት**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች አንዳንድ ድርጊቶች ወይም ሁኔታዎች ከእግዚአብሔር ይሁኑ ከሰይጣን በእርግጠኝነት ለይተው እንዲያውቁ የሚያስችል መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። የሐዋርያት ሥራ 5፥3-6 ፣ የሐዋርያት ሥራ 16፥16-18 ተመልከት።

**እምነት**
ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ቃል ኪዳን፣ ኃይል እና ሕልውና አስደናቂ የሆነ መተማመን እንዲኖራቸው እና ከዚህ የተነሣ ለመጪው የእግዚአብሔር ሥራ እና ለቤተ ክርስቲያን በጀግንነት እንዲቆሙ የሚያስችል መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። ዕብራውያን 11 ተመልከት።

**እንግዶችን መቀበል**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች ሌሎች ሰዎችን በፈቃደኝነት እና በደስታ በቤታቸው ተቀብለው እንዲያስተናግዱ የሚያስችል መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። ዘፍጥረት 18፥1-15 ተመልከት።

**የእጅ ሙያ**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች እጆቻቸውን እና አእምሯቸውን በመጠቀም ሥነ ጥበባዊ በሆኑ የፈጠራ ሥራዎች መንግሥቱን ለመገንባት እንዲችሉ የሚያደርግ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። ዘጸዓት 28፥3-4 ተመልከት።

**መማለድ**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች ረዘም ላለ ጊዜ ለመንግሥቱ ሥራ እንዲጸልዩ እና ትላልቅ በጎ ውጤቶችን እንዲያስገኙ የሚያደርግ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። 1 ተሰሎንቄ 3፥10-13 ፣ 1 ጢሞቴዎስ 2፥1-2 ተመልከት።

**ፈውስ**
የተወሰኑ ክርስቲያኖች የታመሙትን ወደ ጤና ለመመለስ እንዲችሉ የሚያደርግ መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። ያዕቆብ 5፥13-16 ፣ ሉቃስ 9፥1-2 ተመልከት።

**የወንጌል ተልዕኮ**
ለተወሰኑ የክርስቶስ አካል (አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን) አባላት ያላቸውን የትኛውንም ሌላ መንፈሳዊ ስጦታ ተጠቅመው የተለየ ባሕል ወይም ማኅበረ ሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎችን እንዲያገለግሉ የሚያስችል መንፈስ ቅዱስ የሚሰጠው ልዩ ስጦታ ነው። 1 ቆሮንቶስ 9፥19-23 ተመልከት።

**ምዕራፍ 6**

# ሰዎችን ማስተዳደር

***"ሰዎች እንዲያደርጉላችሁ የምትፈልጉትን እናንተም እንዲሁ አድርጉላቸው።"***
**ሉቃስ 6፥31**

ወርቃማው ሕግ። ይህ ሁላችንም የምናውቀው፣ ሆኖም አብዛኛውን ጊዜ ለመከተል የሚያዳግተን ሕግ ነው። ቤተ ክርስቲያን ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር እና እርስ በርሳቸው ባላቸው ግንኙነት ላይ የተመሠረተች ናት። ኢየሱስ ይህንን መርህ ያስተማረን እርስ በርስ እና ከእግዚአብሔር ጋር በስምምነት እንድንኖር እና እርሱ የሞተለትን ፍቅር ለዓለም እንድናሳይ ነው። ሰዎችን ስታስተዳድር ከእነርሱ ጋር ግንኙነት እየፈጠርክ እንጂ፣ እንዲሁ በላያቸው ላይ በሥልጣን እየተመላለስክ አይደለም። ሰዎችን ማስተዳደር ማለት ሰዎችን ለአንተ እንዲያደርጉ የምትፈልገውን ነገር ከማዘዝ ይልቅ፣ አንተ ለእነርሱ ምን ልታደርግ እንደምትችል መጠየቅ ነው። ይህም ኢየሱስ እንዳስተማረን ዕለት ተዕለት በወርቃማው ሕግ መሠረት መመላለስ ነው። በዚህ ምዕራፍ ሰዎችን የማስተዳደርን አስፈላጊነት፣ አንዳንድ ሰዎችን የማስተዳደሪያ መርሆዎች፣ እንዲሁም እንዴት ሰዎችን ማስተዳደር እንደሚቻል እናያለን።

## I. ሰዎችን ማስተዳደር ያን ያህል አስፈላጊ ነገር የሆነው ለምንድን ነው?

1. ቤተ ክርስቲያን ጉዳዩዋ ሁሉ ከሰዎች ጋር የተያያዘ ነው
   ***"እናንተ ግን ከጨለማ ወደ አስደናቂ ብርሃኑ የጠራችሁን የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ እንድታውጁ፣ የተመረጠ ትውልድ፣ የንጉሥ ካህናት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ እግዚአብሔር ለራሱ የለያችሁ ሕዝብ ናችሁ።"* – 1 ጴጥሮስ 2፥9**

   - ቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ሳትሆን ሕዝብ ናት
   - ትኩረታችን ነገሮች/ቁሶች ላይ ሳይሆን፣ ሰዎች ላይ ነው
   - ዋናው ነገር ግንኙነት ነው
     - ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ግንኙነት
     - ከክርስቶስ ጋር ያለ ግንኙነት
     - እርስ በርስ ጋር ያለ ግንኙነት

2. ሰዎች የቤተ ክርስቲያን ከሁሉ የላቀ ሃብት ናቸው
   - ሰዎች በቤተ ክርስቲያን በሙላት የሚገኙ ሃብት ናቸው
   - ሰዎች ለቤተ ክርስቲያን ሥራ የሚውሉ ብዙ ስጦታዎች እና ክህሎቶችን ይዘው ይመጣሉ
     ***"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ለጋራ ጥቅም ነው።"***
     **– 1 ቆሮንቶስ 12፥7**

     - ለአገልግሎት የሚሆኑ መንፈሳዊ ስጦታዎች
     - ለአገልግሎት የሚሆኑ ክህሎቶች

   - ሰዎች ላይ "ኢንቨስት" ማድረግ እጅግ አትራፊ ነው

3. አገልግሎት ስኬታማ የሚሆነው በሰዎች በኩል ነው
   ***"አሠራርም ልዩ ልዩ ሲሆን፤ ሁሉን በሁሉ የሚሠራው ግን ያው አንዱ እግዚአብሔር ነው።"***
   **– 1 ቆሮንቶስ 12፥6**

   - ሰዎች ሌሎችን ያገለግላሉ፤ ራሳቸውም ይገለገላሉ
   - ሌሎች ሃብቶች (ንብረቶች) ሰዎችን ማገገሚ መሣሪያ ናቸው
   - የኢየሱስ አገልግሎት የሰዎችን ልብ መማረክ ነበር

4. የቤተ ክርስቲያን አባላት በጎ ፈቃደኞች እንጂ ተቀጣሪዎች አይደሉም
   - በጎ ፈቃደኞች ማነሳሻ ያስፈልጋቸዋል
     - በእግዚአብሔር እየተመሩ እንደሆነ ሊሰማቸው ይገባል
     - መነሣሣት/ቅንዓት ከሌለ ዓላማ አይኖርም፤ ዓላማ ከሌለ ሰዎች አይኖሩም
   - በጎ ፈቃደኞች ማብረታቻ ያስፈልጋቸዋል
     - በጎ ፈቃደኞች እያደረጉ ያሉት ነገር ላይ አበጃችሁ መባል ያስፈልጋቸዋል
     - በጎ ፈቃደኞች አስቸጋሪ ሁኔታዎችን አልፈው መሥራት መቻል ይኖርባቸዋል
   - በጎ ፈቃደኞች ማነቃቂያ ያስፈልጋቸዋል
     - ገንዘብ ስለማይከፈላቸው፣ በርትተው እንዲቀጥሉ የሚገፋፋቸው ነገር ያስፈልጋቸዋል
     - በወንጌል መነቃቃት ያስፈልጋቸዋል

5. አለመግባባት/ግጭቶችን መቅረፍ ያስፈልጋል
   - በቤተ ክርስቲያን ውስጥ አለመግባባት/ግጭት የሚከሰተው በሰዎች መካከል ነው
   - ስለዚህ በአለመግባባት/ግጭት ውስጥ ሰዎችን እንዴት አድርጎ መያዝ እንደሚያስፈልግ ማወቅ አስፈላጊ ነው

## II. ሰዎችን የማስተዳደር መርሆዎች

1. ሰዎች እያንዳንዳቸው <u>ልዩ ልዩ</u> ናቸው
   ***"አንተ ውስጣዊ ሰውነቴን ፈጥረሃልና፤ በእናቴም ማሕፀን ውስጥ አበጃጅተህ ሠራኸኝ።"***
   ***– መዝሙር* 139፥13**

   - ልዩ ልዩ ክህሎቶች አሏቸው
   - ልዩ ልዩ ልምምዶች አሏቸው
   - ልዩ ልዩ ሃሳቦች አሏቸው
   - ልዩ ልዩ ሰብዕናዎች አሏቸው

2. ሰዎች <u>ቤተኝነት እንዲሰማቸው</u> ይፈልጋሉ
   - ሰዎችን የአንድ ነገር አካል እንደሆኑ እንዲሰማቸው ይፈልጋሉ
   - ሰዎች በአጠቃላይ ብቸኝነት ወይም ለብቻ መሆን አይወዱም
     ***"ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር አምላክ ፣ 'ሰው ብቻውን መሆኑ መልካም አይደለምና የሚስማማውን ረዳት አበጅለታለሁ' አለ።"* – ዘፍጥረት 2፥18**

   - ኢየሱስ ኅብረት አስፈላጊ መሆኑን ገልጿል

3. ሰዎች <u>መሳተፍ</u> ይፈልጋሉ
   - ሰዎች ተመልካች ሳይሆን ተሳታፊ መሆን ይፈልጋሉ
   - ሰዎች አስተዋጽዖ ማበርከት ይሻሉ
   - ሰዎች እንደ አስፈላጊነቱ ስጦታ እና ክህሎታቸውን መጠቀም ይሻሉ

4. ሰዎች <u>ዋጋ እንዲሰጣቸው</u> ይፈልጋሉ
   - ሰዎች ጠቃሚ እንደሆኑ እንዲሰማቸው ይሻሉ
     ***"እስር እያለሁ ስለ ወለድሁት ልጄ ስለ አናሲሞስ እለምንሃለሁ። አስቀድሞ የሚጠቅምህ አልነበረም፤ አሁን ግን ለአንተም ሆነ ለእኔ የሚጠቅም ሰው ሆኖአል።"* – ፊልሞና 1፥10-11**

   - ሰዎች ዋጋ ከተሰጣቸው፣ በበጎ ፈቃደኝነት ይሳተፋሉ

5. ሰዎች <u>አክብሮት</u> ይፈልጋሉ
   ***"ለሰው ሁሉ ተገቢውን አክብሮት ስጡ"* – 1 ጴጥሮስ 2፥17**

   - ሰዎች ክብራቸውን በጠበቀ መልኩ መታየት እና መስተናገድ ይፈልጋሉ
   - ሰዎች በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ አላቸው፤ ለእኛም ዋጋ ሊኖራቸው ይገባል

6. ሰዎች <u>እውቅና እንዲሰጣቸው</u> ይፈልጋሉ
   ***"እስጢፋኖስ፣ ፈርዶናጥስና አካይቆስ በመምጣታቸው ደስ ብሎኛል፤ ምክንያቱም እናንተ እዚህ ባለመኖራችሁ የጐደለኝን አሟልተዋል፤ የእኔንም የእናንተንም መንፈስ አሳርፈዋልና። ስለዚህ እንደነዚህ ያሉትን ሰዎች መታወቅ ይገባቸዋል።"*
   – 1 ቆሮንቶስ 16፥17-18**

   - ሰዎች ሊመሰገኑ እና ጎሽ ሊባሉ ይገባል
   - እውቅና መስጠት በራስ መተማመንን ይገነባል

7. ሰዎች <u>አቅጣጫ</u> ይፈልጋሉ
   - ራዕዩን አጋራ
     - እንደ መሪ፣ ሌሎችን ማነሣሣት እና ማነቃቃት አለብህ
     - ሁሉም ሰው አጠቃላይ ግቦች ላይ ያለውን ትኩረት እንዳይስት ጠብቅ
       ***"ራእይ በሌለበት ሕዝብ መረን ይሆናል"*
       – ምሳሌ 29፥18**

   - የሁሉንም ጥረት አስተባብር፤ አቀናጅ
     - ሁሉም በጋራ እየሠራ መሆኑን አረጋግጥ
     - እየተከናወኑ እንደሆኑ የማታውቃቸው ወይም ከቤተ ክርስቲያኗ ራዕይ እና ግቦች ጋር አብረው የማይሄዱ ተግባሮች እንዲካሄዱ አትፍቀድ

   - ከሁሉም ይበልጥ ውጤታማ የሆነውን የአመራር ዘይቤ ተጠቀም
     - ለተለያዩ ሁኔታዎች እንደ አስፈላጊነቱ የተለያየ የአመራር ዘይቤ ተጠቀም
     - እንደ አስፈላጊነቱ ኃላፊነት እና ሥራን ለሌሎች አስተላልፍ

8. ሰዎች <u>መረጃ</u> ይፈልጋሉ
    - ማሳካት የምትፈልጋቸውን ዓላማዎች እና ከእያንዳንዱ ሰው ምን እንደምትጠብቅ በግልጽ አስረዳ
        - ሁሉም ሰው ያለውን ሚና መገንዘቡን አረጋግጥ
        - ሰዎች "ይሄን ማወቃቸው አይቀርም" ብለህ እንዲሁ አትገምት፤ እንዲያውቁ የምትፈልገውን ነገር ንገራቸው
        - አስፈላጊ የሆነ መረጃን ሁሉ አጋራ

## III. ሰዎችን እንዴት እናስተዳድር?

ሰዎችን በተሻለ መንገድ ለማስተዳደር የሚከተሉትን መሠረታዊ እርምጃዎች መከተል ትችላለህ፡-

**ደረጃ #1: አሳትፏቸው**

- እንዲሳተፉ ጋብዛቸው
- መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን ጥቅም ላይ እንዲያውሉ አበረታታቸው

**ደረጃ #2: አክብራቸው**

- ለግብዓታቸው ዋጋ ስጥ
- ሐሳባቸው ምን እንደሆነ ጠይቃቸው

**ደረጃ #3: አሰልጥናቸው**

- ክህሎቶቻቸውን እና ችሎታዎቻቸውን እንዲያዳብሩ እርዳቸው
- ለሥልጠና ላካቸው ወይም ራስህ አሠልጥናቸው

**ደረጃ #4: እውቅና ስጣቸው**

- ለሚያደርጉት አስተዋጽዖ እውቅና ስጥ
- ላስመዘገቡት ስኬት የሚገባቸውን ምስጋና እና እውቅና ስጣቸው

**ደረጃ #5: ማበረታቻ ስጣቸው**

- ምስጋናህ/አድናቆትህን አነስተኛም ቢሆን በስጦታ አሳይ
- ምሳ ወይም ሻይ/ቡና ጋብዛቸው

## IV. የተለያዩ ዓይነት የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞችን ማስተዳደር

1. ደመወዝ ተከፋይ የቤተ ክርስቲያን ሠራተኞችን ማስተዳደር
    - የአገልግሎት ቡድንህ አካል ናቸው፤ ስለዚህ በሚገባ ያዛቸው፣ ደግፏቸው
    - ለእነዚህ የምትመድበው የተለያዩ ተግባሮችን ሳይሆን ኃላፊነቶችን ነው
    - የቡድን ሥራ ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል፤ ስለዚህ ሁላችሁም በጋራ መሥራት አለባችሁ
    - እያንዳንዱ ሠራተኛ በግልጽ የተቀመጠ ኃላፊነት እና ተያያዥ ሥልጣን ሊኖረው ያስፈልጋል

2. የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ማስተዳደር
    - ተለይቶ የተቀመጠ አንድ የትኩረት አቅጣጫ ወይም አገልግሎት ላይ መድባቸው
    - ሥልጣንህን እና አጠቃላይ ቁጥጥርህን እንደያዝክ ቀጥል
    - ምሪት እና ድጋፍ ስጥ
    - ቀጣይነት ያለው ሥልጠና ስጥ
    - አገልግሎትህን ከሚያደናቅፉ ሰዎች ተጠንቀቅ
        - በራሳቸው ሙሉ ሥልጣን መንቀሳቀስ የሚፈልጉ ሰዎች
        - ለሥልጣንህ አልገዛም የሚሉ ሰዎች

3. በጎ ፈቃደኞችን ማስተዳደር
    - አበረታች እና አነሳሽ ሁን
    - በግልጽ ተለይተው የተቀመጡ ዓላማዎች እና ግቦችን ስጣቸው
    - ለምትሰጣቸው ሥራ የጊዜ ገደብ አስቀምጥ፤ ሥራው በአግባቡ መጠናቀቁን ለማረጋገጥ ተከታተል
    - የወደፊት መሪዎችን ለማፍራት የቅርብ ምክር እና ክትትል (ሜንተሪንግ) ስጣቸው
    - የፈጠራ ወይም አዳዲስ ሐሳቦችን አበረታታ
    - በቀጥታ ለማስተዳደር እንዲመች አንድ መሪ ወይም የቤተ ክርስቲያን ተቀጣሪ ሠራተኛ የሆነ ሰው መድብላቸው

# <u>ሰዎችን የማስተዳደር መልመጃ</u>

*መመሪያ*: በግራ በኩል ለተገለጸው እያንዳንዱ "ሁኔታ"፣ ጥቅም ላይ መዋል ያለበትን ተገቢ ሰዎችን የማስተዳደሪያ መርህ በቀኝ በኩል አስፍር።

| **ሁኔታ** | **ሰዎችን የማስተዳደሪያ መርህ** |
|---|---|
| 1. አንድ የቤተ ክርስቲያን አባል ወደ አንተ መጥታ የአምልኮ ቡድኑን በመቀላቀል ማገልገል እንደምትፈልግ ነገረችህ | |
| 2. ከአገልግሎት መሪዎችህ አንዱ ሁሉንም የቤተ ክርስቲያን አባላት እና መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸውን የያዘ ዝርዝር እንድትሰጠው ጠየቀህ | |
| 3. አንድ ቤተ ሰብ ከአንተ ቤተ ክርስቲያን ሊለቅ ሲሉ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ በደንብ የሚያውቁት አንድም ሰው እንዳልነበረ ነገሩህ | |
| 4. ቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች የአንዳንድ ግብዓቶች/ቁሳቁስ ይሰጠን ጥያቄዎቻቸውን በቁም ነገር የሚወስድላቸው በማጣታቸው ተበሳጭተዋል። | |
| 5. የልጆች አገልግሎት መሪ ወደ አንተ መጥታ የልጆች አገልግሎት ከአጠቃላዩ የቤተ ክርስቲያን ዕቅድ ጋር እንዴት አብሮ ሊሄድ እንደሚችል ማወቅ እፈልጋለሁ አለችህ። | |
| 6. በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ያሉ ሰዎች አንድ ዋና የሚባል ፕሮጀክት ላይ በበጎ ፈቃደኝነት ለመሳተፍ ብዙም ፈቃደኝነት እያሳዩ አይደለም። | |
| 7. ሁለት የቤተ ክርስቲያንህ የአገልግሎት መሪዎች አንድን የቤተ ክርስቲያን ግብ በምን መልኩ እናሳካው የሚለው ላይ አልተስማሙም። | |
| 8. በልጆች አገልግሎት ውስጥ ረጅም ጊዜ ሲያገለግል የቆየ አንድ በጎ ፈቃደኛ በድንገት አገልግሎቱን አቋረጠ። | |

## ***ምዕራፍ 7***

## ***<u>ግጭትን መፍታት</u>***

***"ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉና።"***
***ማቴዎስ* 5፥9**

ሁሉም የቤተ ክርስቲያን ወይም የአገልግሎት/ሚኒስትሪ መሪ፣ ጉዳዩን ከሰዎች ጋር ያደረገ ማንኛውም ድርጅት ግጭት እንደሚገጥመው ማወቅ አለበት። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው፣ ቤተ ክርስቲያን ጉዳዩዋ ከሰዎች ጋር ነው፤ የተመሠረተችውም በግንኙነቶች ላይ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር ግጭት ኃጢአት ይባላል። እርስ በርስ መጋጨትም ወደ ኃጢአት ሊያመራ ይችላል፤ ስለሆነም ***ዕብራውያን* 12፥1** ላይ እንደሚለው ***"በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኀጢአት"*** ማስወገድ እና በዚያ ውስጥ ወድቀን እንዳንጠላለፍ መጠንቀቅ አለብን። ኢየሱስ በተራራው ስብከት ***ማቴዎስ* 5፥9** ላይ ***"ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉና"*** ብሏል። ኢየሱስ ሁላችንንም ሰላም የምናወርድ እንድንሆን ጠርቶናል። ግጭት መከሰቱ ደግሞ አይቀሬ ስለሆነ፣ ተዘጋጅተን ልንጠብቀው እና ሲከሰት መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መንገድ ልንይዘው ይገባል። በዚህ ምዕራፍ፣ ግጭትን በአግባቡ የመያዝን አስፈላጊነት፣ ምን ምን ግብዓቶችን ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚገባ፣ እንዲሁም ግጭት መኖሩን እንዴት እውቅና መስጠት እንደሚቻል እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መልኩ እንዴት መፍታት እንደሚቻል እናያለን።

### **I. *ግጭትን እንዴት በአግባቡ መፍታት እንደሚቻል ማወቅ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?***

1. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ግጭቶች ሁሌም መኖራቸው አይቀሬ ነው
   - ከሰዎች ጋር የተያያዘ ነገር ሁሉ ግጭት የመፈጠር ዕድልን አያይዞ ይመጣል
   - ያለው እውነት አንድ ቢሆንም፣ ግንዛቤ ግን አንጻራዊ ነው

2. አብዛኞቹ የቤተ ክርስቲያን ችግሮች ከግጭት ጋር ይያያዛሉ
   - የቤተ ክርስቲያን ማነቆ ሆነው እድገቷን ሊገቱ ይችላሉ
   - ጥቃቅን ግጭቶች ትላልቅ ችግሮች ወደ መሆን ሊያድጉ ይችላሉ

3. ግጭት በቀላሉ ቤተ ክርስቲያንን ሊሰነጥቅ ወይም ሊከፍል ይችላል

   ***"ቤትም እርስ በርሱ ከተለያየ ሊቆም አይችልም።"***
   **– *ማርቆስ* 3፥25**

   - ተጻራሪ ጎራዎችን ሊፈጥር ይችላል
   - ሥልጣንህን ዋጋ ቢስ ሊያደርገው ይችላል

4. ግጭቶችን በአግባቡ መፍታት አንዲት ቤተ ክርስቲያንን ወደ ፊት እንድትራምድ ያስችላታል
   - የግጭቶች በአግባቡ መፈታት የእድገት እንቅፋቶችን ያስወግዳል
   - እርስ በርስ መግባባትን ይፈጥራል፤ ወደ ፊትም ግጭትን ለመፍታት መሠረት ይሆናል

## II. የግጭት መነሻዎች

1. በአባላት መካከል
    - የተለያዩ እይታዎች
    - የተለያዩ ልምዶች
    - የተለያዩ ግቦች እና ዓላማዎች

2. በመጋቢ እና በአባላት መካከል
    - የተለያዩ ዓላማዎች
    - የተለያዩ መነሻ ሰበቦች
    - የተለያዩ ዘይቤዎች (የአመራር/የአገልግሎት)

3. በልማዳዊ እና በዘመናዊ እይታዎች መካከል
    - ልማድን የተከተለ አካሄድ ከ-ነጻነት
    - ምቾትን ጠብቆ መጓዝ ከ-አስፈላጊነት
    - ዘላቂውን አካሄድ ማስቀጠል ከ-እንደየ ሁኔታው ነገሮችን መቀያየር

4. በትውልዶች መካከል
    - አሁን ከ-ያኔ
    - ወጣቱ ካረጀው
    - ጮክ ያለ ከ-ለሆሳስ

5. በአገልግሎቶች መካከል
    - ለግብዓቶች መፎካከር
    - ሰዎችን ለማግኘት/ለመያዝ መፎካከር
    - በሰፊው ለመታየት/ለመተዋወቅ መፎካከር

## III. የግጭት ምንጮች

ሁሉም ግጭት ምንጭ አለው፤ ይህ ምንጭም ከሚከተሉት 3ቱ ከአንዱ ይሆናል፡-

1. ሰይጣን
    - ሰይጣን ሁሌም በዙሪያችን በኃጢአት እንድንወድቅ ሲፈትነን ይኖራል

***"ራሳችሁን የምትገዙ ሁኑ፤ ንቁም፤ ጠላታችሁ ዲያብሎስ የሚውጠውን በመፈለግ እንደሚያገሣ አንበሳ ወዲያ ወዲህ ይዞራል።" - 1 ጴጥሮስ 5፥8***

2. ኃጢአተኛ ተፈጥሯችን
    - ከውልደታችን አንሥቶ ኃጢአተኞች ነን። ተፈጥሯችን ነው።

***"ሥጋ መንፈስ የማይፈልገውን፣ መንፈስም ሥጋ የማይፈልገውን ይመኛልና፤ እነዚህ እርስ በርሳቸው ስለሚጋጩ፣ የምትፈልጉትን አታደርጉም።" - ገላትያ 5፥17***

3. በኃጢአት የተሞላችው ዓለም
    - ዓለማችን ራሷ ብልሹ ሆና እኛም እንደዛው እንድንሆን ትስበናለች።

***"ምክንያቱም በዓለም ያለው ሁሉ፦ የሥጋ ምኞት፣ የዐይን አምሮትና የኑሮ ትምክሕት ከዓለም እንጂ ከአብ የሚመጣ አይደለም።" - 1 ዮሐንስ 2፥16***

## IV. የግጭት ምክንያቶች

1. ከጸሎት፣ ከጥሞና እና ከውይይት በኋላ የሚቀረጹ ሆኖም ጥርት ያላሉ ራዕይ ወይም ግቦች
    - የተለያዩ ሰዎች እርስ በርስ የሚጋጩ የተለያዩ ራዕዮች ወይም ግቦች ይኖሯቸዋል
    - ማዕከላዊ የሚባል ራዕይ ጨርሶ ይጠፋል
      ***"ራዕይ በሌለበት ሕዝብ መረን ይሆናል"***
      **- ምሳሌ 29፥18**

2. ስትራቴጂካዊ/ስልታዊ የሆነ ዕቅድ አለመኖር
    - ግብዓቶችን ቅደም ተከተል እየሰጠ የሚደለድል ዕቅድ የለም
    - ሰዎች ከግልም ሆነ ከጋራ መሻቶቻቸው በመነሣት ለግብዓቶች ፉክክር ውስጥ ይገባሉ
    - ሰዎች ለመጪ ሳይሆን ለወቅታዊ መሻቶቻቸው ሲሉ ግብዓቶችን ለማግኘት ይፎካከራሉ
    - የቤተ ክርስቲያን ግብዓቶች በሚገባ አይደራጁም

3. በበቂ መጠን በደቀ መዝሙርነት አለማደግ
    - ሰዎች ክርስቲያናዊ መርሆዎችን አልተማሩም
    - የቤተ ክርስቲያን አመራር ክርስቲያናዊ እሴቶችን አልታዩበትም
    - መጽሐፍ ቅዱሳዊ የግጭት አፈታት ትምህርት አልተሰጠም

4. የተግባቦት እና ነገሮችን የማስረዳት ክፍተት
    - ሰዎች ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስላሉ ሌሎች የሚያስፈልጉ ነገሮች አያውቁም
    - ሰዎች በቋሚነት እርስ በርስ መረጃ አይለዋወጡም
    - የመረጃ ልውውጥ ወይም ተግባቦት ለሚጠየቁት ወይም ለሚባሉት ነገር መልስ መስጠት እንጂ በራስ ተነሣሽነት የሚደረግ አይደለም

5. ለችግሮች እልባት ሳይሰጡ መቆየት
    - ያለፉ ግጭቶችን ሳይፈቱ ማለፍ
    - አሁን ላይ ያሉ ችግሮችን ቸል ማለት
    - ሊፈጠሩ የሚችሉ ግጭቶችን ቀድሞ አለመገመት

## IV. ግጭትን ለይቶ ማወቅ

1. ግልጽ ምልክቶች
    - ስሜታዊ መገንፈል
    - የጽሑፍ አቤቱታ
    - የሃሜት እና አሉባልታ መብዛት

2. ያን ያህል ግልጽ ያልሆኑ (ማስጠንቀቂያ) ምልክቶች
   - ከቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ ክንውኖች ገለል ማለት
   - የሥራ መዘግየት ወይም ጨርሶ አለመንቀሳቀስ
   - የግንኙነት አለመኖር

## V. *ግጭትን መፍታት*

***"ወንድምህ ቢበድልህ ሄደህ አንተና እርሱ ብቻ ሆናችሁ ጥፋቱን ንገረው። ቢሰማህ፣ ወንድምህን እንደ ገና የራስህ ታደርገዋለህ። ባይሰማህ ግን ቃል ሁሉ በሁለት ወይም በሦስት ምስክሮች ፊት ስለሚጸና፣ አንድ ወይም ሁለት ሰው ይዘህ አነጋግረው። እነርሱን ባይሰማ ለቤተ ክርስቲያን ንገር፤ ቤተ ክርስቲያንንም ባይሰማ እንደ አሕዛብና እንደ ቀረጥ ሰብሳቢ ቍጠረው።"***

**ማቴዎስ 18፥15-17**

### 1. <u>ከሌላ ሰው ጋር ግጭት ውስጥ ስትሆን፡-</u>

***"በራስህ ዐይን ውስጥ ያለውን ግንድ ሳታይ ወንድምህን፣ 'ወንድሜ ሆይ፤ በዐይንህ ውስጥ ያለውን ጕድፍ ላውጣልህ' እንዴት ልትለው ትችላለህ? አንተ ግብዝ፤ በመጀመሪያ በዐይንህ ውስጥ የተጋደመውን ግንድ አውጣ፤ ከዚያ በኋላ በወንድምህ ዐይን ውስጥ ያለውን ጕድፍ ለማውጣት አጥርተህ ታያለህ።"***
**- ሉቃስ 6፥42**

1. ከግጭቱ የአንተ ድርሻ የቱን ያህል እንደሆነ ለይተህ እወቅ
   - ለራስህ ሃቀኛ በመሆን አንተ ኃላፊነቱን ልትወስድባቸው የሚገቡ የግጭቱን ክፍሎች ለይተህ እወቅ (ለምሳሌ፡- ሸካራ ቃላትን መጠቀም፣ ሰውን የሚያስከፋ ንግግር፣ ሃሜት፣ አለመታገስ ወዘተ)
2. በቅድሚያ አንተ ኃላፊነቱን መውሰድ ያለብህ የግጭቱን ክፍል አምነህ በመቀበል ጥፋትህን ተናዘዝ
   - ከተጋጨኸው ሰው ጋር ጉዳዩን ለመፍታት ስትነሣ፣ መነሻህ ይህ መሆን አለበት
3. ለስህተትህ ይቅርታ ጠይቅ
   - ይቅርታ ከጠየቅክ እና ያ ሰው ይቅርታ ካደረገልህ በኋላ፣ አንተ ደግሞ በግጭቱ ስለደረሰብህ ነገር ልትናገር ትችላለህ
4. ይቅርታ ከተቀበልክ እና አንተም ይቅር ካልክ በኋላ፣ ግጭቱ ተፈቷል
5. ሌላው ሰው ይቅር የማይልህ ከሆነ፣ በ**ማቴዎስ 18፥15-17** እንደተገለጸው አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎችን አሳትፍ።

### 2. <u>ግጭትን በመፍታት መካከለኛ ለመሆን ተጠርተሃል፡-</u>

1. ግጭቱ ምን እንደሆነ ለይተህ እወቅ
   - የግጭቱ መገለጫ መንገዶችን ሳይሆን፣ ራሱ ችግሩ ምን እንደሆነ ለይተህ እወቅ
   - የችግሩ ምንነት እና ለየትኛው ነገር ማን ኃላፊነቱን መውሰድ አለበት የሚለው ላይ ሁሉም ሰው መስማማቱን አረጋግጥ። አስፈላጊ ከሆነ ኋላ ላይ ይቅር ለመባባል እንዲያመች እያንዳንዱን የደረሰ በደል በጽሑፍ መዝግብ።

2. የግጭቱን ተሳታፊዎች ለይተህ እወቅ
   - ግጭቱ ውስጥ ማን ማን ድርሻ እንደነበረው እወቅ
   - እያንዳንዳቸው በምን መልኩ እንደተሳተፉ እወቅ (እያንዳንዳቸው ምን በደል አድርሰዋል?)
   - እያንዳንዳቸው ለምን በግጭቱ እንደተሳተፉ አጣራ

3. ግጭቱን መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነ መንገድ ፍታው
   - በምታደርገው ሁሉ እግዚአብሔርን አክብር!
   - እያንዳንዱን የግጭቱ ተሳታፊ ስህተታቸውን እንዲያውቁ እና እንዲናዘዙ አድርግ (**ሉቃስ 6፥42**)
   - እያንዳንዱ ሰው ይቅርታ እንዲጠይቅ አድርግ
   - ይቅር ከተባባሉ በኋላ፣ ግጭቱ ተፈቷል
   - ይቅር ካልተባባሉ፣ ምስክሮችን በማሳተፍ ሂደቱን ቀጥል (**ማቴዎስ 18፥15-17** ላይ በተገለጸው መሠረት)

4. ግጭቱን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ፍታው
   - ግጭቶች ዕድልን ይዘው ይመጣሉ
   - ግጭቱን ለመፍታት በምታደርገው ጥረት በደል እንዳትፈጽም ተጠንቀቅ
   - ነገሮችን በመገመት ሁኔታውን አታባብስ። እውነታውን አጣራ
   - ታላላቆቹን ትዕዛዛት አስብ
     - እግዚአብሔርን መውደድ
       ***"[ኢየሱስም]እንዲህ አለው፤ '"ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤" ይህ የመጀመሪያውና ከሁሉ የሚበልጠው ትእዛዝ ነው' "***
       **- ማቴዎስ 22፥37**

     - እርስ በርስ መዋደድ
       ***"ሁለተኛውም ያንኑ ይመስላል፤ ይህም፣ "ጎረቤትህን እንደ ራስህ ውደድ" የሚለው ነው"*** **- ማቴዎስ 22፥39**

## VI. ግጭትን ተሻግሮ መጓዝ

1. እኛ ኃላፊነት መውሰድ የምንችለው ለራሳችን ድርጊት ብቻ ነው
   - በጥበብ ኑር
     ***"እንግዲህ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ።"***
     **– ኤፌሶን 5፥15**

   - ልብን መቀየር የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነው
     ***"የእግዚአብሔር መንፈስ በኀይል ይወርድብሃል፤ ከእነርሱ ጋር ትንቢት ትናገራለህ፤ እንደ ሌላ ሰውም ሆነህ ትለወጣለህ።"*** **- 1 ሳሙኤል 10፥6**

2. ይቅርታ ኃይል ነው
   - ግጭቶችን ወደ ኋላ ትተህ ቀጥል
   - ኢየሱስ እንዳለው፣ "ከእንግዲህ ኃጢአት አትሥራ"

     ***"ኢየሱስም፣ "እኔም አልፈርድብሽም፤ በይ ሂጂ፤ ከእንግዲህ ግን ኀጢአት አትሥሪ" አላት።"***
     **– ዮሐንስ 8፥11**

3. ሰላም የምታወርድ/አስታራቂ ሁን

***"ሰላምን የሚያወርዱ ብፁዓን ናቸው፤ የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው ይጠራሉና።"***
**– ማቴዎስ 5፥9**

## VII. ግጭቶች ሁሌም መጥፎ አይደሉም

1. ምንም በደል ወይም ኃጢአት በሌለበት ግጭት ሊከሰት ይችላል
(ይህም ማለት፣ አንድን ችግር ለመፍታት ሁለት የተለያዩ አስተያየቶች ሲኖሩ እና ሁለቱም አንድ የጋራ በጎ ግብን ለማሳካት እና ጥሩ ውጤት ለማምጣት የተነሡ ሲሆኑ ነው)

2. ግጭት አንድ ልብ መባል ያለበትን ጉዳይ ሊያመለክት ይችላል
(ይህም ማለት፣ በደንብ ሊታይ ወይም ሊቀረጽ የሚገባ ሂደትን የሚያሳይ ሊሆን ይችላል)

# <u>የግጭት አያያዝ መልመጃ</u>

| በቤተ ክርስቲያን ሊያጋጥሙ የሚችሉ ግጭቶች ምሳሌዎች | ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ መፍትሔዎች |
|---|---|
| 1. *የወጣቶች አገልግሎት መሪ በተመደበለት ግብዓት እና በተሰጠው ስፍራ መጠን ደስተኛ አይደለም፤ የበለጠ ያስፈልገናል ይላል።* | |
| 2. *ቤተ ክርስቲያኗ በምትከተለው አዲስ አቅጣጫ ላይ፣ የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች ከመጋቢው ጋር አለመግባባት ላይ ናቸው።* | |
| 3. *አንዳንድ ዕድሜያቸው ገፋ ያሉ የጉባዔ አባላት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አምልኮ ላይ የሚውለው አዲስ አዘማመር ዘዬን አስመልክቶ ቅሬታ አቅርበዋል፤ "የድሮ" መዝሙሮች ይበልጥ እንዲዘመሩ ይፈልጋሉ።* | |
| 4. *የጉባዔህ አባላት የሆኑ ሁለት ቤተ ሰቦች በመሬት ጉዳይ የከረረ ክስ ውስጥ ገብተዋል፤ ሌሎች አባላትም በዚህ ጉዳይ ወገን ለይተው ሲቆሙ እያየህ ነው።* | |
| 5. *የአምልኮ መሪህ በማመንዘር እየታማ ነው።* | |

**ምዕራፍ 8**

## ***<u>ደቀ መዛሙርትን ማፍራት</u>***

***"ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ በአብ፣ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው"***
**ማቴዎስ 28፥19**

በምድር ላይ ቤተ ክርስቲያን የተመሠረተችው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ይኖራቸው ዘንድ ሰዎችን ለመሳብ ነው። ***"እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም የላከው በዓለም ለመፍረድ ሳይሆን፣ ዓለምን በእርሱ ለማዳን ነው።"*** **(ዮሐንስ 3፥17)** የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንደ መሆናችን፣ ቀዳሚ ሥራችን ቤተ ክርስቲያንን ማስተዳደር ሳይሆን ሌሎችን ወደ ክርስቶስ ***መምራት*** ነው። ደቀ መዝሙርነት ማለት ይህ ነው። በስብከት፣ በማስተማር፣ በወንጌል ሥርጭት አሊያም በአምልኮ፣ በየትኛውም መንገድ መነሻ ዓላማችን "ክርስቶስ በሌሎች ውስጥ ተቀርጾ" (***ገላትያ* 4፥19**) ማየት ነው። በዚህ ምዕራፍ፣ ደቀ መዝሙር ማፍራትን፣ ዓላማውን፣ መርሆዎቹን እና ሂደቱን፣ እንዲሁም የማያቋርጥ ክትትል እና ምዘናን አስፈላጊነት እናያለን።

**በማስተማር እና ደቀ መዛሙርትን በማፍራት መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?**

- ማስተማር ማለት እውቀትን ወይም መረጃን ማስተላለፍ ነው። ጉዳዩ ***ከማወቅ*** ጋር ነው።
- ደቀ መዝሙር ማፍራት ማለት እውቀትን ወይም መረጃን በተግባር ማዋል ነው። ጉዳዩ ***ከድርጊት*** ጋር ነው።

### **I.** ***ደቀ መዛሙርትን የማፍራት ዓላማ***

1. ክርስቶስ በሌሎች ውስጥ ተቀርጾ ማየት
***"የምወዳችሁ ልጆቼ ሆይ፤ ክርስቶስ በውስጣችሁ እስኪቀረጽ ድረስ ስለ እናንተ እንደ ገና ምጥ ይዞኛል" – ገላትያ* 4፥19**

    - ይህ የቤተ ክርስቲያን <u>ዋና</u> ግብ ነው
    - አንድ የጠፋ ልጅ ሲገኝ፣ በመንግሥተ ሰማይ ታላቅ ደስታ ይሆናል!
    ***"እላችኋለሁ፤ እንደዚሁም ንስሓ በሚገባ በአንድ ኀጢአተኛ በእግዚአብሔር መላእክት ፊት ደስታ ይሆናል።"*** **- ሉቃስ 15፥10**

2. የሌሎችን መንፈሳዊ ስጦታዎች ለማዳበር
***"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስን መግለጥ ለእያንዳንዱ ሰው የሚሰጠው ሊጋራ ጥቅም ነው።"***
**- 1 ቆሮንቶስ 12፥7**

    - በአባላትህ ውስጥ ያሉት ስጦታዎች እንዲወጡ ለማስቻል
    - አባላትህ ያሏቸውን መንፈሳዊ ስጦታዎች ጥቅም ላይ እንዲያውሏቸው ለማስቻል

3. ሌሎችን ለአገልግሎት ለማሰልጠን እና ለማስታጠቅ

   ***"ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው።"* - 2 ጢሞቴዎስ 3፥16-17**

   - የቤተ ክርስቲያን አባላትን ለማገልገል
   - ከቤተ ክርስቲያን ውጪ ያሉትን ለማገልገል

4. ቤተ ክርስቲያንን ለማሳደግ
   - ደቀ መዛሙርት ሌሎች ደቀ መዛሙርትን ያፈራሉ

     ***"ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ … ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው…"*- ማቴዎስ 28፥19**

   - አገልግሎትህን ወደ ሌሎች ሰዎች ወይም ወደ ሌላ ሕዝብ ለማድረስ

5. ሌሎች መሪዎችን ለማፍራት የማያዳግም ቅድመ ሁኔታ ስለሆነ
   - መሪ የመሆን አቅሙ ያላቸው ሰዎች በቅድሚያ ደቀ መዛሙርት መሆን አለባቸው
   - ለመሪነት ጠንካራ እምነት ወሳኝ መስፈርት ነው

## III. *ደቀ መዝሙር የማፍራት መርሆዎች*

1. ደቀ መዝሙርነት ማብቂያ የለውም

   ***"ስለዚህ ስለ ክርስቶስ የተሰጠውን የመጀመሪያ ትምህርት ትተን ወደ ብስለት እንሂድ፤ ከሞተ ሥራ ንስሓ ስለ መግባትና በእግዚአብሔር ስለ ማመን እንደ ገና መሠረትን አንጣል"* – ዕብራውያን 6፥1**

   - ከደቀ መዝሙርነት "የሚመረቅ" የለም
   - የመድረሻውን ያህል ጉዞውም ወሳኝ ነው

2. የቤተ ክርስቲያን ቁጥር አንድ ዋና ተግባር ነው

   ***"ስለዚህ ሂዱና ሕዝቦችን ሁሉ … ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው…"*- ማቴዎስ 28፥19**

   - ቤተ ክርስቲያን የተፈጠረችው ለዚህ ዓላማ ነው
   - በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለ ሁሉም ነገር ከደቀ መዝሙርነት ይጠቀማል
     - ሰዎች ደቀ መዛሙርት ሲሆኑ ይበልጥ ያገለግላሉ
     - ሰዎች ደቀ መዛሙርት ሲሆኑ በአገልግሎት ይሳተፋሉ
     - ሰዎች ደቀ መዛሙርት ሲሆኑ ለቤተ ክርስቲያን ሥራ የበለጠ ይሰጣሉ/ይለግሳሉ

3. ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ጊዜ ይወስዳል
   - በአንድ ጀንበር ወይም በአፋጣኝ የሚሆን አይደለም
   - ተራራ የምትወጣው እንዴት ነው? - በአንድ ጊዜ አንድ እርምጃ በመራመድ

4. ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ጥረት ይጠይቃል
   - ሰዎች ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል
   - ሰዎች ማበረታቻ ያስፈልጋቸዋል
   - ሰዎች ተጠያቂ መደረግ ያስፈልጋቸዋል

5. ደቀ መዛሙርትን ማፍራት ሰዎችን ይፈልጋል
    - አባላትህን ደቀ መዛሙርት በማድረግ እንዲያግዙ ሌሎችን ማሳተፍ አለብህ
    - ምስክርነቶች በጣም ውጤታማ መሣሪያዎች ናቸው
    - እያንዳንዱ ክርስቲያን አብሮት የሚያጓዝ ወንድም ወይም እህት ያስፈልገዋል
      ***"አንዱ ቢወድቅ፣ ባልንጀራው ደግፎ ያነሣዋል። ቢወድቅ የሚያነሣው ረዳት የሌለው ግን፣ እንዴት አሳዛኝ ነው!" – መክብብ 4፥10***

6. ደቀ መዛሙርትን ማፍራት የራስ ፍላጎትን ይጠይቃል
    - ***"ክርስቶስ በሌሎች ውስጥ ተቀርጾ ለማየት"*** መፈለግ አለብህ - **ገላትያ 4፥19**
    - ሁላችንም በእምነታችን ለማደግ ፍላጎት ሊኖረን ይገባል
      ***"ወደ እግዚአብሔር ቅረቡ፤ እርሱም ወደ እናንተ ይቀርባል።" – ያዕቆብ 4፥8***

## IV. ደቀ መዛሙርትን የማፍራት ሂደት

### *ሀ. የደቀ መዛሙርት መለያ ምልክቶች ምንድን ናቸው?*

1. <u>እምነት</u>
   **"ምክንያቱም የምንኖረው በእምነት እንጂ በማየት አይደለም።" - 2 ቆሮንቶስ 5፥7**

    - ደቀ መዝሙር በእምነት ይመላለሳል
    - ደቀ መዝሙር በእግዚአብሔር ይተማመናል
    - ደቀ መዝሙር በመከራ ጊዜ እምነቱን የሙጥኝ ይላል

2. <u>አምልኮ</u>
   ***"[ኢየሱስም] እንዲህ አለው፤ " 'ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍጹም ነፍስህ፣ በፍጹም ሐሳብህ ውደድ፤'" - ማቴዎስ 22፥37***

    - ደቀ መዝሙር ለእግዚአብሔር ሉዓላዊ ሥልጣን እውቅና ይሰጣል
    - ደቀ መዝሙር ሁልጊዜም ክብሩን ለእግዚአብሔር ይሰጣል!
    - ደቀ መዝሙር የአምልኮ ፕሮግራም ላይ በቋሚነት ይገኛል

3. <u>የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት</u>
   ***"ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤ ይኸውም የእግዚአብሔር ሰው ለመልካም ሥራ ሁሉ ብቁ ሆኖ እንዲገኝ ነው።"***
   **- 2 ጢሞቴዎስ 3፥16-17**

    - ደቀ መዝሙር ዘወትር የእግዚአብሔርን መንገድ ይማራል
    - ደቀ መዝሙር የእግዚአብሔርን ጥበብ ይሻል
    - ደቀ መዝሙር መልስን የሚፈልገው ከእግዚአብሔር ነው

4. <u>**ጸሎት**</u>

   ***"ሳታቋርጡ ጸልዩ"* - 1 ተሰሎንቄ 5፥17**

- *ደቀ መዝሙር በየዕለቱ ከእግዚአብሔር ይነጋገራል*
- *ደቀ መዝሙር በመንፈስ ይኖራል*
- *ደቀ መዝሙር እግዚአብሔር ለሕይወቱ ያለውን ፈቃድ ይፈልጋል/ፈልጎ ያገኛል*

5. <u>**አገልግሎት**</u>

   ***"ስለዚህ የተወደዳችሁ ወንድሞቼ ሆይ፤ ጸንታችሁ ቁሙ፤ በምንም ነገር አትናወጡ። ለጌታ ሥራ ዘወትር የምትተጉ ሁኑ፤ ምክንያቱም ለጌታ የምትደክሙት በከንቱ እንዳልሆነ ታውቃላችሁ።"***
   **- 1 ቆሮንቶስ 15፥58**

- *ደቀ መዝሙር የክርስቶስን አካል ያገለግላል*
- *ደቀ መዝሙር ቅድሚያ ሌሎች ሰዎችን ያገለግላል*
- *ደቀ መዝሙር የክርስቶስን ምሳሌ ይከተላል*

6. <u>**ተልዕኮ እና ምስክርነት**</u>

   ***"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በሚወርድበት ጊዜ ኀይልን ትቀበላላችሁ፤ በኢየሩሳሌም፣ በይሁዳና በሰማርያ ሁሉ፣ እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ።"* - የሐዋርያት ሥራ 1፥8**

- *ደቀ መዝሙር እግዚአብሔር ያደረገለትን ነገር ለሌሎች ይናገራል*
- *ደቀ መዝሙር እግዚአብሔር ወደመራው ይሄዳል*
- *ደቀ መዝሙር ሌሎች ደቀ መዛሙርትን ያፈራል*

## ለ. ደቀ መዛሙርትን የማፍራት ዕቅድ መቅረጽ

1. *ደቀ መዛሙርትን ለማፍራት ሂደት የሚውሉ ግቦችን ቅረጽ*
2. *መሪ እና አስተማሪ ሊሆኑ ይችላሉ የምትላቸውን ሰዎች ወስን*
3. *ነገሮችን ሆነ ብለህ በማስተዋል እና በራስ ተነሣሽነት አድርግ*
4. *ቀጥሎ እንደሰፈረው ዓይነት ደቀ መዛሙርትን የማፍራት ስልት/ስትራቴጂ ንደፍ፡-*

*ደረጃ* 1: <u>**ለአምልኮ**</u> *መጋበዝ*

- *ሁሉም ሂደት የሚጀምረው የአምልኮ ፕሮግራም ላይ እንዲመጡ ከመጋበዝ ነው*
- *የመንፈስ ቅዱስ መገኘት እንዲነበኛቸው ዕድል ስጣቸው*
- *መንፈስ ቅዱስ ልዩ በሆነ መንገድ እንዲነካቸው ጸልይ*
- *ሲነኩ፣ ክርስቶስን እንዲቀበሉ አበረታታቸው*
- *እምነታቸውን በይፋ እንዲያውጁ አበረታታቸው*

*ደረጃ* 2: <u>***የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት***</u> *ውስጥ አካታቸው*

- *መደበኛ የሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ውስጥ አስገባቸው*
  - *የክርስትናን መሠረታዊ ነገሮች አስተምራቸው*
  - *በእምነት መኖርን አስተምራቸው*
  - *መጽሐፍ ቅዱሳዊ እይታን/ንጽረተ ዓለምን አስተምራቸው*
- *በግላቸው በየዕለቱ መጽሐፍ ቅዱስን እንዲያነቡ አበረታታቸው*

ደረጃ 3: **<u>የጸሎት</u>** ሕይወት እንዲኖራቸው አበረታታቸው

- የጸሎት ሥልጠና ስጣቸው
- በጸሎት አገልግሎት ውስጥ አሳትፋቸው

ደረጃ 4: **<u>በአገልግሎት</u>** አሳትፋቸው

- በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ማገልገል አለባቸው
  - እንደ አባል፣ ቤተ ክርስቲያንን መደገፍ አለባቸው
  - የክርስቶስ አካል ክፍል እንደ መሆናቸው የተጣለባቸው ግዴታ ነው
- እንደ ችሎታቸው እንዲያገለግሉ አድርጋቸው
  - ባላቸው መንፈሳዊ ስጦታ መሠረት
  - ባሏቸው የተፈጥሮ ችሎታዎች እና ክህሎች መሠረት

ደረጃ 5: **<u>አገልግሎት/ሚኒስትሪ</u>** ውስጥ አካታቸው

- የተልዕኮ/ሚሽን አገልግሎት ዕድሎችን ስጣቸው
  - አካባቢያዊ
  - ብሔራዊ
  - ዓለም አቀፋዊ
- የወንጌል ስርጭት ሥልጠና ስጣቸው
  - ምስክርነትን ማዘጋጀት
  - የሚመሰክሩላቸው ሰዎችን ዝርዝር ማዘጋጀት
- ለቤተ ክርስቲያን ወይም ለአገልግሎት/ሚኒስትሪ መሪነት እንዲበቁ አሰልጥናቸው

ደረጃ 6: አባላትን ደቀ መዛሙርት ከመሆን **<u>ደቀ መዛሙርትን ወደ ማፍራት</u>** አሻግራቸው

- ሌሎችን በማደግ እንዲያግዙ አበረታታቸው
- ሌሎችን ማሰልጠን እንዲችሉ አሰልጥናቸው

## ሐ. የማያቋርጥ ክትትል እና ምዘና

- በየዓመቱ ደቀ መዛሙርት የማፍራት ሂደትህን በመመዘን የሚከተሉትን ጥያቄዎች ጠይቅ፡-
  1. ደቀ መዛሙርትን በማፍራት ሂደት ውስጥ በንቃት እየተሳተፉ የሚገኙ አባላት ስንት ናቸው?
  2. ስኬት እየተቀዳጀን ያለነው የቱ ጋር ነው?
  3. አባላታችን በግላቸው ባላቸው እምነት እያደጉ ነው?
  4. ሂደቱ ለቤተ ክርስቲያን ፍሬ እያስገኘ ነው? በግለሰብ ደረጃስ?
  5. ሂደቱ በቤተ ክርስቲያናችን ላይ ምን ዓይነት ተጽዕኖ አሳድሯል? በማኅበረ ሰባችን ላይስ?

- እንደ አስፈላጊነቱ ማስተካከያዎችን አድርግ
  - ስኬት ያመጡ ክፍለ ጊዜዎች ወይም ትምህርቶች (“ኮርሶች”) ላይ ሰዎች ይበልጥ እንዲሳተፉ አበረታታ
  - ሌሎችን ለማበረታታት ምስክርነቶችን ተጠቀም

# ደቀ መዛሙርትን የማፍራት መልመጃ

***መመሪያ፡-*** ከሥር የቀረበው ሠንጠረዥ ውስጥ፣ በቤተ ክርስቲያን ደቀ መዛሙርትን የማፍራት ፕሮግራም ውስጥ በእያንዳንዱ ደረጃ ምን ርዕሰ ጉዳዮችን ማካተት እንደሚያስፈልግ ሐሳብ ወይም አስተያየትህን አስፍር።

- **አዲስ አማኝ**: ደረጃ 1 (*የእምነት መነሻዎች*)

| | | |
|---|---|---|
| 1. እግዚአብሔር ማነው? | 5. | 9. |
| 2. ጥምቀት | 6. | 10. |
| 3. የጌታ እራት | 7. | 11. |
| 4. የመጽሐፍ ቅዱስ ዳሰሳ (ብሉይ እና አዲስ ኪዳን) | 8. | 12. |

- ***መሠረታዊ* አማኝ:** ደረጃ 2 (*የእምነት መሠረቶች*)

| | | |
|---|---|---|
| 1. ፍጥረት - አሪት ዘፍጥረት | 5. | 9. |
| 2. መንፈሳዊ ስጦታዎች | 6. | 10. |
| 3. ክርስቲያናዊ ሕይወት - አዲስ ኪዳን | 7. | 11. |
| 4. ሥላሴ | 8. | 12. |

- **የተደላደለ አማኝ:** ደረጃ 3 (*የእምነት ኢድገት*)


| | | |
|---|---|---|
| 1. የብሉይ ኪዳን ታሪክ | 5. | 9. |
| 2. ሰይጣን እና ክፉው ኃይል | 6. | 10. |
| 3. እምነት – ዕብራውያን | 7. | 11. |
| 4. መንፈሳዊ እድገት | 8. | 12. |

- **ጠንካራ አማኝ:** ደረጃ 4 (*እምነት በተግባር*)

| | | |
|---|---|---|
| 1. ቃሉን ማስተማር | 5. | 9. |
| 2. አገልግሎትን መምራት | 6. | 10. |
| 3. ተልዕኮ/ሚሽን | 7. | 11. |
| 4. የመጨረሻው ዘመን - የዮሐንስ ራዕይ | 8. | 12. |

# ክፍል 3

## ግብዓት አስተዳደር



**ምዕራፍ 9**

# ስልታዊ (ስትራቴጂክ) ዕቅድ ማውጣት

***"ከእናንተ አንድ ሰው ሕንጻ ለመሥራት ቢፈልግ፣ መደምደም መቻል አለመቻሉን በመጀመሪያ ተቀምጦ ዋጋውን የማይተምን ማን ነው? መሠረቱን ጥሎ መደምደም ቢያቅተው፣ ያዩት ሁሉ ይዘባበቱበታል"***
**ሉቃስ 14፥28-29**

ዕቅድ ማውጣት የቤተ ክርስቲያን አመራር አስፈላጊ ክፍል ነው። በካሊፎርኒያ (አሜሪካ) የምትገኘው የክሪስታል ካቴድራል ቤተ ክርስቲያን መጋቢ እና ጸሐፊ የሆኑት ሮበርት ሹለር፣ *"ሳያቅዱ የሚቀሩ ሰዎች፣ ሳይሳካላቸው ለመቅረት እያቀዱ ነው"* የሚል አባባል አላቸው። በግልጽ የተቀመጠ ዕቅድ ሲኖር ቤተ ክርስቲያን ያሏትን ንብረቶች እና ግብዓቶች ራዕዩዋን ለማሳካት ይበልጥ በሚያስችል መልኩ መጠቀም ትችላለች። ዕቅድ ሳይኖር ሲቀር፣ አብያተ ክርስቲያናት ያላቸውን ውሱን የሆነ ግብዓት እና ጠቃሚ ጊዜ ያባክናሉ፤ ብሎም እግዚአብሔር እንዲፈጽሙ የጠራቸውን ጥሪ ሳያሳኩ ይቀራሉ። ዕቅድ መኖሩ አንዲት ቤተ ክርስቲያን ቀድሞ ከታሰበው መስመር ውጪ እንዳትሄድ ገደብ ይጥልባታል ማለት አይደለም፤ ይልቁንም ቤተ ክርስቲያን ስልታዊ በሆነ መንገድ ያሏትን ሃብቶች ለከፍተኛ ውጤታማነት ጥቅም ላይ እንድታውል መሠረት ይሆናታል። በዚህ ምዕራፍ፣ ስልታዊ የሆነ ዕቅድ ምን ምን ነገሮችን ማካተት እንዳለበት እና እንዲህ ያለ ዕቅድ ለቤተ ክርስቲያን እንዴት መቅረጽ እንደሚቻል እናያለን።

## I. ስልታዊ ዕቅድ ምንድን ነው?

- ስልታዊ ዕቅድ ማውጣት ማለት ተግባሮችን እና ግቦችን፣ ራዕይን ለማሳካት በሚያስችል መልኩ የማቀናጀት ጥበብ ነው
- ስልታዊ ዕቅድ ምን ምን ግብዓቶችን እንደምትጠቀም፣ መቼ እንደምትጠቀም፣ እና እንዴት እንደምትጠቀም ይገልጻል

## II. ቤተ ክርስቲያን ስልታዊ ዕቅድ የሚያስፈልጋት ለምንድን ነው?

- ለመጪው ጊዜ መንገድ ለመቀየስ
  - ለመጪው ጊዜ ዕድገት እና መስፋፋት መሠረት ለመጣል

    ***"እኔ የምለውን ኢታደርጉም፤ ታዲያ ለምን፣ 'ጌታ ሆይ፤ ጌታ ሆይ' ትሉኛላችሁ? 47 ወደ እኔ የሚመጣ፣ ቃሌንም ሰምቶ የሚፈጽም ሁሉ ማንን እንደሚመስል ላሳያችሁ፤ 48 ቤት ለመሥራት አጥልቆ የቈፈረና በዐለት ላይ መሠረቱን የመሠረተ ሰው ይመስላል፤ ጐርፍ በመጣ ጊዜ የውሃው ሙላት ያን ቤት ገፋው፤ በሚገባ ስለ ታነጸም ሊያነቃንቀው አልቻለም። 49 ቃሌን ሰምቶ የማይፈጽም ግን ቤቱን ያለ መሠረት በዐፈር ላይ የሠራን ሰው ይመስላል፤ የወንዝ ሙላትም ቤቱን በመታው ጊዜ ወዲያው ወደቀ፤ ክፉኛም ፈራረሰ።"*** **– ሉቃስ 6፥46-49**

  - የቤተ ክርስቲያንን ዘርፈ ብዙ ተግባራት እና አገልግሎቶች አቅጣጫ ለመስጠት እና መንገድ ለመምራት
- ትኩረት የሚያስቱ ነገሮችን ለማስወገድ
  - አትኩሮት ከራዕይ እና ከተልዕኮ ላይ እንዳይነሣ ለማገዝ

***“እንግዲህ እነዚህን የመሳሰሉ ብዙ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን ካሉልን፣ ሸክም የሚሆንብንን ሁሉ፣ በቀላሉም ተብትቦ የሚይዘንን ኀጢአት አስወግደን በፊታችን ያለውን ሩጫ በጽናት እንሩጥ።” – ዕብራውያን 12፥1***

  - *መንገድ ስቶ መሄድን ለመከላከል*

- *ግብዓቶችን ውጤታማ በሆነ እና አግባብነቱን በጠበቀ መልኩ ሳያባክኑ ለመጠቀም*
  - *ግብዓቶች በአግባቡ ያለ ብክነት ጥቅም ላይ እንዲውሉ*
  - *ጥቅም ላይ ከሚውሉ ግብዓቶች ከፍተኛ የሆነ ውጤት ለማግኘት*

- *ወደ ፊት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ግጭቶችን ለመከላከል*
  - *የግብዓቶች አጠቃቀም ላይ የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለማስወገድ*
  - *እርስ በርስ የሚጋጩ ግቦችን ለማስወገድ*

## III. *ስልታዊ ዕቅድ ምን ምንን ያካትታል?*

*ስልታዊ ዕቅድ 7 ነገሮችን ያካትታል። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው፡-*

**1. *የራዕይ መግለጫ***
  - *ለማሳካት የምትፈልገውን ውጤት ይገልጻል*
  - *የመጨረሻ **ግብህ** ምንድን ነው?*

**2. *የመሻቶች መግለጫ***
  - *ራዕዩን ለማሳካት የሚያስፈልግህን ነገር ይገልጻል*
  - *እዚህ ላይ ትኩረትህ **ምን** እንደሚያስፈልግህ እንጂ እንዴት እንደምታገኘው አይሁን*

**3. *የክንዋኔ ዕቅድ***
  - *እያንዳንዱን መሻት በተመለከተ ተያይዘው የሚመጡ ክንዋኔዎችን ወይም ተግባሮችን ለይተህ አስቀምጥ*
    - *እያንዳንዱ መሻት **እንዴት** እንደሚገኝ ዘርዝር*
    - *<u>በተለይ</u> ምን እንደምታደርግ ግለጽ*
  - *የትኞቹ ተግባራት ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ ወስን*
  - *ተግባሮች ወይም ፕሮጀክቶች በምን ቅደም ተከተል እንደሚከናወኑ እና እንደሚጠናቀቁ ወስን*
    - *አንዳንድ ድርጊቶች ከሌሎች አስቀድመው መከናወን ሊኖርባቸው ይችላል*
    - *አንዳንድ ክንዋኔዎች ለአገልግሎትህ ወሳኝ ሊሆኑ ይችላሉ*

**4. *የጊዜ ወሰን***
  - *አንድ ተግባር መቼ እንደሚደረግ ይገልጻል*
  - *እያንዳንዱ ተግባር ወይም ክንዋኔ ምን ያህል ጊዜ እንደሚወስድ ለይቶ ያስቀምጣል*
  - *አንድ ተግባር ወይም ክንዋኔ መቼ መጠናቀቅ እንዳለበት ይገልጻል*

**5. *ግብዓቶች***
  - *ቀድሞውኑ ካሉ ግብዓቶች ውስጥ የትኞቹ ያስፈልጋሉ?*
    - *ሰዎች ሥራውን ለመሥራት ምን እንደሚያስፈልጋቸው ይገልጻል*

  - ምን ቁሳቁስ እንደሚያስፈልግ ለይቶ ያስቀምጣል
  - ለምን ለምን ጉዳይ የገንዘብ ግብዓቶች እንደሚያስፈልጉ ይወስናል

- ምን ምን አዳዲስ ግብዓቶች ያስፈልጋሉ?
  - ስፍራዎች/ቦታዎች
  - ቁሳቁስ
  - ሰዎች

- ምን ሥልጠና ያስፈልጋል?
  - አገልግሎቱን የሚመሩ ሰዎች
  - አገልግሎቱን የሚያከናውኑ ሰዎች

**6. ዘዴዎች**

- ያሉህን ዕድሎች በማያሻማ መልኩ በግልጽ ለይተህ እወቅ
- የአባላትህን ስጦታዎች እንዴት በሚገባ መጠቀም እንደምትችል ወስን
- አስቀድሞ ያሉህን ግብዓቶች እንዴት በሚገባ መጠቀም እንደምትችል ወስን

**7. መዋቅር**

- ማን ምን ሥልጣን እንደሚኖረው ወስን
  - ለፕሮጀክት/ትግበራ ውሳኔዎች
  - ከገንዘብ ጋር ለተያያዙ ውሳኔዎች

- ማን ኃላፊነቱን እንደሚወስድ ወስን
  - የፕሮጀክት/ትግበራ ግቦችን ለማሳካት
  - ተግባሮችን ከፍጻሜ ለማድረስ

- ምን ምን ቡድኖች እንደሚያስፈልጉ እና ማን ማንን እንደሚያካትቱ ወስን

## IV. ስልታዊ ዕቅድ የሚነደፈው እንዴት ነው?

ስልታዊ ዕቅድ ለመንደፍ የምንከተላቸው መሠረታዊ ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፡-

1. **ስልታዊ ዕቅድ የሚነድፍ ቡድን አዋቅር**
   - ቁልፍ ሰዎችን ምረጥ
   - ከሚሰጣቸው ሚና ጋር ተያያዥ ክህሎቶች ወይም የኋላ ታሪክ ያላቸውን ሰዎች ምረጥ
   - ለሥራው ቅንዓት ያላቸውን ሰዎች ምረጥ

2. **ዕቅድህን ዘርዝር**
   - ቀለል አድርገህ በመዘርዘር ጀምር
   - ራዕይህን እና ቁልፍ መሻቶችን አስቀምጥ

3. **ዕቅዱ ላይ ዝርዝር ነገሮችን ጨምር**
   - እያንዳንዱን መሻት ለማሟላት መደረግ ያለባቸውን ድርጊቶች ዘርዝረህ አስፍር
   - የእያንዳንዱን ድርጊት ዝርዝር ይዘት አብራራ
     - የጊዜ ወሰን

- ግብዓቶች
- ዘዴዎች
- መዋቅር

- ከቡድኑ የሚመጡ ሁሉንም ሐሳቦች/አስተያየቶች አጢን
- ዕቅዱን እያዳበርከው ሂድ

## 4. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ካሉ ከሌሎች ሰዎች የሐሳብ/አስተያየት ግብዓትን ሰብስብ

- ዕቅዱን ለማስፋት ወይም አዳዲስ ሐሳቦችን ለማካተት
- እጅግ አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉ ተጨማሪ አተያዮችን ለማግኘት
- በአንዳች እንቅፋት መቆም እንዳይከሰት ለመከላከል

## 5. በጽሑፍ የሰፈረ ሰነድ አዘጋጅ

- ዕቅድን በጽሑፍ ማስፈር ግርታን ለማጥራት ይረዳል
- አስተያየት እንዲሰጡበት ለሌሎች ሰዎች ሊሰራጭ ይችላል
- ለውይይት እና ለማመሳከሪያ መነሻ ነጥብ ሆኖ ያገለግላል
- ዕቅድ የመንደፍ ሂደቱ ተጨባጭ ውጤት ነው

## 6. ዕቅዱን አጠናቅቅ

- የመጨረሻ በጽሑፍ የሰፈረ ስልታዊ ዕቅድ አዘጋጅ
- የቡድን አባላቱ ዕቅዱን እንዲገመግሙ ፍቀድ
- ዕቅድ የመንደፍ ቡድን ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ሰው ሰነዱ ላይ እንዲፈርም አድርግ
    - ለመስማማታቸው እውቅና ይሰጣል
    - ወደፊት ሊፈጠሩ የሚችሉ ግጭቶችን ለማስወገድ ይረዳል

## 7. ዕቅዱን ይፋ አድርግ

- ቁልፍ ለሆኑ መሪዎች በጽሑፍ የዕቅዱን ቅጂ ስጥ
- ዕቅድህን ለጉባዔው ወይም ለአገልግሎት ክፍሉ/ሚኒስትሪው አቅርብ

# <u>ስልታዊ ዕቅድ የመንደፍ መልመጃ</u>

**የራዕይ መግለጫ** ______________________________________________
______________________________________________
______________________________________________

**ግብ ቁጥር 1፦** ______________________________________________

**ተግባራት፦**

1. ______________________________________________
2. ______________________________________________
3. ______________________________________________
4. ______________________________________________
5. ______________________________________________

**ግብ ቁጥር 2፦** ______________________________________________

**ተግባራት፦**

1. ______________________________________________
2. ______________________________________________
3. ______________________________________________
4. ______________________________________________
5. ______________________________________________

**ግብ ቁጥር 3፦** ______________________________________________

**ተግባራት፦**

1. ______________________________________________
2. ______________________________________________
3. ______________________________________________
4. ______________________________________________
5. ______________________________________________

**ግብ ቁጥር 4፦** ______________________________________________

**ተግባራት፦**

1. ______________________________________________
2. ______________________________________________
3. ______________________________________________
4. ______________________________________________
5. ______________________________________________

**ምዕራፍ 10**

# <u>*ገንዘብ አያያዝ*</u>

***"እግዚአብሔርንና ገንዘብን በአንድነት ማገልገል አይቻልም።"* – ማቴዎስ 6፥24**

ከሞላ ጎደል ሁሉም አገልግሎቶች መጠኑ ይለያይ እንጂ ሥራቸውን ለመሥራት ገንዘብ ያስፈልጋቸዋል። የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ የሚያሟሉትም አብዛኛውን ጊዜ አባላት ከሚሰጡት ልገሳ እና ስጦታ ነው። እንደ የቤተ ክርስቲያን መሪ፣ ሁሉም ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጥ ገንዘብ በትክክል መመዝገቡን፣ እንዲሁም ሁሉም ለአገልግሎት የሚደረጉ ወጪዎች ምክንያታዊ እና በአግባቡ የተወራረዱ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለብህ። ይህ በሕግም ጭምር የተቀመጠ ግዴታ ቢሆንም፣ በይበልጥ ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትዕዛዝም ነው! የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ በአግባቡ ይዘህ ማስተዳደርህ ለእግዚአብሔር እና ለቤተ ክርስቲያኒቱ አባላት ተዓማኒ መሆንህን ያሳያል። ገንዘብ ላይ ከፍተኛ የሆነ ሃቀኝነት ከሌለ፣ የነገሮችን ሁሉ መበላሸት እና ችግር እንደሚያስከትል መጽሐፍ ቅዱስ ያስጠነቅቃል። በዚህ ምዕራፍ፣ ገንዘብን በአግባቡ መያዝ ለምን አስፈላጊ እንደሆነ፣ ይህንን ማድረጊያ መርሆዎች፣ እንዲሁም ገንዘብን በተመለከተ ሃቀኝነትን መተግበሪያ መንገዶች እና ጥቅሞቹን እናያለን።

## I. *ገንዘብን በአግባቡ ይዞ ማስተዳደር ያን ያህል አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?*

1. መጽሐፍ ቅዱስ ገንዘብ ብዙ ችግር ሊያስከትል እንደሚችል ይናገራል
   ***"ምክንያቱም የገንዘብ ፍቅር የክፋት ሁሉ ሥር ነው"* – 1 ጢሞቴዎስ 6፥10**

- ደካማ የሆነ የገንዘብ አስተዳደር ውጥረት እና ሌሎች ችግሮችን ያመጣል
  - ሌሎች ኃጢአቶች ያስከትላል (ውሸት፣ ስርቆት፣ ምቀኝነት፣ ቁማር፣ ወዘተ)
    ***"ጽድቅ ቅን የሆነውን ሰው ትጠብቀዋለች፤ ክፋት ግን ኃጢአተኛውን ትጥለዋለች።"***
    **- ምሳሌ 13፥6**
  - ግንኙነቶችን ያበላሻል
    ***"ሐቀኛ ሰው ያለ ሥጋት ይራመዳል፤ በጠማማ ጐዳና የሚሄድ ግን ይጋለጣል።"***
    **- ምሳሌ 10፥9**
- ገንዘብ ወደ ግብ መድረሻ መንገድ እንጂ በራሱ ግብ አይደለም
  - ገንዘብ ግብህን ለማሳካት የምትጠቀመው አንድ መሣሪያ ነው
  - እግዚአብሔር ለእርሱ ሥራ የሚያስፈልገውን አቅርቦት ያደርጋል
- ገንዘብ በሰዎች ላይ በኃይል የመሠልጠን አቅሙ በተደጋጋሚ የታየ ነው
  - አብዛኛውን ጊዜ አጉል ውሳኔዎችን ያስከትላል
  - ወኅኒ መውረድ ሊያመጣ ይችላል
- ገንዘብ አምልኩኝ የሚል ጣዖት ሊሆን ይችላል
  **"እግዚአብሔርንና ገንዘብን በአንድነት ማገልገል አይቻልም።" – ማቴዎስ 6:24**
  - ገንዘብን ማሳደድ ሃሰተኛ አምላክን መከተል ነው
  - የገንዘብ ባሪያ ከሆንክ በክርስቶስ ያገኘኸውን ነጻነት ታጣለህ

2. ገንዘብን ያለ አግባብ መጠቀም እግዚአብሔርን ማጭበርበር ነው
    - ለቤተ ክርስቲያን የተሰጡ ግብዓቶች/ሃብቶች ለእግዚአብሔር የተሰጡ ናቸው
        - ያለን ነገር ሁሉ የእርሱ ነው፤ እኛ ባለ አደራዎች (አስተዳዳሪዎች) ብቻ ነን
        - እግዚአብሔር ያሉትን ሃብቶች እንዴት መጠቀም እንደሚገባ ዕቅድ አለው

    - ገንዘብን ያለ አግባብ መጠቀም ከመስረቅ አይተናነስም
        - ቤተ ክርስቲያንን መስረቅ ነው
        - እግዚአብሔርን መስረቅ ነው (**ሚልክያስ 3፥8**)
        - ስርቆት ፍቅርን አያሳይም

          ***"ፍቅር በባልንጀራው ላይ ክፉ አያደርግም"* – ሮሜ 13፥10**

3. የገንዘብ አስተዳደር ድክመት የባለ አደራነት ድክመት ነው
    - የባለ አደራነት አንዱ ድክመት ገንዘብን (የእግዚአብሔርን ሃብት) በጥበብ አለማስተዳደር ነው
        - የእግዚአብሔርን ስጦታዎች በጥበብ መጠቀም ለመንግሥቱ ፍሬ ያፈራል
        - የእግዚአብሔርን ስጦታዎች በሚገባ ማስተዳደር እግዚአብሔርን ያከብራል

4. መልካም የገንዘብ አስተዳደር መተማመንን ይገነባል
    - ገንዘብን በአግባቡ መያዝ ካልቻልክ፣ መንፈሳዊ ነገሮችንም በአግባቡ መያዝ አትችልም

      ***"እንግዲህ፣ በዚህ ዓለም ሀብት ካልታመናችሁ፣ እውነተኛውንማ ሀብት ማን አደራ ብሎ ይሰጣችኋል?"* - ሉቃስ 16፥11**

    - ሰዎች የሚተማመኑብህ አንተ በእግዚአብሔር የምትተማመን ከሆነ ነው

      ***"በትንሽ ነገር ታማኝ የሆነ በትልቁም ይታመናል፤ በትንሽ ነገር ያልታመነ በትልቁም አይታመንም።"* – ሉቃስ 16፥10**

## II. የገንዘብን አያያዝ መርሆዎች ምንድን ናቸው?

**"እርሱም፣ 'ከታዘዛችሁት በላይ ቀረጥ አትሰብስቡ…የማንንም ገንዘብ በግፍ አትንጠቁ፤ ሰውንም በሐሰት አትክሰሱ፤ ደመወዛችሁ ይብቃችሁ' አላቸው።"**
**ሉቃስ 3፥13-14**

1. እግዚአብሔር በሚሰጥህ ነገር የምትረካ ሁን
    - የሚያስፈልግህን ብቻ እንዲሰጥህ ጠይቀው
    - የሚያስፈልግህን ነገር እንደሚያሟላ በእግዚአብሔር ታመን

2. ገንዘብን ላልታሰበለት ዓላማ አትጠቀም
    - ገንዘብን ከጠየቅክበት ዓላማ ውጪ ለሌላ ነገር አትጠቀም
    - የሰዎችን ስጦታ አክብር

3. የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ ለግል ፍላጎትህ አትጠቀም
    - በግልህ ለሚያስፈልግህም ሆነ ለምትፈልገው ነገር ስትል በፍጹም ከቤተ ክርስቲያን ገንዘብ አትውሰድ
    - ሌሎች በግል ለሚፈልጉትም ሆነ ለሚያስፈልጋቸው ነገር በፍጹም የቤተ ክርስቲያንን ገንዘብ አትስጥ

4. ሁሉንም ገቢ የሆነ ገንዘብ በአግባቡ መዝግበህ አወራርድ
   - ሁሉንም ገቢ እና ስጦታ መዝግብ
   - ለተወሰነ ዓላማ ተብለው የተሰጡ ስጦታዎችን የተሰጡበትን ዓላማ መዝግበህ ለዚያው ዓላማ እንዲውሉ አድርግ
   - ትክክለኛ እና ጊዜውን የጠበቀ መዝገብ ይኑርህ

5. ወጪ የተደረገን ገንዘብ ሁሉ በአግባቡ መዝግበህ አወራርድ
   - ሁሉንም ወጪዎች መዝግብ
   - ለሁሉም ወጪዎች ደረሰኝ ይኑርህ

6. ከፍተኛ ወጪ ለሚደረግባቸው ግዢዎች የአሠራር ሂደት አኑር
   - ከፍተኛ ወጪ የሚደረግባቸው ግዢዎች ላይ አንድ ሰው ብቻ በሙሉ ሥልጣን እንዲወስን አትፍቀድ
   - ዋና ዋና ለሚባሉ ወጪዎች ሁሉ የቁጥጥር እና ሚዛን የመጠበቂያ ሥርዓት አኑር
   - ገንዘብ አውጥቶ ለመስጠት አንዳች ማረጋገጫ ሰነድ እንዲቀርብ ጠይቅ

7. በቋሚነት በየጊዜው የፋይናንስ መግለጫ አውጣ
   - ገቢ
   - ወጪ
   - የሁለቱ ሚዛን እና የገቢ/ወጪ ቀሪ (ባላንስ)

8. በየጊዜው የቤተ ክርስቲያንን የገንዘብ ይዞታ/ፋይናንስ የሚገመግሙ ገለልተኛ ሰዎችን ተጠቀም
   - ከቤተ ክርስቲያንህ ውጪ ያለ ሰው የፋይናንስ መዝገቦችን እንዲገመግም አድርግ
   - ዓመታዊ የፋይናንስ ቁጥጥር/ኦዲት አድርግ

## III. መልካም የሆነ የገንዘብ አያያዝ ተግባራዊ ማድረግ የሚቻለው እንዴት ነው?

1. መጽሐፍ ቅዱሳዊውን አሥራት (10%) የመስጠት ግዴታ አስተምር
   ***"በየዓመቱ ከእርሻህ ከምታገኘው ምርት ከአሥር አንዱን እጅ ለይተህ አስቀምጥ።"***
   **- ዘዳግም 14፥22**

   - በምሳሌ የምትመራ ሁን – ራስህ አሥራት ስጥ
   - በኩራት የመስጠት ልምምድን አበረታታ (**ምሳሌ 3፥9**)

2. የገንዘብ ሃቀኝነትን በተግባር አሳይ
   - ሁሉንም ገቢ እና ወጪ መዝግብ
   - በቅድሚያ ዕዳዎችን ክፈል
   - የቤተ ክርስቲያንን ገቢ ወጪ ለመገምገም እና ቁጥጥር/ኦዲት ለማድረግ አሠራሮችን አስቀምጥ

3. የሚያስፈልግህን ነገር ሁሉ እንደሚያቀርብ በእግዚአብሔር ተማመን
   - እርሱ የሚያስፈግህን ይሰጥሃል
   - እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ ግድ ይለዋል
     ***"በዚህ ዓለም ባለጠጎች የሆኑት እንዳይታበዩ፣ ደስም እንዲለን ሁሉን ነገር አትረፍርፎ በሚሰጠን በእግዚአብሔር እንጂ አስተማማኝነት በሌለው በሀብት ላይ ተስፋ እንዳያደርጉ እዘዛቸው።"***
     **- 1 ጢሞቴዎስ 6፥17**

4. የቤተ ክርስቲያን አባላት የቤተ ክርስቲያን የገንዘብ ፍሰትን እንዲያውቁ አድርግ
   - የገንዘብ ፍሰቱን ከቤተ ክርስቲያን አባላት አትደብቅ
   - ሁሉም ገቢ እና ወጪ ላይ ግልጽ እና እውነተኛ ሁን

## IV. መልካም የገንዘብ አያያዝ ምን ጥቅሞች አሉት?

1. ከቤተ ክርስቲያንህ አባላት ጋር መተማመንን ትገነባለህ
   - በገንዘብ አያያዝህ እምነት ከጣሉብህ፣ በሌሎች ነገሮችም እምነት ይጥሉብሃል
   - የቤተ ክርስቲያንህ አባላት በአንተ ላይ የመተማመን እና መንገድህን የመከተል ዕድላቸው ይጨምራል
   - የቤተ ክርስቲያንህ አባላት ይበልጥ ከገንዘብ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በአግባቡ መያዝ እንደምትችል እምነት ይጥሉብሃል

2. ሊፈጠሩ የሚችሉ አሳሳቢ ችግሮችን ታስወግዳለህ
   - ሰይጣን ሊፈትንህ እንዳይችል ታደርገዋለህ
   - ስግብግብነት በአንተ ላይ አይሠለጥንም
   - ንጽሕና እና ጽድቅህን ጠብቀህ በመቆየት ለመንጋህ በጎ ምሳሌ ትሆናለህ

3. የእግዚአብሔር ኃይል ሊያደርግ የሚችለውን ነገር ትማርበታለህ
   - እግዚአብሔር ለእያንዳንዱ ለሚያስፈልግህ ነገር እንዴት አቅርቦትን እንደሚያደርግ ፊት ለፊት ታያለህ
   - በእግዚአብሔር ቃልኪዳን ላይ እምነትን ታዳብራለህ
   - አስቀድመህ እርሱን መሻትን ትለምዳለህ
     ***"ከሁሉ አስቀድማችሁ ግን የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን እሹ፤ እነዚህ ሁሉ ይጨመሩላችኋል።"*– ማቴዎስ 6፥33**

# የገንዘብ አያያዝ መልመጃ

የገንዘብ አያያዝ (የገንዘብ ይዞታ አስተዳደርህን) ለማሻሻል ዛሬውኑ ማድረግ የምትችላቸውን ነገሮች ዘርዝር፡-

1. ______________________________
2. ______________________________
3. ______________________________
4. ______________________________
5. ______________________________
6. ______________________________
7. ______________________________
8. ______________________________
9. ______________________________
10. ______________________________

## ምዕራፍ 11

# <u>የጊዜ አጠቃቀም</u>

***"…ጥበበኛም ልብ ትክክለኛውን ጊዜና ተገቢውን አሠራር ያውቃል። … ለሁሉም ነገር ትክክለኛ ጊዜና ተገቢ አሠራር አለው።"***
**መክብብ 8፥5-6**

የትኛውንም ሙያም ሆነ ሥራ እንምረጥ፣ ሁላችንም ባሉን የተወሰኑ ግብዓቶች እና ባለን ጊዜ ብዙ ግቦችን ለማሳካት እንጥራለን። በርካታ ግብዓቶች ሊገዙ ወይም በተለያየ መንገድ ሊገኙ ቢችሉም፣ ጊዜ ግን ሊገዛ ወይም "አልቋል ይጨመር" ልንለው የምንችለው ነገር አይደለም። ጊዜ አንዴ ከሄደ ሄደ ነው። ድጋሚ ጥቅም ላይ ሊውል ወይም መልሶ ሊገኝ አይችልም። ስለሆነም፣ ጊዜያችንን እንዴት እንደምንጠቀመው እና ምን ላይ እንደምናውለው በጥንቃቄ ማሰብ አለብን። በተጨማሪም በአጠቃላይ ምን ያህል ጊዜ እንዳለን አናውቅም። ጌታ መቼ ወደ እርሱ እንደሚሰበስበን ማናችንም ስለማናውቅ፣ የተሰጠንን ጊዜ በተቻለ መጠን በሚገባ እና በጥበብ መጠቀማችን እጅግ አስፈላጊ ነው። የጊዜ አጠቃቀምን በተመለከተ ብዙ መጽሐፎች ተጽፈዋል፤ እኛ የምናደርገው ጊዜን በአግባቡ ለመጠቀም የሚያግዙ መርሆዎችን እና ዘዴዎችን በደምሳሳው መቃኘት ነው። በዚህ ምዕራፍ፣ የጊዜ አጠቃቀምን አስፈላጊነት፣ አንዳንድ የጊዜ አጠቃቀም መርሆዎችን፣ ጊዜን እንዴት በአግባቡ መጠቀም እንደሚቻል፣ እንዲሁም ለውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም የሚበጁ 2 ዘዴዎችን እናያለን።

## I. ጊዜን በአግባቡ የመጠቀም አስፈላጊነት

1. የበለጠ የአገልግሎት ሥራ እንዲሠራ ያግዝሃል
    - ያሰብከውን ለማሳካት ያግዝሃል
    - ይበልጥ አስፈላጊ የሆነው ሥራ ላይ እንድታተኩር ያግዝሃል
    - ጊዜህ ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መልኩ ሥራ ላይ ስለሚውል የበለጠ ውጤት ያስገኝልሃል

2. የጊዜ ብክነትን ያስወግዳል

    ***"እንግዲህ ጥበብ እንደሌላቸው ሳይሆን እንደ ጥበበኞች እንዴት እንደምትኖሩ ተጠንቀቁ። ቀኖቹ ክፉ ናቸውና ዘመኑን በሚገባ ዋጁ። ስለዚህ ሞኞች አትሁኑ፤ የጌታ ፈቃድ ምን እንደሆነ አስተውሉ እንጂ።"***
    **– ኤፌሶን 5፥15-16**

    - ቅድሚያ ሊሰጣቸው የማይገቡ ተግባሮች ላይ ከመጠን በላይ ጊዜ አታጠፋም
    - ውጤት የማያስገኝ ጊዜን ነቅተህ መከላከል ትችላለህ
    - ቀጥዬ ምን ላድርግ ብለህ በማሰብ ጊዜ አታጠፋም

3. አስፈላጊ የሆኑ ቀነ ገደብ የተቀመጠላቸው ሥራዎችን ለማጠናቀቅ እና ግቦችን ለማሳካት ያስችልሃል
    - የጊዜ ሰሌዳ እና ቀነ ገደቦችን እንድታስታውስ እና እንዳትስት ያደርግሃል
    - ወደ ግብህ በዘላቂነት እንድትገሰግስ ያስችልሃል
    - ተግባሮችህን ሁሉ በተቀናጀ እና ቅደም ተከተሉን በጠበቀ መልኩ እንድታከናውን ያስችልሃል

4. የሥራ ውጥረትን ለመቀነስ ይረዳሃል
    - አንዳች ወሳኝ ነገር ረስቼ ይሆን የሚለውን ጭንቀት ያስቀርልሃል

- የምታደርጋቸው ተግባሮች እና ፕሮግራምህን እንዳሻህ እንድታደርግ ያስችልሃል
- ለእረፍት የሚሆን ትርፍ ጊዜ ያስቀርልሃል
- ሁሉን ተወት አድርገህ ለእግዚአብሔር እንድትሰጥ ያስችልሃል!
  ***"በእግዚአብሔር ፊት ጸጥ በል፤ በትዕግሥትም ተጠባበቀው"*** **– መዝሙር 37፥7**
  ***"እረፉ፤ እኔም አምላክ እንደሆንሁ እወቁ"*** **– መዝሙር 46፥10**

5. በምትፈለግበት ጊዜ መገኘት እንድትችል ነጻ ጊዜ ይሰጥሃል
   - የአጭር ጊዜ ቀውሶችን በአግባቡ እንድታስተናግድ ያስችልሃል
   - ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች በጊዜ እንዲከናወኑ ያስችላል

## II. የጊዜ አጠቃቀም መርሆዎች

***"ሰው ሁሉ ማደግህን ያይ ዘንድ በእነዚህ ነገሮች ላይ አትኩር፤ በትጋትም ፈጽማቸው"***
**1 ጢሞቴዎስ 4፥15**

1. ለተግባሮችህ ቅደም ተከተል ስጥ
   - እንደ አስፈላጊነታቸው
   - መከናወን እንዳለባቸው ጊዜ
   - ካሉብህ መሰጠቶች አንጻር

2. ግልጽ እና የማያሻሙ ግቦችን አስቀምጥ
   - አንድ ሥራ መቼ መሠራት እንዳለበት
   - አንድን ሥራ ለመሥራት ምን ያህል ጊዜ እንደሚያስፈልግ
   - ያንን ሥራ ማን ሊሠራው እንደሚገባ

3. ተመሳሳይ ተግባሮችን በአንድ ላይ መድብ
   - ጊዜህን በአግባቡ ለመጠቀም አብረው የሚሄዱ ተግባሮችን በአንድ ምድብ አስቀምጥ
     - የስልክ ጥሪ እና ኢሜይል
     - የማማከር ክፍለ ጊዜዎች
     - የስብከት እና የትምህርት ዝግጅት
     - ስብሰባዎች

   - ከአንድ ዓይነት/ምድብ ተግባር ዘለህ ወደ ሌላው ዓይነት አትሂድ
     - ትኩረት ልታጣ ትችላለህ
     - አስቀድመህ የሠራኸውን ነገር ልትረሳው ትችላለህ

   - ከአንድ ተግባር ወደ ሌላ በመሄድ የሚባክን ጊዜን ትቀንሳለህ
     - ከአንድ ዓይነት ተግባር ወደ ሌላ ሲኬድ ብዙ ጊዜ ይጠፋል
     - አንድ ጊዜ አንድ ዓይነት የሥራ ሂደት ውስጥ ከገባህ፣ በዛው መቀጠሉ ይበልጥ ውጤታማ ነው

4. ውሳኔዎችህን በየቀኑ አድራጅ
   - ቆየት ብለው ሊደረጉ የሚችሉ ውሳኔዎችን ***<u>አዘግይ</u>***
   - ውሳኔዎቹን ለመፈጸም የተሻለ ብቃት ላላቸው ለሌሎች የመወሰኑን ኃላፊነት ***<u>አስተላልፍ</u>***
   - ውሳኔህን ወዲያውኑ የሚፈልጉ ጉዳዮች ላይ ወዲያውኑ ***<u>ወስን</u>***

5. የዕለት ተዕለት ፕሮግራምህን እንደ አስፈላጊነቱ ለመለዋወጥ ክፍተት ተው
    - እያንዳንዷን ደቂቃ የሚደለድል ጥብቅ የሆነ ፕሮግራም አታውጣ
    - ያልተጠበቀ ነገር ተፈጥሮ ፕሮግራምህን ሊነካ እንደሚችል ጠብቅ
    - ለእረፍት እና ለመመገቢያ ጊዜ መድብ
    - ካስፈለገ ቅደም ተከተልህን ወይም ፕሮግራምህን እንዲለውጥ እግዚአብሔርን ፍቀድለት
        - በአዲስ አገልግሎት ዕድል መልኩ
        - በአዲስ አተያይ መልኩ

6. የጊዜ ሰሌዳህን የሚጥሱ ጉዳዮችን ቶሎ ፈር አስይዝ
    - ፕሮግራምህን ጥሶ የመጣው ጉዳይ መቆየት የሚችል ከሆነ አቆየው
    - ችግሩን አጢነህ ማቆየት፣ ለሌላ ሰው አሳልፎ መስጠት ወይም መወሰን ይኖርብህ እንደሁ በቶሎ ወስን
    - ቶሎ ውሳኔ መስጠት ከቻልክ ወስነህ ፕሮግራምህን ቀጥል

## III. ጊዜን እንዴት በአግባቡ መጠቀም ይቻላል?

1. ቀንህን በሚገባ አደራጅተህ ደልድል
    - ማድረግ ያለብህን ነገሮች የሚገልጽ ዝርዝር አዘጋጅ
        - ዛሬ መጠናቀቅ ያለባቸውን ነገሮች አስቀምጥ
        - ዛሬ ሊሠሩ የሚገቡ ነገሮችን አስቀምጥ
        - ዛሬ መወሰን የሚገባቸውን ጉዳዮች አስቀምጥ
        - ጊዜ ካገኘህ ዛሬ ልትሠራ የምትወደውን ተጨማሪ ነገር አስቀምጥ

    - በሚገባ የታወቁ ግቦች እና የቅድሚያ አሰጣጥ ቅደም ተከተል ይኑርህ
        - ይበልጥ አስፈላጊው ነገር የቱ እንደሆነ እወቅ
        - የትኞቹን ግቦች ለማሳካት እየሠራህ እንደሆነ እወቅ
        - አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች በቅድሚያ አከናውን

    - አጫጭር የእረፍት ጊዜዎችን ዕቅድህ ውስጥ አካትት – አካልህ እና ኅሊናህ አልፎ አልፎ እረፍት ያሻቸዋል

    - ይበልጥ ውጤታማ የምትሆንበትን ሰዓት ለይተህ በማወቅ ይበልጥ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች በዚያ ሰዓት አከናውን
        - እጅግ አስፈላጊ የሆኑ ውሳኔዎችን በቀኑ መጨረሻ በደከመህ ሰዓት አትወስን
        - ያን ያህል ቅድሚያ የማትሰጣቸውን ጉዳዮች አቅምህ በቀነሰ ሰዓት (ለምሳሌ ከምሳ ሰዓት በኋላ፣ ወዘተ) ለማከናወን መድብ

2. ብክነትን አስወግድ
    - የስልክ ጥሪዎችን በተርታ በአንድ ጊዜ አድርግ
    - ለጥናት እና ለስብከት ዝግጅት የተወሰነ የማይረበሽ/የማይቋረጥ ጊዜ ይኑርህ
    - አስፈላጊ ያልሆኑ ጉዳዮች ወይም ግጭቶች ውስጥ ከመግባት ተቆጠብ
    - ዛሬ መደረግ ***ያለበትን*** ነገር አድርግ

3. ሌሎች ሊያደርጓቸው የሚችሉ ነገሮች ላይ ጊዜ አታጥፉ
    - ከተቻለ ለሌሎች ኃላፊነት ለተሰጣቸው መሪዎች ሥራዎችን አስተላልፍ

- የግድ አስፈላጊ ካልሆነ በስተቀር ሌሎች ሊያደርጉ የሚገባቸውን ነገር አንተ አታድርግ
    - “ለሰው ውለታ ብለህ የሠራኸው ነገር፣ ቀጥሎ ሥራህ ሆኖ ይገኛል” የሚል የቆየ አባባል አለ (ማለትም፣ ለሌሎች የምትሠራቸው ትናንሽ ነገሮች ልማድ ይሆኑና መሰጠትህን የሚጠይቁ እና ለማቋረጥ የሚያስቸግሩ ይሆኑብሃል)

4. ስብሰባዎችን ውጤታማ በሆነ መልኩ አከናውን
    - ከእግዚአብሔር ምሪት ለመጠየቅ ጥሞና እና ጸሎት አካትት

    - ሁልጊዜ የስብሰባውን አጀንዳ አዘጋጅ
        - አጀንዳው ላይ ያልተያዙ ነጥቦች ላይ ውይይት እንዳይካሄድ አድርግ
            - ሰዎች በጉዳዩ ላይ ለመወያየት ተዘጋጅተው ስላልመጡ
            - አብዛኛውን ጊዜ ለውይይት ከተነሡት ነጥቦች ጋር ተያያዥ ስለማይሆኑ
        - ከተያዘው አጀንዳ እና ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ አትውጣ

    - ውሳኔ ሊሰጥባቸው የሚችሉ ሃሳቦች እና ምክረ ሃሳቦች ላይ ብቻ ውይይት ይደረግ
        - የሃሳብ ግብዓት ለመሰብሰብ ካልሆነ በስተቀር ከእነዚህ ውጪ የሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ውይይት አታድርጉ
        - ስብሰባው ቁልፍ በሆኑ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩር ያግዛል
        - ወደ ውሳኔ የሚያመሩ ውይይቶች እንዲካሄዱ ያስችላል

    - ሥራ መድበህ ስጥ
        - ሂደቱ ላይ የባለቤትነት ስሜት እና የቡድን መንፈስን ይገነባል
        - ሁሉም የስብሰባው ተሳታፊ ተጠያቂነት እንዲኖረው ያስችላል

    - ውይይቶች፣ ውሳኔዎች እና ስምምነቶችን በስብሰባው ቃለ ጉባዔ በኩል ተመዝግበው እንዲያዙ አድርግ
        - ውይይቱ በሰነድ ይያዝ
        - የተደረሰበት ውሳኔ በሰነድ ይያዝ
        - ሰዎች ተስማምተው የተቀበሏቸው የሥራ መደቦች በሰነድ ያያዙ

## IV. የውጤታማ ጊዜ አጠቃቀም ሁለት ዘዴዎች

1. የጊዜ ሠንጠረዥ አዘጋጅ (ወይም ዕለታዊ አሊያም ወርሃዊ የቀን መቁጠሪያ ተጠቀም)
    - በሳምንቱ ወይም ቀድመው ፕሮግራም በተደረጉ ክንዋኔዎች ውስጥ የጊዜ አጠቃቀምህን ለመከታተል ተጠቀምበት
        - ጊዜህ በምን በምን እንደሚያልፍ አይተህ እንድትገመግም ያግዝሃል
        - የሳምንት ፕሮግራምህን ለማቀድ ልትጠቀመው ትችላለህ

2. ማድረግ ያለብህን ነገሮች የሚገልጽ ዝርዝር አዘጋጅ
    - ቀንህ፣ ሳምንትህም ሆነ ወርህ የተደራጁ እንዲሆኑ ያግዝሃል
    - ይበልጥ አስፈላጊ የሆነውን የአገልግሎት ሥራ ቅድሚያ እንድትፈጽም ያስችልሃል
    - አስፈላጊ የሆኑ ተግባሮች እና ቃል ገብተህ በፕሮግራም የያዝካቸው ነገሮችን እንዳትረሳ ይከላከላል

# <u>የጊዜ አጠቃቀም መልመጃ</u>

ከዚህ በታች የተቀመጠውን የጊዜ ዕቅድ ማውጫ ሠንጠረዥ በመጠቀም ጊዜህን እንዴት እንደምታሳልፍ የተለመደ ፕሮግራም ያሉህን ቀኖች (ለምሳሌ የዕረፍት ቀን፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት፣ የስብከት ዝግጅት፣ ሳምንታዊ የአምልኮ ጊዜ፣ ወዘተ) እና ሰዓታት ምልክት አድርግባቸው። የቀረህ ጊዜ እንደ አስፈላጊነቱ ባሉብህ ሌሎች ተግባሮች የምትሞላው ይሆናል።

| | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ | እሁድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **2:00 ጠዋት** | | | | | | | |
| **2:30** | | | | | | | |
| **3:00** | | | | | | | |
| **3:30** | | | | | | | |
| **4:00** | | | | | | | |
| **4:30** | | | | | | | |
| **5:00** | | | | | | | |
| **5:30** | | | | | | | |
| **6:00** | | | | | | | |
| **6:30** | | | | | | | |
| **7:00** | | | | | | | |
| **7:30** | | | | | | | |
| **8:00** | | | | | | | |
| **8:30** | | | | | | | |
| **9:00** | | | | | | | |
| **9:30** | | | | | | | |
| **10:00** | | | | | | | |
| **10:30** | | | | | | | |
| **11:00** | | | | | | | |
| **11:30** | | | | | | | |
| **12:00 ማታ** | | | | | | | |
| **12:30** | | | | | | | |
| **1:00** | | | | | | | |
| **1:30** | | | | | | | |
| **2:00** | | | | | | | |
| **2:30** | | | | | | | |
| **3:00** | | | | | | | |
| **3:30** | | | | | | | |

# <u>የጊዜ አጠቃቀም ማሳያ ናሙና</u>

| | ሰኞ | ማክሰኞ | ረቡዕ | ሐሙስ | አርብ | ቅዳሜ | እሁድ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **2:00 ጠዋት** | | የስልክ ጥሪዎች | | መ/ቅ ጥናት | | የቤተ ሰብ ጊዜ | |
| **2:30** | | የስልክ ጥሪዎች | | መ/ቅ ጥናት | | የቤተ ሰብ ጊዜ | |
| **3:00** | | ቢሮ | | መ/ቅ ጥናት | ማማከር | የቤተ ሰብ ጊዜ | አምልኮ |
| **3:30** | | ቢሮ | | መ/ቅ ጥናት | ማማከር | የቤተ ሰብ ጊዜ | አምልኮ |
| **4:00** | | ቢሮ | | | ማማከር | የቤተ ሰብ ጊዜ | አምልኮ |
| **4:30** | | ቢሮ | | | ማማከር | የቤተ ሰብ ጊዜ | አምልኮ |
| **5:00** | | | | | | | አምልኮ |
| **5:30** | | | | | | | አምልኮ |
| **6:00** | ምሳ | ምሳ | ምሳ | ምሳ | ምሳ | | ምሳ |
| **6:30** | ምሳ | ምሳ | ምሳ | ምሳ | ምሳ | | ምሳ |
| **7:00** | | | | ጉብኝት | | | |
| **7:30** | | | | ጉብኝት | | | |
| **8:00** | | | ስብከት ዝግጅት | ጉብኝት | | | |
| **8:30** | | | ስብከት ዝግጅት | ጉብኝት | | | |
| **9:00** | | | ስብከት ዝግጅት | | | | |
| **9:30** | | | ስብከት ዝግጅት | | | | |
| **10:00** | | | | | | | |
| **10:30** | | | | | | | |
| **11:00** | እራት | እራት | እራት | እራት | እራት | | |
| **11:30** | እራት | እራት | እራት | እራት | እራት | | |
| **12:00 ማታ** | | | | | | | |
| **12:30** | | | | | | | |
| **1:00** | | ስብሰባ | | | | ለእሁድ ዝግጅት | |
| **1:30** | | ስብሰባ | | | | ለእሁድ ዝግጅት | |
| **2:00** | | ስብሰባ | | | | ለእሁድ ዝግጅት | |
| **2:30** | | | | | | ለእሁድ ዝግጅት | |
| **3:00** | | | | | | | |
| **3:30** | | | | | | | |

## ምዕራፍ 12

# <u>መረጃ ማደራጀት</u>

**"ጠቢባን ዕውቀት ያከማቻሉ"**
**ምሳሌ 10፥14**

በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሲበዛ ቸል ከሚባሉ ግብዓቶች ውስጥ አንዱ መረጃ ነው። መረጃው ስለ ቤተ ክርስቲያን አባላት፣ ስለ ቤተ ክርስቲያኒቱ አገልግሎቶች፣ ተግባራት ወይም ስለ ልዩ ልዩ ግብዓቶች/ሃብቶች ሊሆን ይችላል። የተጠራንበትን አገልግሎት በሚገባ እንድናገለግል የሚያግዝ የመረጃ ሃብት አለ፤ ስለሆነም ያ መረጃ የት እንደሚገኝ እና እንዴት ማግኘት እንደሚቻል ማወቁ አስፈላጊ ነው። አንዳንዱ መረጃ (ለምሳሌ አባላትን እና የእነርሱን ተግባራት እና ስጦታዎች የተመለከተ መረጃ ወዘተ) በቤተ ክርስቲያን ተሰብስቦ መቀመጥ ሊኖርበት ይችላል። ሌሎች መረጃዎች ደግሞ ከኢንተርኔት ወይም ከቤተ መጻሕፍት ወይም ከመጻሕፍት መደብር ሊገኙ ይችላሉ። የሚያስፈልገንን መረጃ በጊዜው ማግኘት እንድንችል፣ አዘጋጅተን ልናስቀምጠው ወይም የት እንደምናገኘው ልናውቅ ይገባል። ይህ የመረጃ አደረጃጀት ሂደት ነው። ይህንን ለማድረግ ኮምፒዩተር በጣም ጠቃሚ ቢሆንም፣ መረጃን ለማስቀመጥ ግን የግድ ኮምፒዩተር አያስፈልግም። ውጤታማ የሆኑ ሌሎች ዘዴዎችን መጠቀም ትችላለህ። በዚህ ምዕራፍ፣ መረጃን የማደራጀትን አስፈላጊነት፣ የመረጃ ማደራጀት አንዳንድ መርሆዎችን፣ እንዲሁም ለወደፊት የአገልግሎት ጥቅም መረጃን እንዴት መሰብሰብ እና ማስቀመጥ እንደሚቻል እናያለን።

## I. *መረጃን የማደራጀት አስፈላጊነት*

***"አስተዋይ ሰው ሥራውን በዕውቀት ያከናውናል"***
**ምሳሌ 13፥16**

1. ልትጠቀማቸው የምትችላቸው ግብዓቶች ላይ ያለህን እውቀት ይጨምራል
   - የአባላትህ መንፈሳዊ ስጦታዎች እና ክህሎቶች ላይ ያለ መረጃ
   - ሌሎች የቤተ ክርስቲያን ሃብቶች (መጻሕፍት፣ ቪዲዮዎች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች፣ ወዘተ) ላይ ያለ መረጃ
   - የቤተ ክርስቲያን ተግባሮች እና አገልግሎቶች (ማን፣ ምን እና የት የሚለውን የሚገልጽ) መረጃ

2. መረጃ በመፈለግ የጊዜ መጥፋትን ይከላከላል
   - ሰነዶችን በመፈለግ ከመጠን በላይ ጊዜ አታጠፋም
   - በተለይ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ለማግኘት ማን ጋር መሄድ እንዳለብህ ታውቃለህ
   - የምትፈልገውን መረጃ ለማግኘት ሰዎች ጋር መሄድ አያስፈልግህም

3. የተሻሉ ውሳኔዎችን ለመስጠት ያስችልሃል
   - የውሳኔ ትክክለኛነት የሚመሠረተው ግብዓት በሆነው መረጃ ላይ ነው
   - በሚያስፈልግበት ጊዜ መረጃን ዝግጁ አድርጎ መጠበባቅ ወሳኝ ነው
   - እርግጡን ማወቅ ከመገመት ይሻላል

4. ጥሩ ዕቅድ ለማውጣት ወሳኝ ነው
    - የዕቅድ አስተማማኝነት የሚመሠረተው ግብዓት በሆነው መረጃ ላይ ነው
    - የመረጃ ክፍተት የሚገኘው ውጤት አመርቂ እንዳይሆን ያደርጋል
    - በማታውቀው ነገር ላይ ዕቅድ ልታወጣ አትችልም

5. ለአገልግሎት የሚሆኑ ዕድሎችን ለማየት ያስችልሃል
    - ያሉህን ነገሮች ማወቅ ፈጠራ በታከለበት መልኩ ግብዓቶችን እንድትጠቀም ያስችልሃል
    - የአገልግሎት ዕድሎችን እንድትጠቀም ያስችልሃል
        - የአባላትን ስጦታዎች እና ቅንዓቶች በማወቅህ ላይ በመመሥረት
        - ማኅበረ ሰቡ ያሉበትን መሻቶች በማወቅህ ላይ በመመሥረት

## II. *የመረጃ አደረጃጀት መርሆዎች*

**“*ከጠቢብ ጋር የሚሄድ ጠቢብ ይሆናል*”**
**ምሳሌ 13፥20**

1. የምትፈልገውን ወይም የሚያስፈልግህን መረጃ ብቻ ሰብስበህ አስቀምጥ
    - ለውሳኔ ግብዓት የሚያስፈልግ መረጃ
    - የቤተ ክርስቲያንን የዕለት ተዕለት ተግባር ለማካሄድ የሚያስፈልግ መረጃ
    - አባላት በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያላቸውን ሚና እንዲያውቁ ለማገዝ የሚያስፈልግ መረጃ

2. በመደበኛነት በየጊዜው የሰበሰብከውን መረጃ ከጊዜው ጋር አዘምን
    - መረጃ በፍጥነት ጊዜ እያለፈበት በመሄድ ምንም የማይጠቅም ሊሆን ይችላል
    - መረጃ መሰብሰቢያ ሂደቶችን ንደፍ
        - በየክፍለ ጊዜው ያለውን እና የቀረውን መከታተያ
        - አዲስ አባል መመዝገቢያ ቅጽ
    - መረጃ ለመሰብሰብ የቤተ ክርስቲያን መሪዎችን ተጠቀም
        - የአገልግሎት ተሳታፊዎች
        - የአገልግሎት ውጤቶች እና ተግባራት
    - በየዓመቱ ከጊዜው ጋር የሚቀየር የቤተ ክርስቲያን አባላት መረጃ ሊኖር ስለሚችል እንዲህ ያለ መረጃው መሰብሰቢያ ቅጽ ተጠቀም
        - የአድራሻ ለውጥ
        - አዳዲስ የስልክ ቁጥሮች እና የኢሜይል አድራሻዎች

3. የግለሰብ መረጃ ደኅንነትን ጠብቅ
    - ያ አባል ተስማምቶ ካልሆነ በቀር የአንድን አባል የግል መረጃዎች ይፋ አታድርግ
    - በሚቆለፍ ማስቀመጫ ውስጥ መረጃውን አኑር
    - ምስጢራዊነቱን ጠብቅ

4. መረጃውን ለመጠቀም በሚቀል መልኩ አስቀምጥ
    - በሚያገለግልበት ጉዳይ (ርዕስ፣ ዓላማ፣ ጥቅም፣ ወዘተ)
    - በአገልግሎት ዘርፍ
    - በአባል ስም

5. መረጃውን የምትጠቀምበት ዕቅድ ይኑርህ
    - ለመጠቀም ዕቅድ ሳይኖርህ እንዲሁ መረጃ አትሰብስብ
    - እያንዳንዱ የምትሰበስበውን መረጃ ዓይነት ለምን ዓላማ እንደምትሰበስበው እወቅ
    - ካላስፈለገህ፣ መረጃውን ሰብስበህ አታስቀምጥ

6. መረጃውን አደራጀው
    - ሳታጣራ መረጃ እየተሰበሰበ እና እየተቀመጠ ነው የሚል ግምት አትያዝ
    - ከጊዜው ጋር የሚሄድ/የዘመነ መሆኑን አረጋግጥ
    - በየጊዜው የሚያስፈልግህን የመረጃ ፍላጎት ገምግም

## III. መረጃ የሚደራጀው እንዴት ነው?

1. የምትፈልገውን ወይም የሚያስፈልግህን መረጃ ለይተህ እወቅ
    - የቤተ ክርስቲያን አባላት
    - የቤተ ክርስቲያን ተግባራት
    - የቤተ ክርስቲያን ግብዓቶች (መጻሕፍት፣ ክፍሎች፣ ቁሳቁስ፣ ወዘተ)
    - በማኅበረ ሰቡ ውስጥ የሚገኙ ግብዓቶች (ሆቴሎች፣ መሰብሰቢያ አዳራሾች፣ ዕቃ አቅራቢዎች፣ ወዘተ)

2. የቤተ ክርስቲያን አባላትን በተመለከተ መረጃ ሰብስበህ አስቀምጥ
    - ስማቸው፣ አድራሻቸው፣ ስልክ ቁጥራቸው፣ ኢሜይል አድራሻቸው
    - መንፈሳዊ ስጦታዎቻቸው
    - ክህሎት እና ልምዳቸው
    - በቤተ ክርስቲያን የሚያደርጉት እንቅስቃሴ እና ከሰዎች ጋር ያሏቸው ተያያዥነቶች

3. የቤተ ክርስቲያን ተግባራት ላይ መረጃ ሰብስበህ አስቀምጥ
    - የአምልኮ ፕሮግራም ተሳታፊ ቁጥር
    - የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ተሳታፊ ቁጥር
    - የአነስተኛ ቡድን ስብሰባ ተሳታፊ ቁጥር

4. መረጃ አጠናቅሮ ማስቀመጫ እና አንድን የተለየ መረጃ ፈልጎ ማግኛ ሥርዓት ንደፍ
    - መረጃው የት እንደተቀመጠ መታወቅ አለበት (በኮምፒዩተርም ይሁን በወረቀት)
    - ጠቃሚ የሆኑ ድረ ገጾችን ተጠቀም
    - መረጃው ማን ጋር እንደሆነ መታወቅ አለበት

5. መረጃውን ጥቅም ላይ ማዋያ ዕቅድ ንደፍ
    - ምን መረጃ ይሰበሰባል?
    - እያንዳንዱ የመረጃ ዓይነት የሚሰበሰብበት ዓላማ ምንድን ነው?
    - መረጃውን የመሰብሰቡ ኃላፊነት የማን ነው?

6. መረጃውን የማደራጀቱን ኃላፊነት ለአንድ ሰው መድብ
    - መረጃ መሰብሰብ ቀጣይነት ያለው ሥራ ነው
    - ለሁሉም መረጃ ማዕከላዊ ሰው ይኖራል
    - በደንብ ለማቀድ እና መረጃውን ጠብቆ ለማቆየት ያስችላል

# <u>መረጃ የማደራጀት ዕቅድ አወጣጥ መልመጃ</u>

**ከዚህ በታች የቀረበውን ሠንጠረዥ በመጠቀም ለቤተ ክርስቲያንህ ወይም ለአገልግሎትህ/ሚኒስትሪህ የሚሆን የመረጃ ማደራጀት ዕቅድ አውጣ፡-**

| የሚሰበሰበው መረጃ | ዓላማው | መረጃውን የሚሰበስበው ማነው? | መረጃው እንዴት ይሰበሰባል? |
|---|---|---|---|
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |
| | | | |